# የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ

# ዋስትና ኤጀንሲ

# የግዥ አፈጻጸም መመሪያ

ቁጥር 329/2013

ግንቦት 7 ቀን 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ


| አንቀጽ | የአንቀጹ ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ክፍል አንድ | ጠቅላላ | 1 |
| 1 | አጭር ርዕስ | 1 |
| 2 | ትርጓሜ | 1 |
| 3 | የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን | 3 |
| 4 | የመመሪያው ዓላማ | 3 |
| 5 | መርሆዎች | 3 |
| ክፍል ሁለት | ተግባርና ኃላፊነት | 4 |
| 6 | የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ኃላፊነት | 4 |
| 7 | የግዥ ሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት | 6 |
| 8 | የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት | 9 |
| ክፍል ሦስት | የግዥ ዕቅድ | 10 |
| 9 | የግዥ ዕቅድ ስለማዘጋጀት | 10 |
| 10 | የግዥ ፍላጎትን መለየት ማሰባሰብና ማደራጀት | 11 |
| 11 | የግዥ ዘዴ መምረጥ | 12 |
| 12 | የግዥ መፈጸሚያ ጊዜን መወሰን | 12 |
| 13 | የግዥ ዕቅድ ይዘት | 13 |
| 14 | የግዥ ዕቅድ የሚፀድቅበት እና የሚሻሻልበት ሁኔታ | 13 |
| 15 | ዓመታዊ የግዥ ዕቅድን ይፋ ማድረግ | 14 |
| ክፍል አራት | የግዥ ዘዴዎች አፈጻጸማቸው | 14 |
| 16 | የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች | 14 |
| 17 | የብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ግዥ አፈጻጸም | 15 |
| ክፍል አምስት | የዓለም አቀፍ ግዥ አፈጻጸም | 48 |
| 18 | ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ | 48 |
| 19 | ሌሎች ዓለም አቀፍ ግዥዎች | 49 |
| 20 | በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ | 50 |
| 21 | የሁለት ደረጃ ጨረታ አፈጻጸም | 50 |
| 22 | በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ | 51 |
| 23 | የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ | 52 |
| 24 | በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ጨረታ | 54 |
| 25 | የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ | 60 |

| አንቀጽ | የአንቀጹ ርዕስ | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| 26 | የውስን ጨረታ ግዥ አፈጻጸም | 60 |
| 27 | በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ | 62 |
| 28 | ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ | 64 |
| ክፍል ስድስት | ልዩ ግዥ | 68 |
| 29 | የማዕቀፍ ግዥ | 68 |
| ክፍል ሰባት | የውል አስተዳደር | 69 |
| 30 | ውልን ተፈጻሚ ማድረግ | 69 |
| 31 | የውል አፈጻጸምን መከታተል | 70 |
| 32 | ውል ማጠናቀቅ | 71 |
| ክፍል ስምንት | ሌሎች ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች | 72 |
| 33 | መደበኛ ያልሆኑ የግዥ ጥያቄዎችን መመርመር | 72 |
| 34 | የግዥ ሰነዶች | 72 |
| ክፍል ዘጠኝ | የመንግሥት ግዥ ሥነ-ምግባር | 73 |
| 35 | ከግዥ ባለሙያ የሚጠበቅ ሙያዊ ሥነ-ምግባር | 73 |
| 36 | ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚጠበቅ ሥነ-ምግባር | 75 |
| ክፍል አሥር | በተቋሙ ግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብ አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ | 76 |
| 37 | የኮሚቴ አባላት ስያሜና የሥራ ዘመን | 76 |
| 38 | የኮሚቴ ስብሰባ | 76 |
| 39 | ከኮሚቴ አባልነት መልቀቅ | 76 |
| 40 | የኮሚቴ አባልነት መቋረጥ | 77 |
| 41 | የጥቅም ግጭትን ስለመግለጽ | 77 |
| 42 | የኮሚቴ ሥልጣን | 77 |
| 43 | የኮሚቴ ተግባር | 78 |
| ክፍል አሥራ አንድ | ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወይም የግዥ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ የሚቀርብ አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት | 78 |
| 44 | የዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች አቤቱታ የማቅረብ መብት | 78 |
| 45 | አቤቱታ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች | 79 |
| 46 | ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር የሚቀርብ አቤቱታ የሚጣራበት ሥርዓት | 79 |
| 47 | የተቋሙን የግዥ አፈጻጸም ሂደትን ስለማገድ | 80 |
| 48 | አቤቱታ ለኮሚቴው የሚቀርብበትና የሚጣራበት ሥርዓት | 81 |
| 49 | አቤቱታን በፍርድ ቤት ስለማቅረብ | 82 |

| አንቀጽ | የአንቀጹ ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ክፍል አሥራ ሁለት | ልዩ ልዩ | 82 |
| 50 | ከአቅም በላይ የሆነ ችግር | 82 |
| 51 | የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት | 82 |
| 52 | መመሪያውን ስለማሻሻል | 83 |
| ክፍል አሥራ ሦስት | ይህ መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ | 83 |
| 53 | መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ | 83 |


## አባሪዎች


| | | |
|---|---|---|
| አባሪ አንድ | ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ | 1 |
| አባሪ ሁለት | የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢና ፀሐፊ ዋና ዋና ኃላፊነቶች | 1 |
| አባሪ ሦስት | ጨረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ | 1-2 |
| አባሪ አራት | በቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ለመንገድ ሥራ እና ለሕንፃ ግንባታ የሚገዙት ማሽነሪዎች ዝርዝር | 1 |
| አባሪ አምስት | በተጫራቾች የሚሞላ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና | 1 |
| አባሪ ስድስት | በግንባታ ሥራ ግዥ የብቃት መስፈርት አወጣጥ | 1-6 |

# የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

## የግዥ አፈጻጸም መመሪያ

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 203/2003 የተቋቋመ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት በመሆኑ፤

ኤጀንሲው ከጡረታ ፈንዱ በሚመደብ በጀት እንደሚተዳደር በዚሁ ደንብ አንቀጽ 11 የተደነገገና የተቋሙ የግዥ አፈጻጸም የሚመራበትን ራሱን የቻለ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የተቋሙ የግዥ አፈጻጸም ሕግንና ሥርዓት በተከተለ ሁኔታ እንዲመራ ማድረግ ስለሚገባና ማንኛውም የኤጀንሲው ግዥ ግልጽ አሠራር በመከተል የሚፈጸምበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በተለያዩ ጊዜያት በተጻፉ ደብዳቤዎች ተቋሙ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ እንደማይሸፈን በመገለጹ፤

የግዥ ሥራው የሚመራበትን ዝርዝር አፈጻጸም ሂደት፣የግዥ ፈጻሚዎች ኃላፊነትና ተጠያቂነት በግልጽ ማመልከት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህ መንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 329/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

2.1. የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

ሀ/ "የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ" ማለት ዕቃው፣ አገልግሎቱ፣ የግንባታ ሥራው ወይም የምክር አገልግሎቱ ሊያሟላ የሚገባውን ጥራት፣ ዓይነትና ደረጃ የሚገልጽ ሰነድ ነው፤

ለ/ "መደበኛ የጨረታ ሰነድ" ማለት በተቋሙ አጠቃላይ ይዘቱ አንድ ወጥ ወይም ተመሳሳይ የሆነ የጨረታ ሰነድ በቀላሉ ለማዘጋጀት የሚረዳ በተቋሙ የተዘጋጀ ሰነድ ነው፤

ሐ/ "ግዥ" ማለት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ስራዎችን፣ የምክር አገልግሎትና ሌሎች አገልግሎቶችን በግዥ፣ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል ማግኘት ነው፤

መ/ "የግዥ ሥራ ሂደት" ማለት በኤጀንሲው ግዥ ለመፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው የስራ ሂደት ወይም ቡድን ነው፤



የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

ሠ/ " አገልግሎት" ማለት ከዕቃ፣ ከግንባታ ዘርፍ ስራ እና ከምክር አገልግሎት ውጪ ያለ ሲሆን፣ የጥገና፣ የጽዳት፣የዕቃ መሸከምና ማመላለስ አገልግሎት፣የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የቴሌኮሙኒኬሽን እና የውሃ አቅርቦት የመሳሰሉትን ይጨምራል፤

ረ/ "የምክር አገልግሎት" ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚሰጡት የጥናት፣ የዲዛይን እና ቁጥጥር፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ለደንበኞች ምክር የመስጠት፣ ስልጠና የመስጠትና ዕውቀትን የማስተላለፍ የአማካሪነት ባህሪ ያለው የአዕምሮ አገልግሎት ነው፤

ሰ/ "የግንባታ ዘርፍ ስራ" ማለት ከህንጻ ፣ከዋና መሥሪያ ቤትና ጽ/ቤቶች ግንባታዎች ስራ ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ ግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣ ደረጃ የማሳደግ፣ የማፍረስ፣ የጥገና፣ የማደስ ስራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ስራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን፣የመገንባት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ስራውን የማንቀሳቀስና የማስተላለፍ ውሎችን ይጨምራል፤

ሸ/ "ጨረታ" ማለት የጨረታ ማስታወቂያ ይፋ ከሆነበት ወይም የጨረታ ግብዣ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ የጨረታው አሸናፊ ተለይቶ ውል እስኪፈረም ድረስ ያለውን የግዥ አፈጻጸም ሂደትን የሚገልጽ ነው፤

ቀ/ "የጨረታ ሰነድ" ማለት ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንዲችሉ በተቋሙ የሚዘጋጅ ዝርዝር የግዥ ፍላጎትን የሚገልጽ ሰነድ ነው፤

በ/ "የመጫረቻ ሰነድ" ማለት ተቋሙ ለግዥው ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መነሻነት ተጫራች በግዥው ለመሳተፍ የሚያቀርበው ሰነድ ነው፤

ተ/ "ተጫራች" ማለት የመጫረቻ ሀሳብ ያቀረበ ሰው ወይም ድርጅት ነው፤

ቸ/ "ጠቅላላ ዋጋ" ማለት ለአንድ ግዥ አፈጻጸም ታክስን ጨምሮ ማናቸውንም ሌሎች ወጪዎችን በማካተት በተቋሙ ለሚፈጸም ግዥ የሚከፈል ዋጋ ነው፤

ኀ/ "ኤጀንሲ ወይም ተቋሙ" ማለት የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ማለት ነው፤

ነ/ "የስራ አመራር ቦርድ ወይም ቦርድ" ማለት በመንግስት ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 203/2003 አንቀጽ 6(1) መሰረት የኤጀንሲውን ስራ በበላይነት ለመምራት እና ለመቆጣጠር የተቋቋመ አካል ነው፤

ኘ/ "ዕቃ" ማለት በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሳሪያ፣ ሸቀጥ፣ ለገበያ የተዘጋጀ ሶፍት ዌር፣ ከሚገዛው ዕቃ ጋር ግንኙነት ያለውን እና ከዕቃዎቹ ዋጋ ያልበለጠ ዋጋ ያለው የተከላ፣ የትራንስፖርት ፣ የጥገናና ሌላ ተመሳሳይ አገልግሎትን ይጨምራል፤

ኦ/ "ዕጩ ተወዳዳሪ" ማለት በተቋሙ ግዥ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም ለመካፈል ያመለከተ ሰው ወይም ድርጅት ነው፤

ከ/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

ወ/ "የኤጀንሲው ገንዘብ" ማለት በኤጀንሲው ስራ አመራር ቦርድ የተመደበ፣ ከውጪ በዕርዳታ(ድጋፍ) የተገኘ ገንዘብ ነው፤

ዐ/ "አቅራቢ" ማለት ለተቋሙ ዕቃ ወይንም አገልግሎት ለማቅረብ ወይም የግንባታ ዘርፍ ስራ ለማከናወን ውል የገባ ሰው ወይም ድርጅት ነው፤

ዘ/ "ልዩ ግዥ" ማለት ተቋሙ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚኖረውን የግዥ ፍላጎት ለማሟላት የሚፈፀም ግዥ ነው፣

ዠ/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

**3. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ዋና መስሪያ ቤት፣ በሪጅኖች እና በተቋሙ ተለይቶ በኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በገደብ በሚሰጥ የግዥ ውክልና መሰረት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚፈጸሙ ግዥዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**4. የመመሪያው ዓላማ**

ግልጽ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ የግዥ አፈጻጸም ስርዓትን በመዘርጋትና የመቆጣጠሪያ ሥልት በመቀየስ የግዥ አፈጻጸሙ ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ለማድረግ ነው።

**5. መርሆዎች**

ማናቸውንም የኤጀንሲውን ግዥ ለማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው እና የግዥ አፈጻጸም ተግባር የሚከተሉትን መርሆዎች መሰረት ማድረግ ይኖርበታል።

ሀ/ በግዥ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፣ ይህም ማለት ቁጠባን፣ የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ፣

ለ/ በዚህ መመሪያ በግልጽ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት፣ በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በግዥ እንዳይሳተፍ አለመከልከል ወይም አድልዎ አለማድረግ፣

ሐ/ የኤጀንሲውን ግዥ አፈጻጸምን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የጡረታ ፈንዱን ዕድገት መደገፍ፣

መ/ ማናቸውም የግዥ ውሳኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልጽ ማድረግ፣

ሠ/ ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ውሳኔዎች እና የሚወሰዱ እርምጃዎች የሚያስከትሉት ተጠያቂነት መኖሩን ማረጋገጥ፣

ረ/ በዚህ መመሪያ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት መሠረት እንደ ሁኔታውና አስፈላጊነቱ የአገሪቱን ኢኮኖሚ የሚደግፉ የአገር ውስጥ አምራቾችን፤ኩባኒያዎችን እና አነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችን ማበረታታት።

## ክፍል ሁለት
## ተግባርና ኃላፊነት

### 6. የዋናው ዳይሬክተር ሥልጣንና ኃላፊነት

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

6.1. በተገቢው የሰው ኃይል የተሟላ የግዥ የስራ ተግባራትን የሚያከናውን የስራ ሂደት ማደራጀት፣

6.2. የግዥ ስራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

6.3. የግዥ ስራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች በዘርፉ በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

6.4. የግዥ ስራን እንዲፈጽም የሚደራጀው የሥራ ሂደት ስራውን በቡድን ለማከናወን የሚያስችል በቂ ስልጣን ያለውና ግልጽ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋለት መሆኑን ማረጋገጥ፣

6.5. የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉና ከ3 (ሦስት) ያላነሱ አባላት ያሉት የተቋሙን ከፍተኛ ግዥዎች መርምሮ የሚያፀድቅ ፦

ሀ/ በተቋሙ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙ፣

ለ/ በተቻለ መጠን ከተለያየ የሙያ ዘርፍ የተውጣጡ እና በተቋሙ ሥራ የተሻለ ዕውቀት እና ልምድ ያላቸው፣

ከ3 (ሦስት) ዓመታት የማይበልጥ የአገልግሎት ዘመን የሚኖረው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ማቋቋም፣

6.6. ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አባላትን የአገልግሎት ዘመን ለአንድ ተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን ማራዘም፣

6.7. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አባላት ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ እና የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች የተሟሉላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

6.8. በግዥ አፅዳቂነት የሚመደቡ ሠራተኞች ለሥራው የሚያውሉት ጊዜ የመደበኛ ሥራቸው አካል ሆኖ በስራ ፕሮግራሞቻቸው እና ውጤት ላይ መመዝገቡን ማረጋገጥ፣

6.9. በግዥ ስራ እና አፅዳቂነት ለተመደቡ ሠራተኞች እና የሥራ ኃላፊዎች ተቋሙ ያወጣውን ይህንን የግዥ አፈጻጸም መመሪያ፣የግዥ ማንዋል፣መደበኛ የጨረታ ሰነዶች፣ መደበኛ የግዥ ሰነዶች እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች(ቅጾች) እንዲደርሷቸው እና የተቋሙን የግዥ ስርዓት በሚገባ እንዲያውቁ የሚያስችል ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣

6.10. ለግዥ ሥራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የሥራ ክፍሉም ሆነ አፅዳቂ ኮሚቴው ሥራቸውን በተገቢው ለመወጣታቸው ክትትል ማድረግ፣ እንደ አስፈላጊነቱም የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

6.11. ውስብስብ ለሆኑ እና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚፈልጉ ግዥዎች ጊዜያዊ ገምጋሚ ኮሚቴ ማቋቋም፣

6.12. የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የኤጀንሲውን የግዥ ዕቅድ መርምሮ ማፅደቅ:-

ሀ/ የግዥ ዕቅዱ ከኤጀንሲው የሥራ ፕሮግራሞች ጋር መጣጣሙን፣

ለ/ ተሰባስበው ሊፈጸሙ የሚችሉ ግዥዎች አንድ ላይ መሰባሰባቸውን፣

ሐ/ ዕቅዱ የኤጀንሲውን የግዥ ፍላጎቶች በሙሉ ያካተተ እና ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ የኮሚቴው ይሁንታ ማግኘቱን፣

6.13. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 27.2 መሰረት በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ መፅደቅ የማያስፈልጋቸውን አነስተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸው ግዥዎችን በሚመለከት:-

ሀ/ በግዥ የስራ ሂደቱ ደረጃ እንዲፀድቁ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

ለ/ ከስራው ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሚኖረው የቡድን መሪ ወይም የሥራ ሂደት ኃላፊ (ዳይሬክተር) እንዲያፀድቅ ውክልና ሊሰጥ ይችላል

ሐ/ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የሚሰጠው ውክልና በገንዘብ መጠን ተገድቦ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ የስራ ኃላፊዎች ሊሰጥ ይችላል፣

6.14. በዚህ መመሪያ አንቀጽ17.14 መሰረት በግዥ አፈጻጸም ሂደት የሚደረጉ የዋጋ ማስተካከያዎችን አግባብነት የማረጋገጥ፣

6.15. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 44 መሰረት እና በኤጀንሲው የተከናወነውን የግዥ አፈጻጸም አስመልክቶ የቀረበ የመረጃ ፍላጎት ጥያቄ በግዥ ሥራ ክፍሉ ተቀባይነት በማጣቱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣

6.16. የግዥ ውል ሰነድ ይፈርማል፣ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ የግዥ ውል የመፈረም ውክልና ሊሰጥ ይችላል፣ በውሉ መሰረትም ግዥው መፈጸሙን ይከታተላል፣

6.17. ከግዥው ውስብስብነት ወይም ኤጀንሲው ካለው የግዥ አቅም በላይ በመሆኑ ምክንያት የኤጀንሲውን ግዥ የሚከተሉትን ተመርኩዞ በሶስተኛ ወገን እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል:-

ሀ/ ከሶስተኛ ወገን የሚገኘው የግዥ አገልግሎት ይህንን መመሪያ ተከትሎ እንዲፈጸም ያደርጋል፣

ለ/ ለኤጀንሲው ግዥ በሚፈፅመው ሦስተኛ ወገን እና በኤጀንሲው መካከል ግልጽ የሆነ የስራ ክፍፍል እንዲኖር ያደርጋል፣

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ሀ እና ለ መሰረት በሦስተኛ ወገን ለሚፈጸሙ ግዥዎች የሚሰጡ ውሳኔዎች በሙሉ በቅድሚያ ቀርበው የተፈቀዱ መሆኑን ያረጋግጣል፣

6.18. በተቋሙ የተከናወኑ ግዥዎችን የሚገልጽ የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት በተቋሙ በሚዘጋጁ ቅጾችና በሚወሰነው መሰረት የመላኪያ ጊዜውን ጠብቆ እንደ አስፈላጊነቱ ለስራ አመራር ቦርድ ወይም ለሚመለከተው አካል መቅረቡን ይቆጣጠራል፣

6.19. ከኤጀንሲው ግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ለአቅራቢዎች የተፈጸሙ ክፍያዎችን በሚመለከት መረጃው ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት መድረሱን ያረጋግጣል፣

6.20. የሚከተሉትን ጨምሮ የተቋሙን የግዥ አፈጻጸም በሚመለከት በኤጀንሲው የውስጥ ኦዲት ወይም የውጪ ኦዲት በሚደረግ የግዥ ኦዲት ወይም ምርመራ ሥራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡-

ሀ/ ለኦዲት ሥራው የሚያስፈልጉ ሰነዶች በሚፈለገው ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ፣

ለ/ ለተመደቡት ኦዲተሮች አገልግሎት የሚሆን የሥራ ቦታ እንዲመቻች ማድረግ፣

ሐ/ ስለተፈጸሙት ግዥዎች አካሄድ ሊያስረዳ የሚችል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ እንዲመደብ ማድረግ፣

6.21. በግዥ ኦዲት ግኝቶች በሚሰጡ አስተያየቶች መሠረት ተገቢ ማስተካከያ የማድረግ እና የተደረጉ ማስተካከያዎችንም ለሚመለከታቸው ማሳወቅ፣

## 7. <u>የግዥ ሥራ ሂደት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የኤጀንሲው የግዥ ሥራ ሂደት በስራ ዝርዝር ከተሰጡት ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል

7.1. የኤጀንሲውን ፍላጎት በማሰባሰብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9.1 በተገለጸው መሰረት የግዥ ዕቅድ ያዘጋጃል፣

7.2. የተቋሙ ግዥን በተሟላ ስነ-ምግባርና ክህሎት ይፈጽማል፣

7.3. ይህንን የግዥ መመሪያ፣ የመደበኛ የጨረታ ሰነድ፣ የአፈጻጸም ቅጾችን እና የግዥ ውሉን መሰረት በማድረግ የተቋሙን ግዥ ይፈጽማል፤

7.4. የሥራ ሂደት ኃላፊው የሚከተሉትን የግዥ ሰነዶች እና መረጃዎች ይይዛል፡፡

ሀ/ የሚገዙትን ዕቃዎች ፤የግንባታ ስራዎች ወይም አገልግሎቶች አጭር መግለጫ

ለ/ የጨረታ ማስታወቂያ፣

ሐ/ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ወይም የዋጋ ማቅረቢያ ያቀረቡ አቅራቢዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ስምና አድራሻ፣

መ/ ለጨረታ ግምገማ የተዘጋጀውን መስፈርት እና ተፈጻሚ የተደረገበትን ሁኔታ፣ የጨረታ ግምገማና የውድድሩን አፈጻጸም እና ከተወዳዳሪዎች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሃሳብና የዋጋ ማቅረቢያ የሚያሳይ አጭር መግለጫ፣

ሠ/ አቤቱታ ቀርቦ ከሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ፣

ረ/ ከግልጽ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ዘዴዎች የተመረጠበትን ምክንያት እና

ሰ/ ሌሎች ተፈላጊና ተያያዥ የግዥ መረጃዎችን(ሰነዶችን)፣

7.5. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 28 ከተፈቀደው በስተቀር ማንኛውም የተቋሙ ግዥ የሚፈጸመው በመንግስት ግዥ ኤጅንሲ ከተመዘገቡና የባንክ ሂሳብ ካላቸው አቅራቢዎች የተፈጸመ መሆኑን ያረጋግጣል፤

7.6. ከጠያቂ የሥራ ሂደት ጋር በመተባበር የጨረታ ሰነድ አዘጋጅቶ ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ያቀርባል፣

7.7. በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ በሚሰጡ አስተያየቶች መሰረት የጨረታ ሰነዶችን ያስተካክላል፣

7.8. የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀበት ቋንቋ በሚታተም እና አገራዊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ጊዜ ያወጣል፣እንደ አስፈላጊነቱ በብሄራዊ የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ጣቢያ ማስታወቂያውን ያስነግራል፣

7.9. በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚፈጸመውን ግዥ ጨምሮ የግዥው የገንዘብ መጠን በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተገለጸው እና ከዚህ በላይ የሆነን ግዥ የጨረታ ማስታወቂያው በጋዜጣ በወጣበት ተመሳሳይ ጊዜ በተቋሙ የመረጃ መረብ (ድረ-ገጽ/ ዌብ ሳይት/ዌብ ፖርታል) ላይ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፣

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ለግንባታ ስራ | ከብር | 20,000,000.00በላይ |
| ለ. ለዕቃ | ከብር | 6,000,000.00 በላይ |
| ሐ. ለምክር አገልግሎት | ከብር | 4,000,000.00 በላይ |
| መ. ለሌሎች አገልግሎቶች | ከብር | 2,000,000.00 በላይ |

7.10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 ከተከለጸው የገንዘብ መጠን በላይ ግዥዎች የጨረታ አሸናፊው ከተመረጠና የግዥ ውል ከተፈረመ በኋላ ባሉት አምስት ቀናት ውስጥ በተቋሙ የመረጃ መረብ (ድረ-ገጽ/ ዌብ ሳይት/ዌብ ፖርታል) በተዘጋጀው ፎርም ላይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሙላት መረጃው ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፣

7.11. የጨረታ ሰነድ ይሸጣል፣ በጨረታ ሰነዱ ላይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ማብራሪያ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፣

7.12. የመጫረቻ ሰነድ መቀበያ ሳጥን ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል፣

7.13. ጨረታ ይከፍታል፣እስከተቻለ ድረስ የግዥ ጠያቂው ክፍል እና የውስጥ ኦዲት ተወካይ በጨረታ አከፋፈት ስነ-ስርዓት ላይ እንዲገኙ ይጋብዛል፣

7.14. በቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶች ዋና ዋና ገጾች ላይ ማህተም እየተደረገ መፈረሙን ያረጋግጣል፣ የጨረታ መክፈቻ ቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ያደርጋል፣

7.15. የጨረታ ማስከበሪያ ይቀበላል፣ እንዲጠበቅ ያደርጋል፣ በጨረታ ሰነዱ በተገለጹት ሁኔታዎች መሰረት የጨረታ ማስከበሪያውን ለኤጀንሲው ገቢ ያደርጋል ወይም ተመላሽ ያደርጋል፣

7.16. የመጫረቻ ሰነዶች ኮፒዎች ጨረታውን እንዲገመግሙ ለተወከሉ ኮሚቴ አባላት መሰጠታቸውን እና ኦርጅናል ሰነዶቹ ለማጣቀሻነት በጥንቃቄ ተነጥለው መያዛቸውን ያረጋግጣል፣

7.17. የመጫረቻ ሰነዶችን በቡድን በመሆን ይገመግማል ወይም እንዲገመግሙ ያደርጋል፣ የግዥው መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 27.2 ላይ ከተጠቀሰው በላይ በመሆኑ ምክንያት የግምግማ ውጤቱ ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ መፅደቅ ያለበት ከሆነ ለኮሚቴው ያቀርባል፣

7.18. የመጫረቻ ሰነድ በግዥ የሥራ ክፍል ሲገመገም መረጃዎች በትክክል መገልበጣቸውን፣ የሂሳብ ስሌት በትክክል መሰራቱን ወይም አንድን ተጫራች ሊጠቅም ወይም ሊጎዳ የሚችል ማንኛውም ተግባር አለመፈጸሙን ያረጋግጣል፣

7.19. የመጫረቻ ሰነድ የግምገማ ውጤትን አስመልክቶ ለተቋሙ ኃላፊ ማብራሪያ ይሰጣል ወይም ማብራሪያ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

7.20. በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ የሚፀድቁ ግዥዎችን በሚመለከት ከኮሚቴው ለሚቀርቡ የማብራሪያ ጥያቄዎች ማብራሪያ ይሰጣል ወይም ማብራሪያ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

7.21. በሦስተኛ ወገን የሚከናወኑ ግዥዎችን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

7.22. በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር በሚሰጠው ውክልና መሰረት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 27.2 ላይ ከተጠቀሱት የገንዘብ ገደቦች በታች የሆኑ ግዥዎችን ያፀድቃል፣

7.23. ለአሸናፊ እና ተሸናፊ ተጫራቾች የጨረታውን ውጤት ያሳውቃል፣

7.24. በውሉ ረቂቅ ላይ ከአቅራቢዎች ጋር ይደራደራል፣ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት ይፈርማል ወይም በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ እንዲፈረም ያደርጋል፣

7.25. ተቋሙ በውል ስምምነቱ መሰረት ግዴታውን መወጣቱን እና የውል መብቱ መከበሩን ያረጋግጣል፣

7.26. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጸሙ ግዥዎች ተሳታፊ የሚሆኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ይመርጣል፣ የዋጋ ማቅረቢያም ይሰበስባል፣

7.27. በተለይ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸሙ ግዥዎችን በሚመለከት በአሸናፊነት የሚመረጡት አቅራቢዎች ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን ያረጋግጣል፣

7.28. የግዥ ሰነዶችን ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ከሚመለከታቸው ሕጋዊ አካላት ማብራሪያ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ ይሰጣል፣

7.29. የተቋሙን የግዥ አፈጻጸም ሂደት አስመልክቶ መረጃ እንዲሰጠው ጥያቄ ለሚያቀርብ አካል የተጠየቀውን መረጃ በተቻለ ፍጥነት ይሰጣል፡፡ ሆኖም

ሀ/ የመረጃው ይፋ መሆን በሕግ የማይፈቀድ፣የሕግ አፈጻጸምን የሚያሰናክል፣የሕዝብን ጥቅም የሚቃረን፣ የተዋዋዮችን ሕጋዊ የንግድ ጥቅም እንዲሁም ቀና ውድድርን የሚጎዳ

ለ/ ከተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሀሳብ ከመመርመር እና ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን

ሐ/ ተጫራቾች ያቀረቡዋቸውን የመወዳደሪያ ሀሳቦች እና የጨረታ ሰነዶች ይዘት የሚገልጹ መረጃዎችን የማይጨምር ሲሆን የሚሰጠው መረጃ ወጪ የሚያስከትል ከሆነ መረጃ ፈላጊው ወጪውን እንዲሸፍን መደረግ ይኖርበታል፡፡

7.30. የግዥ ሥራ ሂደት ኃላፊ በዚህ መመሪያ መሰረት ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ሃላፊነት (ተጠያቂነት) ይወስዳል፡፡

## 8. <u>የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

8.1. በግዥ ሥራ ሂደት የሚዘጋጀው ዓመታዊ ዕቅድ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣

ሀ/ የተለዩት የግዥ ፍላጎት ከተቋሙ ፕሮግራሞች ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን፣

ለ/ እያንዳንዱን ፍላጎት ለሟሟላት ከግዥ የተሻለ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን፣

ሐ/ ዕቅዱ ግዥን በጥቅል ለመፈጸም በሚያስችል መልኩ መዘጋጀቱን፣

መ/ ከተቋሙ ልዩ ባህሪይ አንፃር ሊሟሉ የሚገባቸው ሌሎች ሁኔታዎች መሟላታቸውን፣

8.2. በግዥ የሥራ ሂደት የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላቱን ያረጋግጣል፤

ሀ/ በኤጀንሲው ለየግዥው ዓይነት የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ የተከተለ መሆኑን፣

ለ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በዚህ መመሪያ የተገለጹትን ሁኔታዎች ያሟላ መሆኑን

ሐ/ የመወዳደሪያ መስፈርቶቹ አድሏዊ ያልሆኑ ግልጽ እና ተደራሽ መሆናቸውን፣

መ/ ተገቢ ቅፆችን በዚህ መመሪያ መሰረት እንደ ግዥው ዓይነት ሊገልጹ የሚገባቸውን ሁኔታዎች እና ሌሎችንም መሰረታዊ ጉዳዮች መሟላቱን፣

8.3. የሚከተሉትን የማጣራት ሥራዎች በማከናወን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 27.2 ላይ እንደ ግዥው ዓይነት ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ ግዥዎች በግምገማ ሪፖርቶችን መርምሮ ያፀድቃል፣

ሀ/ ግምገማው በወጣው የጨረታ ሰነድ መሰረት መሰራቱን፣

ለ/ የዚህን መመሪያ፣ የግዥ ማንዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሰነዶችንና ሌሎች ቅጾችን እና መስፈርቶች የጠበቀ መሆኑን፣

ሐ/ በግዥ ውሳኔ ሀሳቡ ላይ ለመድረስ የተከናወኑት ዝርዝር ግምገማዎችና አጠቃላይ የግዥ ሂደቱ ተቋሙ ለሚከፍለው ክፍያ ተመጣጣኙን ለማግኘት የሚያስችሉ መሆኑን ማረጋገጥ፣

8.4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.23 ላይ የተገለጸውን ተግባራዊ ያደርጋል፣

8.5. በቀረበው የግዥ ግምገማ ሪፖርት ላይ የሚሰጥ ማንኛውም ዓይነት የኮሚቴው ውሳኔ ምክንያታዊ መሆን ይኖርበታል፣

8.6. የግዥ አፈጻጸም ውጤታማና በተሻለ ሁኔታ ሊፈጸሙ በሚያስችሉ ዘዴዎች ላይ የተቋሙን የበላይ ኃላፊ ያማክራል፣

8.7. በኮሚቴው ስለተከናወኑ የግዥ ተግባራት፣ ስላጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች የሚገልጽ ሪፖርት ለተቋሙ ኃላፊ ያቀርባል፣

8.8. በተቋሙ የግዥ አፈጻጸም ሂደት ውስጥ በኮሚቴው ስለተሰጡ ውሳኔዎች በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወይም በሌላ ስልጣን ባለው አካል ሲጠየቅ ማብራሪያ ይሰጣል፣

8.9. የአፅዳቂ ኮሚቴው ሰብሳቢ እና ጸሃፊ የሚኖራቸው ዝርዝር የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት እንዲሁም ስነ-ስርዓት በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር 2 ላይ ተመልክቷል።

8.10. የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አባላት በዚህ መመሪያ መሰረት ለሚወስዷቸው እርምጃዎች ኃላፊነት (ተጠያቂነት) ይወስዳሉ።

## ክፍል ሶስት
## የግዥ ዕቅድ

### 9. የግዥ ዕቅድ ስለማዘጋጀት

9.1. ኤጀንሲው የታቀዱ የሥራ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚስፈልገውን ግዥ በወቅቱ ለመፈጸም የሚያስችል በመርሐ ግብር የተደገፈ የግዥ ዕቅድ ያዘጋጃል፤

9.2. የሚዘጋጀው የግዥ ዕቅድ የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችል መሆን አለበት፤

ሀ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ላይ የተገለጹትን የግዥ መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣

ለ/ የተቋሙን የስራ ፕሮግራም ለማሳካት፣

ሐ/ የቁጥቁጥ ግዥን በመከላከል የተቋሙን አሰራር ጊዜና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ፣

መ/ በግዥ አፈጻጸም ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን በቅድሚያ በመገንዘብ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ፣

## 10. የግዥ ፍላጎትን መለየት፣ ማሰባሰብና ማደራጀት

10.1. ኤጀንሲው የግዥ ፍላጎት በሚያዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉትን ማገናዘብ ይኖርበታል፦

ሀ/ ፍላጎቱ በኤጀንሲው ውስጥ ባለ እና ጥቅም ላይ ባልዋለ ሌላ ሀብት ወይም ንብረት ሊሟላ የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ/ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ ምርት ወይንም አገልግሎት ሊሟላ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ/ የግዥ ፍላጎቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ እሴቶችን ያካተተና ኤጀንሲውን ለአላስፈላጊ ወጪ የማይዳርግ መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ/ በተለይ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ ታስበው የሚከናወኑ ግዥዎች በሚሆኑበት ጊዜ የግዥ ፍላጎቱ ወደፊት የሚፈጠርን የፍላጎት ዕድገት ያገናዘበ መሆኑን፣

ሠ/ አስገዳጅ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ መደበኛ አቅርቦት ወይም እስታንዳርድ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ረ/ የግዥ ፍላጎቱ የማህበረሰቡን የአካባቢ ደህንነት እና ጥበቃ የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ፣

10.2. በተቋሙ ስር ከሚገኙ ሥራ ሂደቶች እና ጽህፈት ቤቶች የግዥ ፍላጎት በማሰባሰብ ዓመታዊ የግዥ ፍላጎታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን መፈጸም አለበት፡፡

ሀ/ በተቋሙ ስር የሚገኙ ተጠቃሚዎች ዓመታዊ የግዥ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፣

ለ/ ከተጠቃሚዎች የቀረበውን ፍላጎት በግዥ ዓይነት ፣ ብዛት፣ የጥራት ደረጃ እና በሚገኙበት ቦታ መለየት፣

ሐ/ ተቋሙ ልዩ ትኩረትና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራና አገልግሎት መለየት፣

መ/ የቀረበው ፍላጎት በቂ አቅራቢ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ማጣራት፣

ሠ/ በተቋሙ በተደረገ ጥናት ወይም ከሌሎች ምንጮች በተገኘ የገበያ መረጃ ለየግዥው የሚያስፈልገውን የዋጋ ግምት ማወቅ፣

ረ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጠቃሚዎቹ መዘጋጀቱን ወይም ወደፊት የሚዘጋጅ መሆኑን ማረጋገጥ፣

10.3. ተቋሙ ከተጠቃሚዎች የተሰባሰበውን ፍላጎት ፣ ከገበያ ጥናት የሚገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ እና የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የግዥ ፍላጎታቸውን ማደራጀት አለበት፡፡

ሀ/ በተቋሙ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ግዥ መፈጸም የሚችለው ለምክር አገልግሎት ወይም ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ የምክር አገልግሎቱ ዋጋ ከሃምሳ በመቶ (50%) በላይ ለሚሆን ግዥ መሆኑን የማረጋገጥ፣

ለ/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቃ፣ የአገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ግዥ በአንድ ላይ የሚፈጸምበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከሃምሳ በመቶ (50%) በላይ ድርሻ ያለውን የግዥ ዓይነት መሰረት በማድረግ መፈጸም፣

ሐ/ እስከተቻለ ድረስ ተቀራራቢ እና ተመሳሳይ ፍላጎቶችን በአንድ ላይ ማሰባሰብ፣

መ/ በአንድ ላይ ለሚፈጸሙ ግዥዎች በቂ አቅራቢ በገበያ ላይ መኖሩን ወይም ግዥው በሚኖረው የአቅራቢ ዓይነት በተለያየ ምድብ በመከፋፈል በቂ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሠ/ ግዥውን ለአፈጻጸም አመቺና አደናቃፊ ሁኔታዎች የሌሉበት መሆኑን ማረጋገጥ፣

ረ/ እስከተቻለ ድረስ የአገር ውስጥ አምራቾች የመወዳደር ዕድልን በሚያሰፋ መልኩ ግዥው እንዲደራጅ ማድረግ፡፡

## 11. <u>የግዥ ዘዴን መምረጥ</u>

11.1. ተቋሙ በግዥ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት በዚህ መመሪያ ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች አግባብነት ያለውን በመምረጥ በዕቅዱ ላይ ማመልከት አለበት፣

11.2. ተቋሙ የግዥ ዕቅዱን በሚያዘጋጅበት ወቅት የሚታወቁ የግዥ ፍላጎቶች ሁሉ በግዥ ዕቅድ ውስጥ መካተታቸውን እና ለእያንዳንዱም ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ መመረጡን መረጋገጥ አለበት፡፡

## 12. <u>የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን መወሰን</u>

12.1. የተቋሙን የግዥ ዕቅድ ማዘጋጃ በተቋሙ የሚዘጋጀውን ቅጽ በመጠቀም በግዥ ሂደቱ ውስጥ ዋና ዋና ተግባራት የሚከናወኑበትን ጊዜ መወሰን አለባቸው፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን እና እንደሚፈጸመው የግዥ ዓይነት ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይገባል፣

ሀ/ ግዥው በሚከናወንበት ጊዜ ከተቋሙ የሥራ ፕሮግራም ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣

ለ/ በገበያ ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚኖርበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን፣

ሐ/ በግዥ መመሪያው አባሪ 3 ላይ በተገለጸው መሰረት ዝቅተኛ የጨረታ መቆያ ጊዜን የጠበቀና እስከተቻለ ድረስ ሰፊ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጃ ተጨማሪ ጊዜ የሰጠ መሆኑን፣

መ/ በተለይ ውስብስብ ለሆኑ እና ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ላላቸው ግዥዎች በቂ የሰነድ ማዘጋጃ፣ መገምገሚያ እና ማፅደቂያ ጊዜ የተሰጣቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፣

12.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለግዥው ዓይነት የሚወሰነው ጊዜ የግዥ አፈጻጸም ዋና ዋና ተግባራትን ለማከናወን ከሚያስፈልገው ጊዜ የረዘመ እንዳይሆን ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

## 13. የግዥ ዕቅድ ይዘት

13.1. ተቋሙ በዚህ መመሪያ ክፍል ሶስት ላይ የሰፈሩትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ እና ተቋሙ ለዚሁ ባዘጋጀውና በአባሪ 1 ላይ በተመለከተው የግዥ ዕቅድ ማዘጋጃ ቅፅ በመታገዝ የግዥ ዕቅዳቸውን ማዘጋጀት አለበት። በዚህ መሠረት የሚዘጋጀው ዕቅድ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ/ የግዥውን ምድብ፣ ቁጥር፣

ለ/ የግዥውን መግለጫ፣

ሐ/ የግዥውን መጠን፣

መ/ የግዥው ዝርዝር አፈጻጸም የሚከተላቸውን አሠራሮች፣

ሠ/ ግዥውን ለማጠናቀቅ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትና የሚፈጸሙበትን ጊዜ፣

ረ/ ለግዥ የሚያስፈልገውን በጀት መጠንና የፋይናንስ ምንጭ፣

ሰ/ ለግዥው ተስማሚ የሆነ የውል ዓይነት፣

ሸ/ በግዥው አፈጻጸም ሂደቱ የሚሳተፉ ዋና ዋና አካላትን የተሳትፎ ሁኔታ፣

ቀ/ ሌሎች እንደ ተቋሙ ባህርይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን፣

13.2. ተቋሙ ለግዥ ዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት የተጠቀመባቸውን ዋና ዋና መረጃዎች ምንጭ እና ሌሎች የግዥ ዕቅዱን ለተጠቃሚው የበለጠ ግልጽ ያደርጋሉ ብሎ የሚያስባቸውን መረጃዎች ከግዥ ዕቅድ ቅፁ ጋር በአባሪነት ማያያዝ ይኖርበታል።

## 14. የግዥ ዕቅድ የሚፀድቅበት እና የሚሻሻልበት ሁኔታ

14.1. በግዥ ሥራ ሂደቶች የተዘጋጁትን ዓመታዊ የኤጀንሲውን የግዥ ዕቅድ በተቋሙ ለተቋቋመው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አቅርበው አስተያየት ከተቀበሉ በኋላ ዕቅዱን ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር አቅርበው ማፀደቅ አለባቸው፣

14.2. የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር የኤጀንሲው ግዥ አፈጻጸም ሂደት በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሰረት መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት አፈጻጸሙን መከታተል አለበት፣

14.3. በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር የፀደቀው ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ቅጅ በየዓመቱ እስከ ሐምሌ 30 ቀን ድረስ ለሚመለከታቸው የስራ ሂደቶች እና ሪጅንና ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች መላክ አለበት፣

14.4. በተቋሙ የተዘጋጀው ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ተቀባይነት ካገኘ፣ ተቋሙ የግዥ አፈጻጸሙን መከፋፈል ወይም በዕቅዱ ከተገለጸው አሰራር ውጭ መፈጸም አይችሉም፣

14.5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እና በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ሲታመንበት በማናቸውም ጊዜ ዕቅዳቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ፣

14.6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተገለጸው መሰረት የተሻሻለው የግዥ ዕቅድ የመጀመሪያው ዕቅድ ለተላከላቸው በተቋሙ ለሚገኙ የሚመለከታቸው የሥራ ሂደቶች፣የሪጅንና ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መላክ አለበት።

## 15. ዓመታዊ የግዥ ዕቅድን ይፋ ማድረግ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ከስራ ሂደቶች እና ጽሕፈት ቤቶች የተላከለትን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በማሰባሰብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ 9 ከተገለጸው የገንዘብ መጠን በላይ የሆነን የግዥ ዕቅድ እንደ አስፈላጊነቱ በግዥው አይነት በመለየት ይፋ ያደርጋል፣ እንዲሁም የተጠቀሰውን መረጃ በተቋሙ ድረ-ገጽ/ዌብ ፖርታል/ መረጃውን ያወጣል፣

# ክፍል አራት

# የግዥ ዘዴዎችና አፈጻጸማቸው

## 16. የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች

16.1. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚከተሉት የግዥ ዘዴዎች በተቋሙ በስራ ላይ ይውላሉ፡-

ሀ/ ግልጽ ጨረታ፣

ለ/ ውስን ጨረታ፣

ሐ/ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ፣

መ/ ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ፣

ሠ/ በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ የሚፈጸም ግዥ፣

ረ/ በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈጸም ግዥ፣

16.2. በዚህ መመሪያ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ተቋሙ የሚፈጽማቸው ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈጸም አለባቸው፣

16.3. ተቋሙ ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችለው በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፣

16.4. ተቋሙ ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ከሆነ በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታ የሚገልጽ ሰነድ መያዝ ይኖርበታል፣

16.5. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተዘረጉ የግዥ ስርዓቶችን ለመሸሽ በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎች መከፋፈል የለባቸውም።

## 17. የብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ግዥ አፈጻጸም

ተቋሙ በግልጽ ጨረታ ዘዴ ግዥን ለመፈጸም በተቋሙ የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መጠቀም እና በዚህ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩትን አፈጻጸሞች መከተል አለበት።

### 17.1. ቅድመ- ሁኔታዎች

ተቋሙ በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ዘዴ ግዥ ለመፈጸም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

17.1.1. የሚፈለገው ግዥ በአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ሊሟላ መቻሉንና ግዥው በዚህ መመሪያ አንቀጽ18 ንዑስ አንቀጽ 2 ለዓለም አቀፍ ጨረታ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በታች መሆኑን፣ ወይም

17.1.2. የግዥው መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ከተገለጸው የገንዘብ ገደብ በላይ ቢሆንም ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ብቻ የሚገኝ መሆኑን፣

### 17.2. የጨረታ ጥሪ

17.2.1. የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያው በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ለማድረግ የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀበት ቋንቋና አገራዊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ጊዜ ታትሞ መውጣት አለበት።

17.2.2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 17.2.1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ በመረጠው ጊዜና መጠን በዚህ መመሪያ ከተገለጸው መንገድና እና በብሔራዊ የሬድዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ ስልቶች በመጠቀም ጥሪ ሊያስተላልፍ ይችላል።

17.2.3. የጨረታው ጥሪ ማስታወቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ሊይዝ ይገባል፡-

17.2.3.1. የተቋሙን ሙሉ ስምና አድራሻ፣

17.2.3.2. የሚቀርበውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ዓይነት፣ ከተቻለ ብዛት እና ርክክቡ የሚፈጸምበትን ቦታ ወይም የግንባታ ስራውን ዓይነት እና የሚከናወንበትን ቦታ ወይም የምክር አገልግሎቱን ዓይነት እና የሚካሄድበትን ቦታ፣

17.2.3.3. በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያሟሉ የሚገባው መሥፈርት፣

17.2.3.4. የጨረታው ሰነድ የሚገኝበትን ቦታ፣

17.2.3.5. የጨረታው ማስከበሪያ ዋስትና መጠን፣

17.2.3.6. የጨረታውን ሰነድ ለመውሰድ የሚከፈልን ዋጋ፣ እና የአከፋፈሉ ዘዴ፣

17.2.3.7. የመጫረቻ ሠነዱ የመጨረሻ ማስረከቢያ እና የሚከፈትበትን ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት፣

17.2.3.8. ተቋሙ ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ ለመሰረዝ መብት ያለው መሆኑን፣ እና

17.2.3.9. ለተጫራቾች መገለጽ እንዳለባቸው በተቋሙ የታመነባቸው ሌሎች ጉዳዮች፣

17.2.4. የጨረታውን ጥሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.13 ላይ በተገለጸው መሰረት ጨረታው በሚካሔድበት ቋንቋ መዘጋጀት ይኖርበታል ::

## 17.3. <u>የጨረታ ሰነድ</u>

ተቋሙ፣

17.3.1. የሚዘጋጁት የጨረታ ሰነድ በተቋሙ የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መጠቀማቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚዘጋጁት የጨረታ ሰነዶች

ሀ/ የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀትና ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን (Instructions)

ለ/ የመጫረቻ ሰነዱን ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን፣ የመጫራቻ ሰነዱ የሚላክበት አድራሻ፣ ጨረታው የሚከፈትበት ቀን ሰዓትና ቦታ እንዲሁም የተጫራቾች ወኪሎች በጨረታው መክፈቻ ስነስርዓት ላይ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ

ሐ/ የጨረታ መወዳሪያ ሃሳብ ማቅረቢያ ቅጾች እንዲሁም አግባብነት እስካለው ድረስ የጨረታ መስከበሪያ ቅጾች፣

መ/ ከዋናው የመጫረቻ ሰነድ ጋር መቅረብ ያለባቸውን ተጨማሪ ኮፒዎች

ሠ/ የውሉን አጠቃላይ እና ልዩ ሁኔታዎች

ረ/ እንደ አግባብነቱ ዕቃውን ለማቅረብ ወይም ሥራውን ለማጠናቀቅ ይወስዳል ተብሎ የሚገመተውን የጊዜ ገደብ ጨምሮ ተፈላጊውን የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር

ሰ/ ተጫራቹ በጨረታው ለመሳተፍ ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያቀርባቸውን መረጃዎች ዓይነት እንዲሁም የፋይናንስ አቋሙን እና ህጋዊነቱን ለማረጋገጥ ማቅረብ ያለበትን መረጃ

ሸ/ ጨረታው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ

ቀ/ ጨረታውን ለመገምገም እና በጨረታው አሸናፊ የሆነውን ለማስታወቅ የሚያገለግሉ መስፈርቶችንና ለእያንዳንዱ መስፈርት የተሰጠውን ነጥብ

በ/ ተቋሙ የጨረታው አሸናፊ ይፋ ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብት ያለው መሆኑን፣ እና

ተ/ በዚህ መመሪያ በልዩ ሁኔታ ለተፈቀዱ ግዥዎች በውል አፈጻጸም ወቅት የዋጋ ማስተካከያ ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ እና የዋጋ ማስተካከያው የሚደረግበትን ሁኔታ እና አፈጻጸሙን ያካተተ መሆኑን መረጋገጥ አለበት

17.3.2. የጨረታ ሰነድ በሚዘጋጅበት ወቅት በተቋሙ ከተዘጋጀው መደበኛ የጨረታ ሰነድ ውስጥ በተጫራቾች መመሪያ እና በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ምንም ለውጥ ሳይደረግ በሌሎች የሰነዱ ክፍሎች ላይ እንደግዥው አይነትና ባህርይ ማሻሻያ በማድረግ ሰነዱ መዘጋጀት አለበት።

17.3.3. የጨረታ ሠነድ በዋናነት በግዥ የሥራ ክፍል ወይም ቡድን የሚዘጋጅ ሲሆን፣በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው ውሳኔ መሰረት ለመፈጸም ግዥ የሚዘጋጅ ማንኛውም የጨረታ ሰነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኮሚቴው ተቀባይነት ማግኙቱን መረጋገጥ አለበት።

17.4. <u>የተጫራቾች መመሪያ</u>

17.4.1. ተቋሙ የመደበኛ የጨረታ ሰነዶች አንዱ ክፍል ሆኖ የተዘጋጀውን የተጫራቾች መመሪያ እና የዚሁ አካል የሆነውን የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የጨረታው ሰነድ ክፍል አድርጎ ለተጫራቾች መስጠት አለበት።

17.4.2. በተቋሙ የሚዘጋጀው የተጨራቾች መመሪያ የሚከተሉትን ያካተተ መሆኑን መረጋገጥ አለበት፡-

ሀ/ የሚገዛውን ዕቃ ወይም የግንባታ ስራ፣ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች አጠቃላይ መግለጫ፣ የተቋሙ ሙሉ ስምና አድራሻ እንዲሁም የግዥውን የበጀት ምንጭ፣

ለ/ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ስለሚያሟሏቸው መስፈርቶች የሚገልፅ ሆኖ የገንዘቡ መጠን በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ከወጣው ጨረታ ውስጥ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ.ህ ብር) እና ከዚህ በላይ ዋጋ በማቅረብ በጨረታው የሚሳተፍ ማንኛውም የአገር ውስጥ ተጫራች በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ እንዳለበት እንዲሁም የውጭ አገር ተጫራቾች በሚሆኑበት ጊዜ እንደ አግባብነቱ በተቋቋሙበት አገር የተሰጣቸውን የኩባንያ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ማቅረብ እንዳለባቸው መጠቀሱን፣

ሐ/ በጨረታ ሰነዱ ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች አስመልክቶ ማብራሪያ የሚጠየቅበትን አድራሻ፣ ጊዜ እና የማብራሪያ ጥያቄው በጽሑፍ መቅረብ እንደሚገባው የሚያመለክት መግለጫ፣

መ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ሰነድ ይዘት ምን መሆን እንዳለበት፣ በምን ቋንቋ እንደሚዘጋጅ፣በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተገለጹ እና በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች አይነት እና ብዛት፣

ሠ/ ተጫራቹ የማጭበርበር ድርጊት እና ሙስናን በሚመለከት፣ በኢትዮጵያ ሕጎች የተደነገገውን የሚያከብር መሆኑን በማረጋገጥ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን ሙስና ላለመፈጸም ቃል የሚገባበትን ቅፅ እና ሌሎች በተጫራቹ ተሞልተው እንዲቀርቡ የሚፈለጉ ቅፆችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ እንዳለበት፣

ረ/ የጨረታውን አካሄድ ለማዛባት የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታው ውጪ እንደሚሆኑ፣ለወደፊቱም በተቋሙ ግዥ እንዳይሳተፉ እንደሚደረግ እና ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደሚወረስ የሚያመለክት መግለጫ፣

ሰ/ የዕቃዎች ናሙናዎች በተጫራቾች እንዲቀርቡ የሚያስፈልጉ ከሆነ ተፈላጊዎቹ ናሙናዎች የሚቀርቡበትንና እንደ አስፈላጊነቱ በተጫራቾች የሚታዩበትን ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም እነዚህ ናሙናዎች በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚመለሱ ወይም ሊመለሱ የማይችሉ መሆናቸውን፣

ሸ/ የጨረታ ሳጥኑ የሚገኝበትን ቦታ እና ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሰነድ ተቀባይነት እንደማይኖረው የሚገልጽ መግለጫ፣

ቀ/ ጨረታውን ለመገምገም በሥራ ላይ የሚውሉትን ዘዴዎች፣ ለዚሁ ግምገማ የሚያገለግሉትን መስፈርቶች እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን የነጥብ ድርሻ፣ እንዲሁም ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በግምገማው እኩል ቢሆኑ አሸናፊውን ተጫራች ለመለየት የመወዳደሪያ ሐሳብ የሚቀርብበት ሁኔታና መስፈርቶች፣

በ/ በውሉ አፈጻጸም ወቅት የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ መቻል አለመቻሉን እና የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚፈቀድ ከሆነ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ሁኔታ፣

ተ/ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ፣ የውል አፈጻጸም ዋስትና መጠን እና ዓይነት እንዲሁም እነዚህ ዋስትናዎች ፀንተው የሚቆዩበትን ጊዜ፣

ቸ/ የመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ ጊዜ የሚያበቃበትን እና ጨረታው የሚከፈትበትን ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት፣

ነ/ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲሁም የርክክቡን ቦታና ጊዜ፣

ኘ/ ለአገር ውስጥ ምርትና ኩባንያዎች የተፈቀደውን ልዩ አስተያየት ዝርዝር አፈጻጸም የሚያመለክት መግለጫ፣

አ/ ጨረታው በአንድ ወይም በሁለት ኢንቨሎፕ የሚቀርብ ስለመሆኑ፣ ስለኤንቨሎፖች አስተሻሸግ፣ አንድ ወጥ የሆኑ ዋናና ቅጂ ሰነዶች መቅረብ እንዳለባቸው፣የቅጂዎችን ብዛት፣ሠነዶች ሥልጣን ባለው አካል የተፈረመባቸው ሊሆኑ እንደሚገባ እና ማህተም እንደሚያስፈልጋቸው፣ እንዲሁም (ወቅታዊ የግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት፣ የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና ሌሎች መ/ቤቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸው ደጋፊ ሰነዶች) ስለሚቀርቡበት ሁኔታ፣

ከ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.26 በተገለጸው መሰረት የቅድሚያ ክፍያ የሚሰጥ ከሆነ፣ የቅድሚያ ክፍያውን መጠን እና ተቀባይነት ያለውን የዋስትና ዓይነት እና

ወ/ ተጫራቾች በጨረታው አፈጻጸም ሂደት ቅሬታ ካላቸው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 46 እና48 መሰረት አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳላቸውና አቤቱታው የሚቀርብበትን ቦታ፣

ዘ/ ተቋሙ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከመፈረሙ በፊት በጨረታ ሰነዱ ከተገለጸው የአቅርቦት መጠን ላይ መጨመር ወይም መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው ውድድሩ የተገኘው ዋጋ ሳይቀየር እስከ 20% (ሃያ በመቶ) መጨመር ወይም መቀነስ እንደሚችል፣

17.4.3. በመደበኛ ጨረታ ሠነድ የተጫራቾች መመሪያ ይዘት ላይ ምንም ዓይነት ማሻሻያ ማድረግ አይቻልም፡፡ በተጫራቾች መመሪያ ላይ የሚደረጉት ለውጦች የሚመለከቱት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ ነው፡፡

17.5. <u>የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ</u>

ሀ/ ስለ ግዥው ምንነት ትክክለኛ እና የተሟላ መግለጫ እንዲኖር እንዲሁም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሃዊና ግልጽ በሆነ አሰራር መወዳደር የሚችሉበት ሁኔታ ለማመቻቸት የሚገዙ ዕቃዎች፣ የግንባታ ስራዎች ወይም አገልግሎቶች ባህሪ የሚያሳይ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መዘጋጀት አለበት

ለ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው ሊገዛ የሚፈለገው ዕቃ ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ተገቢ ጥንቃቄ እንዳስፈላጊነቱ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን ፣ ምልክቱን ወይም የአመራረቱን ሂደትና ዘዴ እንዲሁም ተፈላጊ የሆነውን ባህሪ የሚያሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበትን ስርዓት የሚገልጽ መሆን አለበት

ሐ/ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ እንደግዥው ዓይነት ጠቀሜታን፣አሠራርን፣ የቴክኒክ ወይም የዲዛይን ባህርይን መሰረት በማድረግ ውድድርን እንዳይገድብ ተደርጎ መዘጋጀት አለበት፡፡

መ/ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የውሉ አንድ ክፍል በመሆን የአቅርቦቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ሠ/ የሚፈለገው ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት ፣ የግንባታ ሥራ ወይም አገልግሎት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ግዥው እንዲፈጸምለት በሚፈልገው ክፍል ወይም ስለሚፈጸመው ግዥ በቂ ዕውቀት ባላቸው የተቋሙ ባለሙያዎች መዘጋጀት አለበት፡፡ ከፍተኛ ወጪ በሚጠይቁ እና ውስብስብ በሆኑ ግዥዎች የፍላጎት መግለጫ አዘገጃጀት ላይ ከኤጀንሲው ውጪ ያሉ ባለሙዎችን ድጋፍ ሊጠይቁ ወይም አማካሪ ቀጥረው ሊሰሩ ይችላሉ፣

ረ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጪ ... ማመልከት የለበትም፡፡ ሆኖም ፍላጎትን በትክክል ሊገልጽ የሚችል

መግለጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ግዥው ለተለየ ፕላንት ወይም መሳሪያ የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን የሚመለከት ሲሆን ወይም የተፈለጉትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ማቅረብ የሚችል አንድ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ የአምራቹን ወይም የአገልግሎት ሰጪውን ስም በመጥቀስ "ወይም ተመሳሳይ" የሚል ሐረግ እንዲታከል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሰ/ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የተቋሙን የአሁን ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችል ፍላጎትን ለማርካት የሚያስችሉ የጠቀሜታ እሴቶችን ለመግለጽ የሚያስችል እና ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ እሴቶችን የማያካትት መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

ሸ/ የተቋሙ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን ወይም እንደግዥው ዓይነት አግባብነት ያላቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን ደረጃዎች በዝርዝሩ ውስጥ ሊያካትት ይችላል፡፡

ቀ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የተሟላና ትክክለኛ የመጫረቻ ሠነድ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል መሆን አለበት፡፡

በ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው እስከተቻለ ድረስ በዲዛይን ወይም ባህሪያን በመዘርዘር ላይ ሳይሆን በጠቀሜታ ላይ፣ አገራዊ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ደረጃውን ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ደረጃዎች ወይም የግንባታ ኮዶች መሰረት ያደረገ፣ ሰፊ ውድድር የሚጋብዝ እና ውድድርን ሊገድቡ የሚችሉ መግለጫዎች ያልተካተቱበት ሆነው መዘጋጀት አለበት፡፡

ተ/ ፍላጎትን በትክክል ለመግለጽ አስቸጋሪ ካልሆነ ወይም ሌላ ዘዴ ካልታጣ በስተቀር የቴክኒክ መግለጫ የተለየ የንግድ ምልክት ወይም ስም ፓተንት ዲዛይን ወይም የተወሰነ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ የሚገልጽ መሆን የለበትም፡፡ አስገዳጅ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ "ወይም ተመሳሳዩን" የሚል ሀረግ በዕቃ እና አገልግሎት ዝርዝር ውስጥ መካተት ይኖርበታል፡፡

17.6. <u>የጨረታ ቅጽና የዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ</u>

ሀ/ ተቋሙ ለጨረታ በሚያዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ውስጥ በተቋሙ የተዘጋጀውን ወይም እንደግዥው ባህርይ ኤጀንሲው ያዘጋጀውን በተጫራቾች ሊሞላ የሚገባውን የጨረታ ቅጽ ፣ ዋጋና ተያያዥ ጉዳዮችን ማቅረቢያ ቅጽ ወይም ሠንጠረዥ ና በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ውስጥ መካተታቸው ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመንባቸው ሌሎች ቅፆችን ማካተት አለባቸው፡፡

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" መሰረት በተቋሙ የሚዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ እንደ አስፈላጊነቱ ዋጋን ፣ ታክስን እና ሌሎችን ከዋጋ አቀራረብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን

በግልጽ ለማመልከት የሚያስችል እንዲሁም የጨረታ ግምገማን ግልጽና ቀልጣፋ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት፡፡

ሐ/ የሚዘጋጀው የጨረታ ቅጽ በተቻለ መጠን ዕጩ ተወዳዳሪው ግልጽ የሆነ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያቀርብ የሚያስችል፣ የጨረታ አካሄዱን መረዳቱን የሚያረጋግጥ፣ ጨረታውን የሚያደናቅፉ ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ የመከላከልና ተጫራቹ ላቀረበው የመወዳደሪያ ሐሳብ ሙሉ ኃላፊነት እንዲወስድ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል፡፡

17.7. <u>አጠቃላይና ልዩ የውል ሁኔታዎች</u>

17.7.1. ተቋሙ የመደበኛ ሰነድ ክፍል ሆነው የተዘጋጁትን የአጠቃላይ እና የልዩ ውል ሰነድ ቅጂዎች የጨረታው ሰነድ ክፍል አድርጎ ለተጫራቾች መስጠት አለበት፡፡

17.7.2.በመደበኛ ጨረታ ሰነዱ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ማሻሻያ ሊደረግባቸው አይችልም፡፡ ልዩ የውል ሁኔታውን ግን እንደሚፈጸሙ ግዥ ባህርይና ዓይነት አጠቃላይ የውል ዐሁኔታዎች ላይ የሰፈሩትን አንቀጾች በማጣቀስ ማሻሻል ይቻላል፡፡

17.7.3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 17.7.1 እና 17.7.2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተቋሙ የሚዘጋጁት ልዩ የውል ሁኔታ እንደግዥው ዓይነት ሊለያይ ቢችልም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡-

ሀ/ የተጫራቾችና የተቋሙ ግዴታና ኃላፊነትን በግልጽ ያመላከተና በተቋሙ ላይ የሚጣሉ ግዴታዎች ህጋዊ መሰረት ያላቸውና ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ለ/ እንደአስፈላጊነቱ የውሉ አፈጻጸም የሚከተላቸውን ዋና ዋና ሂደቶች፣ የማስረከቢያ ጊዜ፣ አስተሻሸግ፣ የማጓጓዝ ኃላፊነት፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈጻጸም፣ የርክክብ እና የፍተሻ ሥነ-ሥርዓት፣ ዋስትና እና የመሳሰሉትን አተገባበር በግልጽ ያስቀመጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

17.8. <u>የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት አዘገጃጀት</u>

17.8.1. የተቋሙ የመጫረቻ ሰነድ የሚገመገምበትን መስፈርት በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ የብቃትና ግምገማ መሥፈርቶች ክፍል ላይ በግልጽ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

17.8.2. የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት እንደ ግዥው ዓይነት የሚለያይ ቢሆንም ከሚከተሉት ሁለት መሰረታዊ የመምረጫ ዘዴዎች በአንዱ ተፈጻሚ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ/ ለግዥው ተቀባይነት ያለውን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት በመወሰን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛውን ካሟሉት ተጫራቾች መካከል አነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች መምረጥ ፣ ወይም

ለ/ ግዥው የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴት ሊወስኑ የሚችሉ መስፈርቶችን እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን አንፃራዊ ክብደት በግልፅ

በጨረታ ሰነዱ ላይ በማሳየትና በነዚህ መስፈርቶች ላይ የተመሠረተ ግምገማ በማካሄድ በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን መምረጥ፣

17.8.3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 17.8.2.ለ በተገለጸው መንገድ ግምገማ ለማካሄድ የሚመረጥ መስፈርት ግዥው ማስገኘት የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም እንዲያስገኝ ከማድረግ አንጻር በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ ሊገለጽ የሚችል ሆኖ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ/ የሚገዛው መደበኛ ወይም ደረጃው የታወቀ አቅርቦት በሚሆንበት ጊዜ ለተቋሙ ጠቃሚ የሆነ እና በተጫራቾች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የሚችል የተለየ እሴት ሊቀርብበት የሚችል መሆን አለመሆኑን፣ ወይም

ለ/ ተቋሙ ካስቀመጠው ዝቅተኛ መስፈርት በተጨማሪነት የሚቀርብ እሴት ተጨማሪ ፋይዳ ማስገኘት አለማስገኘቱን ወይም ተጨማሪው እሴት ለተቋሙ የሚሰጠውን ጥቅም ዝቅተኛነትና ከፍተኛነት፣

ሐ/ የሚገዛው ዕቃ ደረጃ ያልወጣለትና ተጨማሪ ፋይዳ ከመፍጠር አንጻር ስፔሲፊኬሽኑን በተለያየ ደረጃ ሊያሟሉ የሚችሉ ተቀራረቢ ዕቃዎች መኖር አለመኖራቸውን፣

መ/ ዕቃው ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሆኖ የአቅርቦቱ ምንጭ በመለያየቱ ምክንያት የተለያ የመጠቀሚያ፣ የመጠበቂያና የመያዣ እንዲሁም የማስወገጃ ወጪ የሚፈልግ መሆን አለመሆኑን፣

17.8.4. ተቋሙ ተጫራቾች ያቀረቡትን ሠነድ በአንቀጽ 17.8.2.ለ. በተገለጹት መስፈርቶች መሰረት በመገምገም አሸናፊ የሚሆነውን ተጫራች ከለየ በኃላ የአሸናፊው ተጫራች ወቅታዊ የብቃት ሁኔታ በድሕረ ግምገማ መረጋገጥ አለበት ብሎ ሲያምን ይህንኑና ለድሕረ ግምገማ ዓላማ የሚጠቀምበትን መስፈርት በቅድሚያ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

17.8.5. በአንቀጽ 17.8.3 መሰረት ለማወዳደሪያነት የሚመረጡት መስፈርቶች ዕቃው ወይም አገልግሎቱ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ለመወሰን አስተዋፅኦ የሚኖራቸው መሆኑን ማረጋገጥና የግዥውን ጠቀሜታ ለመወሰን ባላቸው አስተዋፅኦ ደረጃ መሰረት አንፃራዊ ክብደት እንዲሰጣቸው መደረግ ይኖርበታል፡፡

17.8.6. ለአገልግሎት ግዥ አፈጻጸም በሥራ ላይ የሚውለው የግምገማ ዘዴ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.8.2. (ለ) ላይ የተመለከተው ሲሆን፣ ለዋጋ የሚሰጠው አንፃራዊ ክብደት ከጠቅላላው የማወዳደሪያ ነጥብ ሃምሳ በመቶ (50%) ማነስ የለበትም፡፡

17.8.7. ለግንባታ ሥራ እና ለዕቃ ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.8.2.(ለ) ላይ የተመለከተውን የጨረታ መገምገሚያ ዘዴ መጠቀም አይቻልም፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተቋሙን ለዋና ዳይሬክተር በማሳወቅና በማስፈቀድ መጠቀም ይቻላል፡፡

17.8.8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 17.8.2.(ለ) እና አንቀጽ 17.8.7 እንደተጠበቀ ሆኖ በግንባታ ሥራ ግዥ ዘርፍ የሚጠየቀው የሥራ ልምድና የብቃት መስፈርት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ "6" ከተመለከቱት መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል።

17.9. ጨረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ ስለመወሰን

17.9.1. የተቋሙ የጨረታ ሰነድ በሚዘጋጅበት ጊዜ የመጫረቻ ሠነድ የሚቀርብበትን የመጨረሻ ቀን የሚከተሉትን መሰረት አድርጎ ይወሰናል፡-

ሀ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዱን ለማግኘት፣ ተቀባይነት ያለው የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት፣ መረጃ ለማሰባሰብ፣ ለመተንተን፣እንደ አግባብነቱ ሽርክና መመስረት፣ ከአምራቹ የሚሰጥ ውክልና እና የመፈረም ስልጣን ማረጋገጫ ለማግኘትና ሌሎች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚፈጅባቸውን ጊዜ፣

ለ/ ግዥው በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈጸም ሲሆን የመጫረቻ ሰነዱን የጨረታ ማቅረቢያ ቦታ ድረስ ለመላክ የሚያስፈልገውን ጊዜ፣

ሐ/ በተለይ የግንባታ ሥራ ግዥ በሚሆንበት ጊዜ ለግንባታ ቦታ ጉብኝት ከጨረታ በፊት ለሚደረግ ቅድመ ጨረታ ውይይት የሚያስፈልገውን ጊዜ፣

17.9.2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.9.1. ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨረታ በአየር ላይ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር 3 ላይ ከተገለጸው ቀን ያነሰ መሆን የለበትም።

17.10. የጨረታ ሰነድ ሽያጭ

17.10.1. ለማንኛውም ጨረታ የተዘጋጀው የጨረታ ሠነድ የመሸጫ ዋጋ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ በማስገባት በተቋሙ የሚወሰን ይሆናል፡-

ሀ/ የጨረታ ሰነድ መሸጫ ዋጋ ተቋሙ ለግዥው በርካታ ተወዳዳሪዎች እንዳያገኝ የሚሆን መሆን የለበትም፣

ለ/ ተቋሙ ለማንኛውም የጨረታ ሰነድ የዋጋ ተመን በሚወስንበት ወቅት ትርፍን ማዕከል ያላደረገና ለሰነድ ዝግጅትና ሰነዱን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለማቅረብ የወጣውን ወጪ ለመተካት ብቻ ያለመ መሆን ይኖርበታል፣

ሐ/ ተቋሙ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው የጨረታ ሰነዱ በነጻ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል።

17.10.2. ተቋሙ የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደአስፈላጊነቱ የጨረታ ሰነዱ በነጻ እንዲሰጥ ወይም ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ ከወጣው ወጪ ባነሰ ለተጫራቾች እንዲሸጥ ሊፈቅድ ይችላል፡-

ሀ/ በጨረታው በቂ ተወዳዳሪ አይኖርም ተብሎ ሲገመት፣ ወይም

ለ/ ለጨረታው ሠነድ ዝግጅቱ የወጣው ወጪ ግምት በጣም አነስተኛ ነው ብሎ ተቋሙ ሲያምን፣ ወይም

ሐ/ ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ የወጣው የወጪ ግምት ከፍተኛ በመሆኑ ወጪውን ሙሉ በሙሉ ተጫራቾች እንዲሸፍኑ ቢደረግ የጨረታ መሸጫ ዋጋ ከፍተኛ ስለሚሆን በቂ ተወዳዳሪ እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል ብሎ ሲያምን፣

መ/ ጨረታው በድጋሚ እንዲወጣ የተደረገና በመጀመሪያው ጨረታ ለመሳተፍ ሰነድ የገዙ እጩ ተወዳዳሪዎች እንደገና እንዲገዙ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑ በተቋሙ ሲታመን፣

17.10.3. የጨረታ ሰነዱ ጨረታው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሚዘጋጅበት ጊዜ ድረስ ባለት የሥራ ቀናት በጨረታ ማስታወቂያው በተገለጸው አኳኃን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዝግጁ መሆን አለበት።

17.11. <u>ስለ ናሙና አቀራረብ</u>

17.11.1. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ወይም ከተዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጨማሪነት ግዥው በተሻለ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው የናሙና ምልከታ ሲኖረው መሆኑ ሲታመንበት ተቋሙ በተጨማሪነት ናሙና ሊያቀርብ ወይም እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል።

17.11.2. ተቋሙ ናሙና ራሱ አቅርቦ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለዕይታ በቀረበው ናሙና መሰረት እንዲያቀርቡ በሚፈልግበት ወቅት፦

ሀ/ በተቋሙ የሚቀርበው ናሙና በአንድ አምራች ወይም የንግድ ምልክት በተሠራ ዕቃ የተወሰነ መሆን የለበትም። እስከተቻለ ድረስ ተቀባይነት ያላቸው ናሙናዎች ዓይነት ለዕይታ እንዲቀርቡ ሆኖ ከቀረቡት ናሙናዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጥራት ደረጃ ያላቸው ሌሎች ዕቃዎችንም ማቅረብ እንደሚቻል ለተጫራቾች ማሳወቅ ይገባል፣

ለ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙናውን በግልጽ የሚያዩበት ቦታ ላይ መደረጉን እና ተገቢ እስከሆነ ድረስ ስለናሙናው መግለጫ የሚሰጥ ባለሙያ መመደቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣

ሐ/ ተቋሙ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዕይታ ካቀረበው ናሙና በተጨማሪ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያዘጋጅ ከሆነ የሚዘጋጀው መግለጫ እስከተቻለ ድረስ የቀረበውን ናሙና የሚገልጽና ለዕይታ ከቀረበው ናሙና የቴክኒክ ባሕሪይ ጋር የተጣጣመ መሆን ይገባል፣

17.11.3. በተሰጣቸው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መሰረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙና እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት፦

ሀ/ የሚቀርቡት ናሙናዎችን አይነት፣ ብዛት የሚቀርቡበትን ጊዜ እና አኳኋን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በግልጽ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፣

ለ/ ናሙናዎች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት መቅረብ ያለባቸው ቢሆንም ዕጩ ተወዳዳሪው ናሙናውን በወቅቱ ልኮ ከዕጩ ተወዳዳሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት በማጓጓዝ ሂደት ቢዘገይ የተቋሙ የግዥውን አፈጻጸም አይጎዳም ብሎ እስካመነ ድረስ ተጨማሪ የናሙና ማቅረቢያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፣

17.11.4. ተጫራቾች የተሟላ ናሙና በአካል ማቅረብ የማይችሉ ሲሆን እና የማይችሉበትንም ምክንያት ተቋሙ ሲቀበለው ስለናሙናው ያላቸውን መረጃ ማቅረብ እንዲችሉ ሊፈቅድ ይችላል:: ይህም የናሙናውን ፎቶግራፍ ወይም የተገኘውን የናሙና ክፍል ማቅረብ ይጨምራል:: ሆኖም በዚህ መልኩ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚቻለው አፈጻጸሙ የተሻለውን ተጫራች በመምረጥ ሂደት ልዩነት የማያመጣና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፣

17.11.5. ተቋሙ በተጫራቾች የቀረቡ ናሙናዎችን በጥንቃቄ የመያዝ እና የመፈተሽ ኃላፊነት አለበት:: ሆኖም ተጫራቾች ያቀረቡት ናሙና በሚመረመርበት ወቅት በዕቃው ባህሪይ ምክንያት ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ካሣ አይከፈላቸውም:: በምርመራ ሂደት ያልጠፉ ወይም ያልተበላሹ ናሙናዎች ከምርመራ በኋላ ለተጫራቾች ተመላሽ ይደረጋሉ:: ተጫራቾች ያቀረቡትን ናሙና የጨረታው ውጤት ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልወሰዱ በውርስ ለተቋሙ ገቢ ይደረጋል፣

17.11.6. በተቋሙ የተለየ ውሳኔ ካልተሰጠ በስተቀር የአሸናፊው ተጫራች ናሙና ግዥው እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ በናሙናነት ተይዞ መቆየት ያለበት ሲሆን ናሙናውም በርክክብ ወቅት ለማነጻጸሪያነት እንዲያገለግል መደረግ ይኖርበታል::

17.12. <u>ጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ</u>

17.12.1. ተቋሙ በራሱ ወይም የጨረታ ሰነድ ከገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መነሻ የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የጨረታ ሰነዶችን ይዘት ለማሻሻል ይችላል፣

17.12.2. በተቋሙ በተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ ከማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ የሚቀርብ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄን ተቀብሎ ምላሽ ይሰጣል፣

17.12.3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.12.1. የተገለጸው ቢኖርም የሚከተለውን ሳያሟላ ለቀረበ ማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ተቋሙ ምላሽ እንዲሰጥ አይገደድም:-

ሀ/ በዚህ መመሪያ በተገለጸው መሰረት ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 30 ቀናት ለሆነ ውስብስብ የአገር ውስጥ ግዥ ለመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ ከ10 ቀናት በታች ሲቀረው ለቀረበ ጥያቄ፣

ለ/ ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ለመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ ከ21 ቀናት በታች ሲቀረው የቀረበ ጥያቄ፣

ሐ/ ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 15 ቀናት በታች ለሆነ ውስብስብ ያልሆነ ግዥ ጨረታው ሊዘጋ ከ5 ቀናት በታች ሲቀረው የቀረበ ጥያቄ፣

17.12.4. ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ለሚቀርብ የማብራሪያ ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ በጽሑፍ ሆኖ የጠያቂውን ማንነት መግለጽ ሳያስፈልግ ለሁሉም ተሳታፊ ለመሆን ላመለከቱ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ እንዲላክ መደረግ አለበት፣

17.12.5. ተቋሙ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርብለትን የማብራሪያ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል በተቋሙ በተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጨረታ ሠነዱን ማሻሻል ይችላል። ማንኛውም የጨረታ ሠነዱን ይዘት የሚቀይር ማሻሻያ በተጨማሪ የጨረታ ሰነድነት የጨረታውን ሠነድ ለገዙ ሁሉ በእኩል ጊዜ እንዲደርስ መደረግ አለበት፣

17.12.6. ተቋሙ የግዥ መመሪያ በአንቀጽ 17.12.5. ላይ በተገለጸው መሰረት በጨረታ ሰነዱ ላይ ማሻሻያ ሲያደርግና ጨረታውን ለመዝጋት በቀረው ጊዜ ውስጥ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የተደረገውን ማሻሻያ አካተው የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንደማይችሉ ሲገመት የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም ይችላል፣

17.12.7. ተቋሙ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ተቋሙ በተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ የጨረታ ሰነድ የገዙትን ተጫራቾች በሙሉ የማብራሪያ የማሻሻያ ገለጻና ውይይት ለማድግ ሊጠራ ይችላል። የሚደረገው ውይይትም በቃለ-ጉባዔ መያዝ ይኖርበታል፣

17.12.8. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በሚያዘጋጁበት ወቅት ማሻሻያውን ማካተት እንዲችሉ በተደረገው የጨረታ ሰነድ ማሻሻያና ማብራሪያ ውይይት ላይ የተያዘው ቃለ-ጉባዔ ቅጂ የጨረታውን ሠነድ ለገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሙሉ እንዲደርስ መደረግ አለበት።

17.13. <u>የጨረታ ቋንቋ</u>

17.13.1. የሚዘጋጀው የጨረታ ማስታወቂያ፣ የጨረታ ሠነድ እና ጨረታው የሚካሄድበት ቋንቋ፡-

ሀ/ የአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ የሚሳተፉበት የብሔራዊ ግልጽ ጨረታ በአማርኛ ቋንቋ ይሆናል። ሆኖም ለግዥው አካሄድ አመቺ ሆኖ ከታመነበት የተሟላ ውድድርን እንደማይገድብ ተረጋግጦ ተቋሙ የጨረታ ቋንቋው በእንግሊዘኛ መሆኑ የተሻለ ውድድርና ጠቀሜታ እንዳለው ሲያምን የጨረታ ማስታወቂያው፣ የጨረታ ሰነዱ እና የጨረታው ሂደት በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል፣

ለ/ ለዓለም ዓቀፍ ግልጽ ጨረታ ማስፈጸሚያ የሚዘጋጅ ማናቸውም ሰነድ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይሆናል።

17.13.2. ከላይ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውንና ደጋፊ ማስረጃዎቻቸው በጨረታ ሰነዱ ጨረታው እንዲካሄድበት ከተፈቀደው ውጪ በሌላ ቋንቋ የተዘጋጀ በሚሆንበት ጊዜ በተለይ የጨረታውን መሰረታዊ ይዘት ሊቀይሩ የሚችሉ ሰነዶች በህጋዊ ተርጓሚ ከተተረጎመ ቅጂ ጋር አንድ ላይ በማድረግ ማቅረብ አለባቸው፣

17.13.3. ተቋሙ በተጫራቹ የቀረበው ሰነድ በመጀመሪያ በተዘጋጀበት እና ለጨረታው በተፈቀደው ቋንቋ ትርጉም መካከል ልዩነት እንዳለው ሲያረጋግጥ ልዩነቱ በጨረታው ይዘት ላይ መሰረታዊ ለውጥ አያመጣም ብሎ ካላመነ በስተቀር ሰነዱን ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል።

17.14. <u>የጨረታ ዋጋ እና የዋጋ ማስተካከያ</u>

17.14.1. ተቋሙ ከተጫራቾች የሚሰጡ የመጫረቻ ዋጋዎች በሌላ ተጫራቾች ዋጋ ላይ ያልተመሰረቱና በጨረታው እና በውል አፈጻጸሙ ወቅት የማይለዋወጡ ፅኑ ዋጋ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፣

17.14.2. በአንቀጽ 17.14.1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም፣ ተቋሙ የሚከተሉትን ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ ለግንባታ ስራዎች ውል ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት 18 ወራት በኋላ እና በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸሙ ግዥ ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት 6 ወራት በኋላ ለሚኖር ግዥ የዋጋ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሠነዱ ላይ ማመልከት የሚኖርበት ሆኖ፡-

ሀ/ በውል ስምምነቱ መሰረት የግንባታ ስራውን ለማጠናቀቅ ከ18 ወራት እንዲሁም በማዕቀፍ ስምምነት ጊዜ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ ከስድስት ወራት በላይ የሚፈጅ መሆኑን የተረጋገጠ ሲሆን፣

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መነሻ እና የተለወጠ ወቅታዊ ዋጋ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚሰጥ ሲሆን፣

ሐ/ የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግበት በሚመረጠው ስብስብ ላይ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የዋጋ ኢንዴክስ ወይም የጠቋሚ ዋጋ መረጃ መስጠት መቻሉ ሲረጋገጥ፣

መ/ በንዑስ አንቀጽ 17.14.2 (ሐ) የተገለጸው ቢኖርም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የዋጋ ኢንዴክስ መረጃ መስጠት ባልቻሉባቸው ስብስቦች ላይ ተቋሙ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ይገባል ብሎ ሲያምን ለውጥ የሚደረግባቸው ስብስቦች በያዘው ምድብ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል የዋጋ መረጃ ከታወቀ የአገር ውስጥ አምራች ድርጅት ወይም በውጪ አገር ከሚገኝ ሕጋዊ ተቋም ማግኘት ሲቻል።

### 17.14.3. ለግንባታ ሥራ ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

በንዑስ አንቀጽ 17.14.2 የተገለጹት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ከግንባታ ስራ ግዥ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ከዚህ በታች የተገለጹትን አሠራሮች ተከትሎ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ቀመር በመጠቀም መሰላት ይኖርበታል፡-

ሀ/ ለግንባታ ሥራው የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብዓቶችና በእያንዳንዱ ዋና ግብዓት ሥር ሊካተቱ የሚችሉ ዕቃዎችን ስብስብ መለየት፣

ለ/ በሥራቸው የተለያዩ ዕቃዎች ስብስቦችን የያዙት ዋና ዋና ግብዓቶች፣ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ ግብዓቶች ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ በማስላት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸውን እና የማይደረግባቸውን መወሰን፣

ሐ/ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በሥራ ላይ ያለው የዋጋ ኢንዴክስ/ጠቋሚ አሃዝ በቀመሩ መሠረት የዋጋ ማስተካከያውን ለማስላት በመነሻነት ይወሰዳል፣

መ/ የዋጋ ማስተካከያው ጥያቄ በንዑስ አንቀጽ 17.14.2 ላይ የተገለጸውን ድንጋጌ ተከትሎ በሚቀርብበት ወቅት በተለይ ለግንባታ ሥራ ግዥ የዋጋ ልዩነቱ የሚሰላው በሥራ ላይ ያለውን ወቅታዊ የዋጋ ኢንዴክስ/ጠቋሚ አሃዝን በመጠቀም በቀመሩ መሰረት ይሆናል፡፡

### 17.14.4. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

ተቋሙ በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጽመው ግዥ ዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ የሚችለው በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፡-

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ወይም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ ዋጋ መረጃ ለሚሰጥባቸው አቅርቦቶች ብቻ መሆን አለበት፣

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ተፈጻሚ ለሚሆን ግዥ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ መቅረብ የሚኖርበት ስምምነቱ ስራ ላይ ከዋለ ከሶስት ወራት በኋላ ሊሆን ይገባል፣

ሐ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት ዕቃ ወይም አገልግሎት አስመልክቶ ጨረታው በተከፈተበት ዕለት የነበረው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚያወጣው ዋጋ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ በኮንትራት ስምምነቱ ላይ መገለጽ አለበት፣

መ/ ተቋሙ በውሉ ላይ በተገለጸው እና በጨረታው መክፈቻ ዕለት ተፈጻሚ በነበረው እና አሁን ያለውን ወቅታዊ ዋጋ አስመልክቶ ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተሰጠው ዋጋ መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት በማስላት ልዩነቱ በአቅራቢው ዋጋ ላይ እንዲጨመር ወይም እንዲቀነስ በማድረግ የሚቀጥለው የዋጋ ማስተካከያ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ የተስተካከለውን ዋጋ ተፈጻሚ ማድረግ አለበት፣

ሠ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሠረት ማቅረብ ሲገባው በወቅቱ ላላቀረባቸው እና ዘግይተው ለቀረቡ አቅርቦቶች የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው አቅርቦቶቹ መቅረብ በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

## 17.14.5. ለምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

ሀ/ በምክር አገልግሎት ግዥ የውል አፈጻጸም ወቅት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል መፈጸሚያ ጊዜው በመራዘሙ ለአማካሪው የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ተቋሙ በሚያምንበት ጊዜ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፣

ለ/ በንዑስ አንቀጽ 17.14.5.(ሀ)የተገለጸው ቢኖርም ለአማካሪዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ከአስራ አምስት ከመቶ (15%) ሊበልጥ አይችልም፡፡

17.14.6. ተቋሙ የዋጋ ማስተካከያ የሚያደርግባቸው ዕቃዎች ወይም አቅርቦቶች ለተካተቱበት ግዥ በሚያዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ የሚከተሉትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሁኔታዎች በግልጽ ማመልከት ይኖርበታል፡-

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያውን ተግባራዊ ለማድረግ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ያለባቸውን የመረጃ ዓይነት፣

ለ/ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው የሚቀርብባቸውን ሁኔታዎች፣ የአቀራረብ ዘዴውን እና ከዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ዓይነትና መጠን፣

ሐ/ ሌሎች ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም ይጠቅማሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን መረጃዎች እና ተጫራቾች ሊከተሉት ይገባል የሚላቸውን አሰራሮች፣

17.14.7. ተቋሙ በጨረታ ግምገማ ወቅት ተጫራቾች ለዋጋ ማስተካከያ ዓላማ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች መቀበላቸውን እና ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፣

17.14.8. ተቋሙ እና በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች በሚያደርጉት የውል ስምምነት ላይ የሚከተሉት እና ሌሎች ተገቢ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ሁኔታዎች በግልጽ እንዲካተቱ መደረግ ይኖርበታል፡-

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸውን ግብዓቶች በመጠቀም የሚመረቱ ዕቃዎች ወይም አቅርቦቶችን ዝርዝር እና የማስተካከያ አፈጻጸም፣

ለ/ ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም ተቋሙና አቅራቢው የተስማሙበት የሰነድ አይነት እና ምንጭ፣

ሐ/ ለዋጋ ማስተካከያ የሚቀርበው ማስረጃ በውሉ ላይ በተገለጸው መሰረት መሆን እንዳለበት እና ከሌላ ምንጭ የሚመጣ መረጃ ተቀባይነት እንደማይኖረው፣

መ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት በወቅቱ ሥራውን ወይም አቅርቦቱን ማከናወን ባለመቻሉ የሚፈጠር የዋጋ መናር ማስተካከያ የማይደረግለት ስለመሆኑ፣

17.14.9. የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ የውል ዋጋ 25 % ( ሃያ አምስት ከመቶ) በሚበልጥበት ጊዜ የዋጋ ለውጡን ተቀብሎ ግዥውን መቀጠሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን

ተረድቶ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት እንዲችል የተቋሙ የበላይ ኃላፊ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፣

17.14.10. የተቋሙ የዋጋ ማስተካከያ ለተፈቀደበት ማንኛውም ግዥ ከአቅራቢው የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ባይቀርብም የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለት የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግላቸው በውል ስምምነቱ በተፈቀዱ ግብዓቶች ላይ የዋጋ መቀነስ መኖር አለመኖሩን የማጣራትና የዋጋ ቅናሽ ካለም አስልቶ ከቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ ከቀነሰ በኋላ መክፈል ይኖርበታል፡፡

17.15. <u>የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>

17.15.1. የተቋሙ የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ መቆየት ያለበትን ጊዜ በጥንቃቄ በመወሰን በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ማካተት ይኖርበታል፡፡ የመጫረቻ ሰነድ ወይም የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደ ግዥው አይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ጊዜውን ለመወሰን ተቋሙ የሚከተሉትን ማገናዘብ ይኖርበታል፡-

ሀ/ የግዥውን ውስብስብነት እና የጨረታ አፈጻጸም ሂደቱ ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ፣

ለ/ በጨረታው ሊሳተፉ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ብዛት፣

ሐ/ የተቋሙ ተመሳሳይ ግዥዎችን በመገምገም ረገድ ያለው ልምድ፣

መ/ ግዥው በገበያ ላይ ያለውን የዋጋ ተለዋዋጭነት ሁኔታ፣

17.15.2. በንዑስ አንቀጽ 17.15.1 ላይ በተገለጸው መሰረት የሚወሰነው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ተቋሙ ግዥውን ለመገምገም፣ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ግዥውን ለማፅደቅ፣ አቤቱታ ቢነሳ ለማስተናገድ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል እስከመፈራረም ድረስ የሚፈጀውን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣

17.15.3. በንዑስ አንቀጽ 17.15.2 ላይ በተገለጸው መሰረት የመጫረቻ ሰነድ ረዘም ላለ ጊዜ ፀንቶ የሚቆይበት ሁኔታ መኖሩን ተቋሙ ካላመነ በስተቀር ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ጨረታው ከሚከፈትበት ዕለት ጀምሮ ከ60 ቀናት መብለጥ የለበትም፣

17.15.4. የተቋሙ የግዥ ሂደት የመጫረቻ ሰነዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እና አሸናፊው ድርጅት ጋር ውል መፈራረም ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የግዥ ሂደቱ ሳይጠናቀቅ ለግዥው የቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃ መሆኑን መሥሪያ ቤቱ ሲረዳ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለተጨማሪ ቀናት እንዲያራዝሙለት መጠየቅ አለበት፣

17.15.5. በንዑስ አንቀፅ 17.15.4 ላይ በተመለከው መሰረት ተጫራቾች እንዲያራዝሙ የሚጠይቀው ተጨማሪ ቀናት ተቋሙ የቀረውን የግዥ ሂደት ለማጠናቀቅ የሚበቃውን ያህል ቀናት ብቻ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ተጫራቾች በማንኛውም ምክንያት ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ባይሆኑ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙትን ዋስትና መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ውድድር እንዲወጡ ይደረጋል፣

17.15.6. የቀረበላቸውን ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ የማሻሻያ ጥያቄ የተቀበሉ ተጫራቾች ጥያቄውን መቀበላቸውን እና የመቆያ ጊዜውን ያራዘሙት እስከመቼ እንደሆነ በመጥቀስ በጽሑፍ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ለዚህ ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ዋስትና መቆያ ጊዜ ማሻሻያ ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፣

17.15.7. በንዑስ አንቀፅ 17.15.6 በተገለጸው መሰረት የጨረታ ዋስትናውን ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያላሻሻለ ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውድድር ውጪ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

17.16. <u>የጨረታ ማስከበሪያ</u>

17.16.1. ከምክር አገልግሎት ግዥ በስተቀር ተቋሙ ግልጽ ወይም ውስን ወይም የሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴዎች በሚጠቀምበት ጊዜ በጨረታው ሰነድ ውስጥ ለእያንዳንዱ ግዥ የሚጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው በግልጽ መወሰንና ማመልከት አለበት፡፡ ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች አላስፈላጊነቱን ተቋሙ ካመነበት ለምክር አገልግሎት ግዥም ቢሆን ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንዲያስይዙ ሊጠይቅ ይችላል፣

17.16.2. ተቋሙ የጠቅላላ ግዥውን ግምታዊ ዋጋ መሠረት በማድረግ ከ0.5% ያላነሰና ከ2% ያልበለጠ የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ወስኖ በጨረታ ጥሪው እና በጨረታ ሰነዱ ውስጥ መግለጽ ይኖርበታል፡፡በዚህ መሰረት የሚወሰነው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) የበለጠ መሆን የለበትም፣

17.16.3. በንዑስ አንቀጽ 17.16.2 ላይ በተገለጸው መሰረት የተቋሙ የጨረታ ማስከበሪያ መጠንን ለመወሰን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ/ የሚገዛው ዕቃ/አገልግሎት የዋጋ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተለዋዋጭ መሆን፣

ለ/ በጨረታው የሚሳተፉ በቂ ተወዳዳሪዎች መኖር፣

ሐ/ ተጫራቾች እንዲያቀርቡ የሚጠየቀው ዋስትና በጨረታው እንዳይሳተፉ እንቅፋት እንደማይሆን፣

መ/ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ እንዲሆን የሚገፋፋ፣

ሠ/ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆን ዋስትናው በተቋሙ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማካካስ የሚመጥን መሆኑን፣

17.16.4. የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደተጫራቹ ምርጫ ጥሬ ገንዘብ ወይም ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የክፍያ ማዘዣ ቼክ ወይም የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተርኦፍ ክሬዲት ሊሆን ይችላል፣

17.16.5. በንዑስ አንቀጽ 17.16.4. የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በግንባታ ዘርፍ የተሰማሩ የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች ለጨረታ ማስከበሪያ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ የመድን ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፣

17.16.6. ከተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን በኋላ ቢያንስ ለተጨማሪ 28 ቀናት ፀንቶ መቆየት ይኖርበታል፣

17.16.7. የውጪ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ ባንኮች የተሰጠ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በአገር ውስጥ ባንኮች ማረጋገጫ ያገኘና በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ መሆን ይኖርበታል፣

17.16.8. ማናቸውም ተጫራች የሚከተሉትን ተግባራት ባለመፈፀም ምክንያት ያስያዘው ዋስትና ለተቋሙ ሊወረስበት ይችላል፦

ሀ/ በጨረታ ሰነዱ የተገለጸው የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ጊዜ ካለፈ በኋላ ወይም በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በተገለጸው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከጨረታው ካገለለ፣

ለ/ በጨረታው ውድድር አሸናፊ በመሆኑ ውል እንዲፈርም እና የውል ማስከበሪያ እንዲያሲዝ ተጠይቆ ውል ለመፈጸም እና የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፍቃደኛ ካልሆነ፣

17.17. <u>የመጫረቻ ሰነድ መረከብ</u>

17.17.1. ተቋሙ ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን የሚያስገቡት የጨረታ ሳጥን ማዘጋጀት አለበት። የጨረታ ሳጥኑም የጨረታ ጥሪው ላይ በተገለጸው ቦታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ እስከ መጨረሻው የማስመዝገቢያ ሰዓት ድረስ ክፍት ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፣

17.17.2. የጨረታ ሳጥን ደህንነት የተጠበቀ መሆን ያለበት ሲሆን ጨረታው እስከሚከፈት ቀንና ሰዓት ድረስ ቁልፉ በግዥ የሥራ ሂደት ኃላፊ ተይዞ መቆየት ይኖርበታል፣

17.17.3. እስከተቻለ ድረስ ማንኛውም የመጫረቻ ሰነድ ለጨረታው በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት። ሆኖም ለግዥው የሚቀርበው የመጫረቻ ሰነድ በሳጥን ውስጥ ሊገባ የማይችል በሚሆንበት ጊዜ ተቋሙ የጨረታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ የመጫረቻ ሠነድ የሚረከብ ሠራተኛ በመመደብ በተጫራቾች የሚቀርብን የመጫረቻ ሰነድ መረከብ ይኖርበታል፣

17.17.4. በንዑስ አንቀጽ 17.17.3 ላይ በተገለጸው መሰረት የተቋሙ ለሚረከበው የመጫረቻ ሰነድ መረከቡን የሚያረጋግጥ የመተማመኛ ሰነድ ሊሰጥ ይገባል። በዚህ መሰረት የቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶች ደህንነት መጠበቁን ግዥ ለመፈጸም የተመደበው ኃላፊ ማረጋገጥ ይኖርበታል፣

17.17.5. መጫረቻ ሰነድ በጽሁፍ ተዘጋቶና ተፈርሞበት በታሸገ ኢንቨሎፕ ውስጥ ሆኖ በጨረታ ማስታወቂያው ከተመለከተው የጊዜ ገደብ በፊት በተገለጸ ቦታ ገቢ መደረግ አለበት፣

17.17.6. ከመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት በኋላ ዘግይቶ የደረሰ የመጫረቻ ሰነድ እሽጉ ሳይከፈት ለተጫራቹ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

17.18. <u>የጨረታ አከፋፈት</u>

17.18.1. ተቋሙ በጨረታ ሰነዱ የተመለከተው የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የመጫረቻ ሰነድ ከማቅረቢያ የጊዜ ገደብ በፊት የቀረቡ የመጫረቻ ሰነድ መክፈት አለበት፣

17.18.2. ጨረታው የሚከፈተው በጨረታው ጥሪ ወይም ማሻሻያ ተደርጎ ከሆነ በማሻሻያ ሰነዱ ላይ በተገለጸው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በግልጽ ይሆናል፡፡ ጨረታው ሲከፈትም፡-

ሀ/ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በሚገኙበት ይሆናል፡፡ ሆኖም ተጫራቹ በራሱ ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ሳይገኝ መቅረቱ የጨረታውን መክፈት አያስተጓጉልም፣

ለ/ የጨረታ አከፋፈት ሂደቱን እስካላወከ እና የቦታ ጥበት እስከሌለ ድረስ በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ መገኘት የሚፈልግ ማንኛውም የመገናኛ ብዙሐን ድርጅት ወኪል ወይም ሌላ ፍላጎት ያለው ሰው በታዛቢነት መገኘት ይችላል፣

ሐ/ እስከተቻለ ድረስ የውስጥ ኦዲት ተወካይ ጨረታው ሲከፈት መገኘት አለበት፣

መ/ ከግዥ ሥራ ሂደት ቢያንስ 3 ባለሙያዎች በጨረታው አከፋፈት ሂደቱ ላይ መሳተፍ ይኖርባቸዋል፡፡ እስከተቻለ ድረስ የግዥው ተጠቃሚ ከሆኑ ሥራ ሂደቶች የሚወከሉ ባለሙያዎች በአከፋፈት ስነ-ስርዓቱ ላይ ሊገኙ ይችላሉ፡፡

17.18.3. በአንድ ኤንቬሎፕ እንዲቀርብ የተጠየቀ ጨረታ ከሆነ ተቋሙ እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ ያቀረበውን የመጫረቻ ሠነድ በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ ለውሉ ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ መጠንና ሁኔታውን፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዓይነትን እና መጠንን እና ማናቸውንም ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንጻራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ሌሎች ሁኔታዎችን በንባብ ከፍ ባለ ድምጽ ማሰማት እና መመዝገብ እንዲሁም ተጫራቾች በጠየቁ ጊዜ የተመዘገበውን ዝርዝር እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡

17.18.4. ጨረታው በሁለት ኤንቬሎፕ እንዲቀርብ የተጠየቀ ከሆነ፡-

ሀ/ በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ስርዓት የቴክኒክ ዶክመንቱን የያዘው ኤንቬሎፕ እንዲከፈት ተደርጎ የተጫራቹን ማንነት ጨምሮ በወቅቱ ሊገለጹ የሚችሉ ነጥቦች በንባብ መሰማት አለባቸው፣

ለ/ የሁሉም ዕጩ ተዋዳዳሪዎች የዋጋ ኤንቬሎፕ ሳይከፈት አንድ ላይ በሌላ ኤንቬሎፕ ታሽጎና በእሽጉ ላይ የጨረታው መለያ ቁጥር ተፅፎበት፣ የዋጋ ኤንቨሎፕ መሆናቸው ተገልጾ እና ጨረታውን የከፈቱት ኮሚቴዎች ባልደረቦች ተፈራርመውበት ሁለተኛው ዙር የጨረታ

መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት እስከሚካሄድ ድረስ የታሸገው ፖስታ በግዥ ሥራ ክፍል ወይም ኃላፊነት በተሰጠው አካል በጥንቃቄ ተይዞ መቆየት ይኖርበታል፣

ሐ/ የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎ የተገኘው ውጤት ሥልጣን በተሰጠው አካል ከፀደቀ በኋላ ውጤቱ በጨረታው ለተሳተፉ ተጫራቾች በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ በጽሑፍ መገለጽ ይኖርበታል፣

መ/ የቴክኒክ ግምገማውን ላላለፉ ተጫራቾች የሚጻፈው ደብዳቤ በጨረታው የተሸነፉበትን ምክንያት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ ተጫራቾቹም አቤቱታ ካላቸው አቤቱታቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡ አቤቱታ የሚቀርብበትና የሚመረመርበት ስርዓት በዚህ መመሪያ ክፍል አስራ አንድ የተገለፁትን ሁኔታዎች ተከትሎ ይሆናል፣

ሠ/ የቴክኒክ ውጤታቸው ተቀባይነት ላገኘ ተጫራቾች የሚጻፈው ደብዳቤ የዋጋ ኤንቨሎፕ የሚከፈትበትን ዕለት፣ ሰዓት እና ቦታ የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡ ደብዳቤውም በእኩል ጊዜ እንዲደርሳቸው መደረግ እና ሁሉም ፈቃደኛ ተጫራቾች በጨረታው የዋጋ ኤንቬሎፕ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንዲገኙ የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ሆኖም አቤቱታ የቀረበ ከሆነ አቤቱታው ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የዋጋ ኤንቬሎፑ መከፈት የለበትም፣

ረ/ በንዑስ አንቀጽ 17.18.4.ሠ መሠረት በሚደረግላቸው ጥሪ ተከትለው የቴክኒክ ግምገማውን ያለፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚገኙበት የዋጋ መወዳደሪያቸውን የያዘው ኤንቬሎፕ በግልጽ እንዲከፈት ይደረጋል፣

ሰ/ ለዋጋ ውድድር ያለፉ ተወዳዳሪዎችን ኤንቬሎፕ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 17.18.4.ረ ላይ በተገለጸው መሠረት በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ ለግዥው ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ ካለው መጠኑን እና ሁኔታውን፣ እንዲሁም ከዋጋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት፣

ሸ/ የቴክኒክ ግምገማው ውጤት እንደታወቀ በቴክኒክ ውድድሩ ተቀባይነት ያላገኙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንዲሁም የዋጋ መወዳደሪያቸውን የያዘው ኤንቬሎፕ ሳይከፈት ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡ ሆኖም በንዑስ አንቀጽ አንቀጽ 17.18.4.መ መሠረት በቴክኒክ ግምገማው ወጤት ላይ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ በአቤቱታው ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ እስኪታወቅ ድረስ በቴክኒክ የወደቁት ተጫራቾች የዋጋ ማወዳደሪያ ኤንቬሎፕም ሆነ ያስያዟቸው የጨረታ ዋስትናዎች ተመላሽ አይደረግም፡፡

17.18.5. የተቋሙ የግዥ ሥራ ክፍል የጨረታውን አከፋፈት ሂደት ቃለ-ጉባኤ መያዝ አለበት፡፡ ይህም ቃለ-ጉባኤ የተጫራቾቹን ስም፣ ያቀረቡትን ዋጋ እና በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ የተነሱ ሌሎችንም አስፈላጊ ነጥቦች የሚይዝ ይሆናል፡፡ ቃለ-ጉባኤው እና ተጫራቾች ያቀረቡት ዋናው የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ አከፋፈት ሂደቱ ላይ በተገኙት የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ይፈረማል፡፡ ጨረታው በተከፈተበት ጊዜ የተገኙ ተጫራቾች መገኘታቸውን በሚያረጋግጠው ዝርዝር ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል፣

17.18.6. ማንኛውም በጨረታ መክፈቻ ሥርዓት ላይ ያልተከፈተና ለተጫራቾች ያልተነበበ የመጫረቻ ሰነድ ለቀጣይ ውድድር ሊያገለግል አይችልም፡፡

17.18.7. ማናቸውም ተጫራች በጨረታ መክፈቻ ሂደት ወቅት ከጨረታው ውጭ ሊደረግ አይገባም፡፡

17.19. ጨረታን መገምገምና ማወዳደር

17.19.1. የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ

17.19.1.1. ተቋሙ ጨረታውን የተሟላ ነው ብሎ ለቀጣዩ ዝርዝር የግምገማ ሂደት ሊያሳልፈው የሚችለው በተጫራቹ የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ በመክፈቻ ሥነ-ሥርዓቱ ወቅት የተከፈተ እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎችና ተፈላጊ ነጥቦች ሙሉ ለሙሉ የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፣

17.19.1.2. ተቋሙ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን ወደ ዝርዝር ግምገማ ማሳለፍ የለበትም፡-

ሀ/ በጨረታው የተወዳደረው አቅራቢ ተቋሙ የሚፈልገውን አነስተኛና የጥራት መመዘኛ እና ሌሎች መሠረታዊ መስፈርቶችን ያላሟላ በመሆኑ በዚህ መመሪያ የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት በተመለከተው መሰረት ብቃት የሌለው ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ በንዑስ አንቀጽ 17.19.1.3 መሠረት የተደረገውን የሂሳብ ስህተት ማስተካከያ የማይቀበል አቅራቢ ሲሆን፣

ሐ/ ተጫራቹ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ያላስያዘ ወይም የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ያልሆነ ከሆነ፣

መ/ በተቋሙ የተጠየቁትን አስፈላጊ ማስረጃዎች ያላቀረበ ከሆነ፣

ሠ/ የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ ሰነዱ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ፣

17.19.1.3. በንዑስ አንቀጽ 17.19.1.1 ላይ የተመለከተው ቢኖርም ኤጀንሲው በምርመራ ወቅት የተገኙ የሒሳብ ስህተቶችን ማረም ይችላል፡፡ እንደዚህ ያሉትን የማስተካከያ እርምጃዎች ተቋሙ ባፋጣኝ ለሚመለከተው ተጫራች በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡ ተጫራቹ በሒሳብ ማስተካከያው የማይስማማ ከሆነ ከጨረታው እንዲወገድ ይደረጋል፣

17.19.1.4. በጨረታ ሰነዱ ከተዘረዘሩት ባህርይዎች፣ የውል ሁኔታዎች እና ከሌሎች ተፈላጊ ነጥቦች ጋር መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም ተቋሙ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡ ሆኖም ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ ተገልጾ በጨረታው ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት፡፡

### 17.19.2. ዝርዝር ግምገማ ማድረግና አሸናፊውን መለየት

17.19.2.1. ተቋሙ አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ የተቀበላቸውን የመጫረቻ ሰነዶች እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለጹትን የግምገማ መስፈርቶች ተጠቅሞ ዝርዝር ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡ በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ከተገለጸው መስፈርት ውጭ ግምገማ ማድረግ አይፈቀድም፡፡ በጨረታ ሰነዱ በሚገለጸው መሠረት ተቋሙ ሽናፊውን ተጫራች ለመምረጥ ከሚከተሉት የግምገማ ሥርዓቶች በአንዱ መጠቀም ይኖርበታል፡፡

ሀ/ በአንድ ኤንቬሎፕ የቀረበን ጨረታ የቴክኒክ ግምገማ መመዘኛዎችን ማሟላቱ የተረጋገጠ እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበን ተጫራች፣ ወይም

ለ/ በሁለት ኤንቬሎፕ የቀረበን ጨረታ የግዥውን የጠቀሜታ እሴት የሚወስኑ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ በሚካሄድ የቴክኒክና የፋይናንስ አጠቃላይ ግምገማ ድምር ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን ተጫራች በመምረጥ ይሆናል፣

17.19.2.2. ዝርዝር ግምገማ በሚደረግበት ወቅት ተጫራቾች የሰጡት በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋጋ ቅናሽ ታሳቢ ይደረጋል፣

17.19.2.3. እንደ አስፈላጊነቱ የተመረጠው ተጫራች ሕጋዊነት፣ የፋይናንስና የቴክኒክ አቋም በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት መሆኑ በድሕረ ግምገማ ሊረጋገጥ ይችላል፣

17.19.2.4. ግዥው በዓለም አቀፍ የጨረታ ዘዴ የሚፈጸም ሆኖ ለግምገማ ዓላማ ሲባል በተለየ ሁኔታ እንዲቀርብ በጨረታ ሰነዱ ካልተገለጸ በስተቀር በተጫራቾች የሚቀርበው ዋጋና የሚካሄደው የጨረታ ግምገማ ታክስን ማካተት ይኖርበታል፣

17.19.2.5. በግምገማ ወቅት ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ተጫራቾች እኩል ነጥብ ቢያገኙ ለሀገር ውስጥ ምርት ወይም አገልግሎት ቅድሚያ ሊሰጥ ይችላል፣

17.19.2.6. በንዑስ አንቀጽ 17.19.2.5 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል ነጥብ ያመጡ ወይም እኩል ተመራጭ የሆኑ ተጫራቾች በሚኖሩበት ጊዜ አሸናፊውን ለመለየት ተቋሙ እኩል ነጥብ ያመጡ ተጫራቾች በተወሰኑ መስፈርቶች ላይ የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግ፡-

ሀ/ እኩል ነጥብ ያመጡ ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸው መስፈርቶች ቁጥር ከሦስት ያልበለጠ እና በአኃዝ ሊገለጽ የሚችል መሆን ይኖርበታል፣

ለ/ መስፈርቶቹ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተለይም በጨረታ ዝርዝር መግለጫው ላይ መገለጽ ይኖርባቸዋል፣

ሐ/ እኩል ነጥብ ያመጡ ተጫራቾች እኩል መሆናቸው ሲረጋገጥ ይኸው ተገልፆላቸው መጀመሪያ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጹት መስፈርቶች መሠረት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፣

መ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሣብ እስከተቻለ ድረስ እኩል የወጡት ተጫራቾች በተገኙበት ተከፍቶ የሰጡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲነበብላቸው ይደረጋል፣

ሠ/ እኩል ነጥብ ያመጡ ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሳብ ተገምግሞ የተሻለ ሀሳብ ያቀረበው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ተደርጎ ይመረጣል፣

ረ/ በንዑስ አንቀጽ 17.19.2.6 ፊደል ተራ ‹‹ሠ›› የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል ነጥብ ያመጡ ተጫራቾች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሃሳብ ባለማቅረባቸው ወይም ባቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሳብ መሠረት በተደረገ ግምገማ በድጋሚ እኩል ቢሆኑ እስከተቻለ ድረስ እኩል የሆኑት ተጫራቾች በተገኙበት አሸናፊው ተጫራች በዕጣ እንዲለይ ይደረጋል፣

17.19.2.7. ተቋሙ የጨረታውን አሸናፊ በሚመርጥበት ጊዜ መለኪያው ተለይቶ የሚታወቅ እስከሆነ ድረስ በእያንዳንዱ የዕቃ ወይም አገልግሎት መለኪያ የተሰጠውን የነጠላ ዋጋ ወይም ሌሎች የውል ቃሎች እና ሁኔታዎችን ሳይለወጥ እንደአስፈላጊነቱ የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ብዛት (መጠን) እስከ 20% (ሃያ በመቶ) ድረስ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር የሚችል ስለመሆኑ በጨረታ ሰነዱ ላይ መገለጽ ይኖርበታል፣

17.19.2.8. ተቋሙ የማናቸውም ጨረታ ግምገማ በተጫራቾች የተሰጠው የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የመጨረሻ ቀን ከማለፉ በፊት ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ለተጫራቾች መግለጽ አለበት፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ግምገማውን በጊዜው ማጠናቀቅ ካልቻለ ተጫራቾች ዋጋው ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ እንዲያራዝሙ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.15.4 መሠረት መጠየቅ ይገባዋል፣

17.19.2.9. ተቋሙ ባወጣው ግልጽ ጨረታ የቀረበው አንድ ተጫራች ያቀረበው የመወዳደሪያ ሃሳብ አጥጋቢ እና ዋጋውም ተወዳዳሪ የገበያ ዋጋ መሆኑን እንዲሁም የሌሎች ተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ የሚገድቡ ምክንያቶች በጨረታ ሰነድ ላይ ያለመኖራቸውን ካረጋገጠ ድጋሚ ጨረታ ማውጣት ሳያስፈልግ የቀረበውን አንድ ተጫራች አሸናፊ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 17.19.3. ጨረታን የመወዳደሪያ ሃሳብን እና የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ስለማድረግ

17.19.3.1. ተቋሙ ከሚከተሉት በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ጨረታን፣የመወዳደሪያ ሃሳብን እና የዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ስምምነት ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ ይችላል፡-

ሀ/ በግዥ አካሄዱ ላይ ውጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈጸሙ ከተረጋገጠ፣

ለ/ በሥራ ዕቅድ መቀየር ምክንያት ወይም ተቋሙ ፍላጎቱን ለሟሟላት ሌላ የተሻለ አማራጭ በመፈጠሩ ምክንያት ግዥውን ማካሄድ ለተቋሙ የተሻለ ቴክኒካል ወይም ኢኮኖሚካል ጥቅም የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ/ የቀረቡት ተጫራቾች በጨረታ ሠነዱ ላይ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት የማያሟሉ ሲሆን፣

መ/ በጨረታ የቀረበው ዝቅተኛ ዋጋ በማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ ከሚሰራጨው የገበያ ዋጋ በላይ ሲሆን እና ተቋሙ ድጋሚ ጨረታ በማውጣት የተሻለ ዋጋ የሚገኝ ሆኖ ሲገመት፣

ሠ/ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች የሰጠው ዋጋ ተቋሙ ለግዥው ከያዘው በጀት በላይ ሲሆን እና የበጀቱን ልዩነት ከሌላ ምንጭ ሟሟላት የማይቻል ሲሆን፣

ረ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የግዥ አካሄዱን ለማዛባት በመመሳጠራቸው በቂ ውድድር አለመደረጉ ሲረጋገጥ፣

17.19.3.2. ተቋሙ ጨረታን የመወደደሪያ ሃሳብን የዋጋ ማቅረቢያን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሰረዝ ሲያደርግ ምክንያቱን የሚገልጽ ማስታወቂያ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ወዲያውኑ እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም የምክንያቱን አግባብነት እንዲያስረዳ አይገደድም፣

17.19.3.3 ጨረታውን ውድቅ የማድረጉ ውሳኔ የተሰጠው ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ከሆነ የመጫረቻ ሰነዶቹ እንደታሸጉ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መመለስ አለባቸው፣

17.19.3.4 በዚህ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 17.19.3.1. (ከ "ሀ" እስከ "ለ") በተገለጹ በተገለጹ ምክንያቶች መሰረት ጨረታን የመወዳደሪያ ሃሳብን የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ በመደረጉ ምክንያት ተቋሙ ምንም ዓይነት ተጠያቂነት አይኖርበትም፣

## 17.19.4. <u>ድጋሚ ጨረታ ስለማውጣት</u>

ድጋሚ ጨረታ ማውጣት የሚያስፈልገው ፡-

ሀ/ በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው ዋጋ ጨረታው ከመውጣቱ በፊት በተቋሙ ከተገመተው ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ልዩነት የሚበልጥ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ባለመሆኑ አዲስ ጨረታ ማውጣት የሚሻል መሆኑ ሲታመንበት ወይም፣

ለ/ የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆንና ይህን ተጫራች በብቸኝነት እንዲቀርብ ያስቻለው በዚህ መመሪያ የተዘረጉትን ሥርዓቶች ያልጠበቀ አሰራር (ሁኔታ) በመኖሩ ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም በጨረታ ሰነዱ ላይ ለውጥ በማድረግ በርካታ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ማግኘት የሚቻል መሆኑ ሲታመን፣

17.20. <u>ልዩ ልዩ አስተያየት</u>

17.20.1. በፕሮፎርማና ከአንድ አቅራቢ ከሚፈጸም ግዥ በስተቀር በማናቸውም ግዥ ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች፣ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት አዋጅ መሠረት ለተቋቋሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፣ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ እና የምክር አገልግሎት ሥራዎች እንደ ሁኔታው ታይቶ ልዩ አስተያየት ሊደረግ ይችላል፣

17.20.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 17.20.1 መሠረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት በዋጋ ላይ በሚደረግ ውድድር ወቅት በሚከተለው መሠረት ተፈጻሚ መደረግ አለበት፡፡ ይኸውም፡-

ሀ/ ለዕቃዎች ግዥ 15% (አስራ አምስት በመቶ)

ለ/ ለግንባታ ሥራና ለምክር አገልግሎት ግዥዎች 7.5% (ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ)

17.20.3. በንዑስ አንቀጽ 17.20.2 (ሀ እና ለ) መሠረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት ዕቃውን ለማምረት ከወጣው ጠቅላላ ወጪ 35% (ሰላሳ አምስት በመቶ) እና ከዚህ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ እሴት መሆኑን የሚያስረዳ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ ይሆናል፡፡ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም «የታከለ ዋጋ» ማለት ከጠቅላላ ወጪ ላይ ከውጭ አገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሁም ከውጭ አገር ለተገኘ አገልግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ሲሆን፣ በምርት ላይ የሚከፈሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን አይጨምርም፣

17.20.4. ማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ወይም የምክር አገልግሎት ሥራ በንዑስ አንቀጽ 17.20.2(ለ) መሠረት የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲሟሉ ይሆናል፡-

ሀ/ ኩባንያው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣

ለ/ ከኩባንያው አክሲዮን ወይም የካፒታል ድርሻ ከ50% (ሃምሳ በመቶ) ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣

ሐ/ ከኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከ50% (ሃምሳ በመቶ) ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣

መ/ ከኩባኒያው ቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ ከ50% (ሃምሳ በመቶ) ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣

17.20.5. በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት አዋጅ መሠረት የተቋቋሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፡-

ሀ/ ከአገር ውስጥ አቅራቢዎች ጋር በሚያደርጉት ውድድር 3% (ሦስት በመቶ) ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል፣

ለ/ ግዥው በዓለም አቀፍ የግዥ ዘዴ የሚፈጸም ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 17.20.2 "ሀ"፣ "ለ" እና "ሐ" ላይ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ብቻ ተፈጻሚ ይደረጋል፣

ሐ/ በጨረታ ማስከበሪያ፣ በውል ማስከበሪያ እና በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ምትክ ተቋማቱን ካደራጃቸው አካል የሚሰጥ የዋስትና ደብዳቤ ተቀባይነት ይኖረዋል፣

መ/ ለጨረታው የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋምነት የተቋቋሙበትን የሕጋዊነት ማስረጃ በማሳየት ያለክፍያ በነፃ ይሰጣቸዋል፣

17.20.6. የዕቃዎች ፣ አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ሥራዎች ጥራትና ዋጋ ተመሳሳይ ሆኖ ተጫራቾች በግምገማ እኩል ነጥብ ሲያገኙ ለአገር ውስጥ ምርቶች፣ አገልግሎቶች ወይም ኩባንያዎች ቅድሚያ ይሰጣል።

17.21. <u>ከጨረታ ውጪ ማድረግ</u>

ከሚከተሉት ጥፋቶች ውስጥ አንዱን የፈጸመን ተጫራች ተቋሙ ከጨረታው ውጪ ሊያደርገው ይችላል፡-

ሀ/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የንግድ ግንኙነቶች ላለማድረግ ክልከላ ከጣለበት አገር የሚመጣ ዕቃና አገልግሎት ከሆነ፣ ወይም፣

ለ/ በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ውሳኔ ከዚያ አገር ዕቃዎችንና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማስመጣት ወይም ለዚያ ሀገር ሰዎች ወይም ድርጅቶች ማንኛውንም ክፍያ መፈፀም የተከለከለ ከሆነ፣

ሐ/ ይህን መመሪያ የሚጥሱ ድርጊቶችን መፈጸሙ የተረጋገጠ እንደሆነ፣ ወይም

መ/ ቀደም ሲል በወጡ ጨረታዎች የገባውን የግዥ ውል ግዴታ ባለማክበሩ እንዳይሳተፍ በኤጀንሲው ተወስኖበት መረጃው የተያዘ ከሆነ፣ ወይም

ሠ/ የተለየ አስተያየትን ለማግኘት ወይም ጨረታውን ለማሸነፍ ለማናቸውም ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ መደለያ መስጠቱ ወይም የመደለያ ሀሳብ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣ ወይም

ረ/ ተወዳዳሪው በጨረታው ሰነድ ላይ የማጭበርበር ተግባር መፈጸሙ ወይም ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር መመሳጠሩ ሲረጋገጥ፣

## 17.22. ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ውይይት

17.22.1. በግዥ ሂደት በማናቸውም ደረጃ ከተጫራቾች ጋር ውይይት ሊደረግ የሚችለው የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም ብቻ ይሆናል፡፡ በተቋሙ እና በአቅራቢዎች መካከል የሚደረጉ ውይይቶች በሁለት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይሆናሉ፡፡

እነዚህም፡-

ሀ/ በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ለመወያየት፣ ወይም

ለ/ የሁለት ደረጃ ጨረታ በሚሆንበት ጊዜ ጨረታው በሚያካትታቸው የግዢ ዓይነቶች ላይ ድርድር ለማድረግ፣

17.22.2. በንዑስ አንቀጽ 17.22.1 በተፈቀደው መሠረት ካልሆነ በስተቀር፣ ተቋሙ ጨረታው ከተከፈተ በኋላ የመወዳደሪያ ሀሳቡን ለመገምገም በሚያስችሉ ነጥቦች ላይ ማብራሪያ ከመጠየቅ በስተቀር ተጫራቾች ካቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ውስጥ ዋጋን ወይም ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን እንዲለውጡ መጠየቅ ወይም መፍቀድ የለበትም፡፡

## 17.23. ጨረታን ማጽደቅ

17.23.1. ተቋሙ የጨረታ ግምገማውን የሚያከናውነው የግዥ የሥራ ሂደት ወይም እንደአስፈላጊነቱ ጨረታ ለመገምገም የተቋቋመው ጊዜያዊ ቡድን በተጫራቾች የተሰጠው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ከአስተያየት ጋር ግዥውን ለማጽደቅ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማቅረብ አለበት፣

17.23.2. በዚህ መመሪያ መሠረት ግዥውን እንዲያፀድቅ ሥልጣን የተሰጠው አካል ግዥው የኤጀንሲው ግዥ አፈጻጸም ሥርዓትን የተከተለ እና የጨረታ ግምገማውን በጨረታ ሰነዱ በተገለጸው መስፈርት መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡ ውሳኔውም ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡-

ሀ/ የግምገማ ሪፖርቱን ሙሉ በሙሉ በመቀበል ቀጣይ አፈጻጸሞች እንዲከናወኑ መፍቀድ፣

ለ/ ሪፖርቱን ባለመቀበል ግምገማው እንደገና እንዲከናወን ማድረግ፣

17.23.3. ግዥውን የሚያጸድቀው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው የግምገማ ሪፖርት ላይ ግምገማውን የሥራው ቡድን ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊያደርግ ይችላል፣

17.23.4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.23.2(ለ) ላይ በተገለጸው መሠረት ግዥውን የሚያጸድቀው አካል የቀረበውን የግምገማ የውሳኔ ሃሳብ ያልተቀበለ ከሆነ ምክንያቱን በመግለጽ ከዚህ በፊት ግምገማውን ላከናወነው ቡድን እንዲመለስ የሚያደርግ ሲሆን ገምጋሚ ቡድኑም ከአጽዳቂው አካል በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ግምገማውን እንደገና አከናውኖ የተስተካከለውን ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፣

17.23.5. በአንቀጽ 17.23.4 ላይ የተመለከተው ቢኖርም ገምጋሚ ቡድኑ ወይም ማንኛውም የጨረታ ገምጋሚ ቡድን አባል የግዥ አጽዳቂ አካሉ በሰጠው አቅጣጫ ወይም በግምገማ ውጤት ላይ የማይስማማ ከሆነ በግምገማ ሪፖርቱ ላይ ያልተስማማበት ሃሳብ ተገልጾ የግዥ አጽዳቂ አካሉ በሰጠው ውሳኔ መሠረት ግዥው እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

17.24. <u>የጨረታ አሸናፊን ማሳወቅ</u>

17.24.1. ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ከጨረታ ምርመራ፣ከማብራሪያ፣ግምገማ እና አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት ከቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ጋር የተያዙ መረጃዎች በሚስጢርነት መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን አሸናፊው ተጫራች እስከሚገለጽ ድረስ ለተጫራቾች ወይም ከሥራው ሂደት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች መገለጽ የለባቸውም፣

17.24.2. ተቋሙ የጨረታውን ውጤት በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑት ተጫራቾች በሙሉ በእኩል ጊዜ በጽሑፍ መግለጽ አለባቸው፡፡ ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚገለጸው የተሸነፉበት ምክንያት እና አሸናፊ የሆነው ተጫራች ማንነት መሆን አለበት፣

17.24.3. በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች የሚላከው ደብዳቤ በተቋሙ እና በተጫራቹ መካከል እንደውል ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡ በተቋሙ እና በተጫራቹ መካከል ውል እንደተፈጸመ የሚቆጠረው ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ውል በተቋሙ ኃላፊ (በተቋሙ ኃላፊ ውክልና በተሰጠው) እና በተጫራቹ ሲፈረም ብቻ ነው፣

17.24.4. ለተጫራቹ ውል እንዲፈረም የሚላክለት ማስታወቂያ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት

ሀ/ተቋሙ በተጫራቹ የቀረበውን የመጫረቻ ሃሳብ የተቀበለ መሆኑን፣

ለ/ውሉ የሚፈጸምበትን ጠቅላላ ዋጋ፣

ሐ/ተጫራቹ ማስያዝ የሚገባውን የውል ማስከበሪያ መጠን እና የማስረከቢያውን የመጨረሻ ቀን፣

17.24.5. በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ተቋሙ በቅድሚያ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በመገምገም በውድድሩ ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች አሸናፊ ማድረግ ወይም አዲስ ጨረታ ማውጣት ይችላል፣

17.24.6. ተቋሙ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ ተወዳዳሪዎች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተመላሽ ማድረግ አለበት፣

ሀ/ ከአሸናፊ ተጫራች ጋር ውል ፈርሞ ተጫራቹ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ያቀረበ ከሆነ፣

ለ/ የተሸናፊ ተጫራች ወይም የጨረታ ማስከበሪያውን የመጠቀሚያ ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ያልሆነ ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያበቃ ከሆነ፣

17.25. <u>የውል ማስከበሪያ</u>

17.25.1. በዋጋ ማቅረቢያ ከሚፈጸም ግዥ እና ከኪራይ አገልግሎት ግዥ በስተቀር ለማናቸውም ሌላ የግዥ ውል ተቋሙ የውል ማስከበሪያ መቀበል አለበት፣

17.25.2. የጨረታው አሸናፊ ከተቋሙ ጋር ውል ከፈረመበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ለጨረታ ማስከበሪያ ተቀባይነት እንዳላቸው በንዑስ አንቀጽ 17.16.4 በተገለጹት የዋስትና ዓይነቶች መሠረት ክፊያ በሚፈጸምበት የገንዘብ ዓይነት ቢያንስ የውሉን ዋጋ 10% (አሥር በመቶ) በውል ማስከበሪያነት ለተቋሙ ማስያዝ አለበት፣

17.25.3. ተቋሙ አቅራቢው በውሉ መሠረት አለመፈፀሙን ሲያረጋግጥ በንዑስ አንቀጽ 17.25.2 መሠረት አቅራቢው ያስያዘውን የውል ማስከበሪያ ሙሉ በሙሉ መውረስ ይኖርበታል፣

17.25.4. በንዑስ አንቀጽ 17.25.3 የተገለጸው ቢኖርም በአቅራቢው ያልተሟላው የውል ግዴታ በተቋሙ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ወይም ተጨማሪ ወጪ እንደማያስከትል እና በአቅራቢው ቸልተኝነት ምክንያት የተፈፀመ አለመሆኑ በተቋሙ የግዥ አጽዳቂ አካል ሲታመንበት የውል ማስከበሪያው ለአቅራቢው ሊመለስለት ይችላል፣

17.25.5. ተቋሙ በዚህ ንዑስ አንቀጽ 17.25.4 መሠረት ለወሰዳቸው እርምጃዎች የተሟላ ሰነድ በመያዝ ለተቋሙ የበላይ ኃለፊ ወይም በሌላ ጉዳይ በሚመለከተው ሕጋዊ አካል ሲጠየቅ ማቅረብ እና የአሰራሩን አግባብነት ማስረዳት ይኖርበታል፣

17.25.6. በንዑስ አንቀጽ 17.25.2 የተመለከተው ቢኖርም፡-

ሀ/ ከአገር ውስጥ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ተቋራጮች ለሚፈጸም ግዥ ከታወቀ የመድን ድርጅት የሚቀርብ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የውል ማስከበሪያ ተቀባይነት ይኖረዋል፣

ለ/ የምክር አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የተሰማሩ አማካሪዎች በሚሰጡት የምክር አገልግሎት ሂደት ውስጥ በመሥሪያ ቤቱ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ተብሎ ሲገመት የባለሙያ የካሣ መድን እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይቻላል፣

ሐ/ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.20.5.ሐ በተገለጸው መሠረት በውል ማስከበሪያ ምትክ ካቋቋማቸው አካል የሚሰጣቸውን የዋስትና ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

መ/ የመድን አገልግሎት ግዥ ለመፈጸም በወጣ ጨረታ አሸናፊ የሚሆኑ የመድን ድርጅቶች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ያስቀመጡትን ገንዘብ በውል

ማስከበሪያነት ለመጠቀም ይችላሉ። ሆኖም በዚህ መንገድ ለሚያስይዙት ዋስትና በቂ መጠባበቂያ ያላቸው ስለመሆኑ ከባንኩ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

17.25.7. በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የተያዘው የውል ማስከበሪያ አቅራቢው የውል ግዴታውን ሙሉ በሙሉ እንዳጠናቀቀ መመለስ ይኖርበታል።

17.26. <u>የቅድሚያ ክፍያ</u>

17.26.1. በዚህ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት እንደአስፈላጊነቱ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30% (ሰላሳ በመቶ) የሚደርስ የቅደሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል። የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ መገለጽ ይኖርበታል፣

17.26.2. አቅራቢዎች በውሉ መሠረት ከሚጠይቁት የቅድሚያ ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅድመ ክፍያ ዋስትና እንደአቅራቢው ምርጫ ከታወቀ ባንክ የሚሰጥ የተረጋገጠ ቼክ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

17.26.3. በንዑስ አንቀጽ 17.26.2ላይ የተመለከተው ቢኖርም የአገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ከታወቀ የመድን ድርጅት ሊያቀርቡ ይችላሉ፣

17.26.4. በንዑስ አንቀጽ 17.20.5.ሐ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ለሚሰጠው የቅደሚያ ክፍያ ዋስትና ተቋሙ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው በጋራ በሚንቀሳቀስ የባንክ ሂሳብ ገንዘቡን ተቀማጭ በማድረግ ከውሉ ጋር ለተገናኙ እና አስፈላጊ ለሆኑ ወጪዎች በጋራ ፊርማ እንዲከፈል ማድረግ ይኖርበታል፣

17.26.5. በንዑስ አንቀጽ 17.25.3 እና 17.26.4 መሠረት ለግንባታ ዘርፍ ሥራ በተደረገ ውል መሠረት ለሚፈፀም የቅደሚያ ክፍያ የቀረበው ዋስትና የመድን ድርጅት ሲሆን ወይም በንዑስ አንቀጽ 17.26.4 መሠረት አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ከሆነ ውል ሰጪው ተቋሙ ውል ተቀባይ ከሆነው ሥራ ተቋራጭ ወይም አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋም ጋር የቅድሚያ ክፍያውን አጠቃቀም በሚመለከት የተለየ ውል መዋዋል አለበት። ውሉም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፣

ሀ/ በውሉ መሠረት ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ የሚፈጸመው የቅድሚያ ክፍያ ለዚሁ ዓላማ በሥራ ተቋራጩ ወይም በአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ ስም በሚከፈት የተለየ የባንክ ሂሳብ ውስጥ እንደሚቀመጥ፣

ለ/ ከላይ በፊደል ተራ ‹‹ሀ›› መሠረት በተከፈተው ሂሣብ ውስጥ የተቀመጠው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ወጪ ሊደረግ የሚችለው በውል ሰጪ እና በውል ተቀባዩ የጣምራ ፊርማ እንደሚሆን፣

ሐ/ በባንክ ሂሣቡ ከተቀመጠው ገንዘብ ላይ ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ ክፍያ የሚፈፀመው ቀደም ሲል በወሰደው ገንዘብ ተገቢውን ሥራ የሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ መሆኑን፣

መ/ በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከሚከፈል ገንዘብ ውስጥ ለመንገድ ሥራ የአገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ 50% (ሃምሳ በመቶ) እንዲሁም ለሕንፃ ሥራ የአገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ 30% (ሰላሳ በመቶ) ለመሣሪያ መግዣ ማዋል የሚችሉ መሆኑን የሚገልጹ አንቀጾችን ሊይዝ ይችላል፣

17.26.6. በንዑስ አንቀጽ 17.25.5.መ በተመለከተው መሠረት መሥሪያ ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ የሥራ ተቋራጮች በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከተሰጣቸው ገንዘብ ውስጥ ከፊሉን ለመሣሪያ መግዣ እንዲያውሉ ሊፈቀድ ይችላል፡-

ሀ/ የሥራ ተቋራጩ በቅድሚያ ክፍያ መልክ በወሰደው ገንዘብ የገዛውን መሣሪያ በውሉ መሠረት ፕሮጀክቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለዕዳ መያዣነት የማያውል እና በማናቸውም መልክ ለሦስተኛ ወገን የማያስተላልፍ ለመሆኑ ማረጋገጫ ካቀረበ፣

ለ/ የሥራ ተቋራጩ የቅድሚያ ክፍያ አከፋፈል ስምምነት ከመፈረሙ በፊት በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚወስደው ገንዘብ የሚገዛቸውን መሣሪያዎች ዓይነት ለአሰሪው መ/ቤት ተቆጣጣሪ መሐንዲስ አቅርቦ መሣሪያዎቹ ለሥራው አስፈላጊ መሆናቸው ከተረጋገጠ፣

ሐ/ መሣሪያዎቹ ከፕሮጀክቱ ባለቤት ፈቃድ ውጪ ከፕሮጀክቱ ወደ ሌላ ቦታ የማይንቀሳቀሱ መሆኑ ከተረጋገጠ ነው፣

17.26.7. በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚከፈል ገንዘብ ለመንገድ ሥራ እንዲሁም ለሕንፃ ግንባታ የሚገዙ ማሽነሪዎች በአባሪ 4 ላይ የተመለከቱት ብቻ ናቸው፣

17.26.8. ተቋራጩ በንዑስ አንቀጽ 18.26.6በተመለከተው መሠረት በተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ የገዛቸውን መሣሪያዎች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ፕሮጀክቱ ቦታ(ሳይት) ካላጓጓዘ በውሉ መሠረት ሊከፈለው የሚገባው የሚቀጥለው ክፍያ አይፈጸምለትም፣

17.26.9. ተቋራጩ ወይም አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋሙ የወሰደው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ በውሉ መሠረት በየደረጃው ከሚዘጋጁት የክፍያ ምስክር ወረቀቶች ወይም በየደረጃው ከሚጸሙ አቅርቦቶች ሂሣብ ላይ እየተቀነሰ እንዲመለስ መደረግ አለበት፣

17.26.10. በግንባታ ሥፍራ ላይ ለሚገኙ የግንባታ ዕቃዎች (ማቴሪያሎች) ከዋጋቸው እስከ ሃምሳ በመቶ (50%) የሚደርስ ክፍያ መፈጸም ይቻላል። ሆኖም ግዥ ፈጻሚ ተቋሙ የተጠቀሰውን የሃምሳ በመቶ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የሚከተሉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰድ ይኖርበታል፣

ሀ. በግንባታ ሥፍራ ላይ ለሚገኙ ዕቃዎች ክፍያ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ማናቸውም ሥራ ተቋራጭ የሚያቀርባቸው ዕቃዎች የተገዙበትን ዋጋ የሚያመለክት ደረሰኝ ትክክለኛነት በተቋሙ እና በአማካሪው መረጋገጥ ይኖርበታል፣

ለ. ክፍያ የተፈጸመበት በግንባታ ሥፍራ የሚገኝ የግንባታ ዕቃ ሥራ ላይ እንዲውል ሲደረግ የተፈጸመው ክፍያ ከሚቀጥለው ክፍያ መቀነስ አለበት፣

ሐ. በአንድ የግንባታ ስፍራ የሚገኙ ዕቃዎችን ለሌላ የግንባታ ፕሮጀክት በግብዓትነት መጠቀምም ሆነ ለሌላ የተለያየ ዓላማ ማዋል አይችልም፣

መ. ሥራ ተቋራጭ በግንባታ ሥፍራ ላይ ለሚገኙ ዕቃዎች ክፍያ እንዲከፍለው ከሚያቀርበው ጥያቄ ጋር ዕቃዎቹ በክምችት ላይ እያሉ አደጋ ቢደርስባቸው፣ ቢሰረቁ፣ ወይም ለረዥም ጊዜ ሥራ ላይ ሳይውሉ በመቅረታቸው ቢበላሹ የጉዳቱን መጠን ለማካካስ እንዲቻል በግንባታ ሥራ መደበኛ የጨረታ ሠነድ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 30 ላይ በተጠቀሰው አግባብ ኢንሹራንስ በመግባት ዕቃዎቹ ኢንሹራንስ የተገባላቸው መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፣

17.27. <u>ውል መፈረም</u>

17.27.1. ተቋሙ የመደበኛ ጨረታ ሰነዶች አንድ ክፍል የሆነውን አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ልዩ የውል ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሰነድ ከአቅራቢው ጋር መፈራረም አለበት፣

17.27.2. ተቋሙ እና በአቅራቢው መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈፀመ አይቆጠርም፣

17.27.3. በአቅራቢው እና በተቋሙ መካከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች ኃላፊነት በግልጽ ማመልከት ያለበት ሲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች በተጨማሪነት ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ/ በውሉ የሚቀርበው ዕቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች ዓይነት፣ ጥራት፣ ብዛት፣ የሚቀርበበት አኳኋን ወይም የማስረከቢያ ጊዜውን የሚከፈለውን አጠቃላይ እና የነጠላ ዋጋ መጠን፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና የክፍያ ጊዜውን፣

ለ/ ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን እንደ ትራንስፖርት፣ ኢንሹራንስ፣ ትራንዚት እና የመሳሰሉት ተግባራትን የመከታተል እና የመፈፀም ኃላፊነት የማን እንደሚሆን መጠቀስ ያለበት ሲሆን ኃላፊነቶቹም በተሻለ ብቃት ሊፈጽማቸው በሚችል አካል እንዲሰሩ መደረግ ይኖርበታል፣

ሐ/ አቅራቢው በመጫረቻ ሰነዱ ላይ ያመለከተው የዋጋ ቅናሽ ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን እና አፈጻጸማቸውን በግልጽ ያመላከተ መሆን አለበት፣

መ/ በውል አፈጻጸም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አካሄድ፣

ሠ/ የውጭ አገር ተጫራች ከጠቅላላው የውሉ መጠን ውስጥ በውጭ አገር ገንዘብ እና በብር ሊከፈለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ድርሻ ተለይቶ መገለጽ ይኖርበታል፣

ረ/ የውል አካል የሆኑ የግዥ ሰነዶች እና የተፈፃሚነት ቅድመ ወሰን፣

ሰ/ ለውል አፈጻጸም የተያዘው የውል ማስከበሪያ ሊወረስ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች፣

ሸ/ አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቶ ባያስረክብ፣ ለዛገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ፣

17.27.4. በንዑስ አንቀጽ 17.27.3.ሸ መሠረት የሚወሰደው እርምጃ በሚከተለው መሠረት መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ/ አቅራቢው ሳይፈጽም በቀረው የውሉ መጠን ላይ በየቀኑ 1% የጉዳት ካሣ እንደሚከፍል፣

ለ/ በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ ከውሉ ዋጋ 10% የሚበልጥ መሆን እንደሌለበት፣

ሐ/ የውሉ አፈጻጸም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ የበለጠ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ተቋሙ የመቀጫው መጠን 10% እስከሚሞላ ድረስ ለመጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን መሰረዝ እንደሚችል፣ የሚገልጽ አንቀጽ ውሉ እንዲያዝ መደረግ አለበት፣

17.27.5. ተቋሙ በውል ሰነድ ላይ የሚሰፍሩ ኃላፊነቶችን እና ግዴታዎችን በጥንቃቄ መመርመር ያለበት ሲሆን በተቋሙ ደረጃ ሊከናወኑ የማይችሉ ግዴታዎችን ተቀብሎ ውል መፈረም የለበትም፣

17.27.6. በንዑስ አንቀጽ 17.27.7 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ውሉን መፈረም ይኖርበታል፣

9 ላይ ከተመለከተው የገንዘብ ገደብ በላይ ለሆነ ግዥ በተቋሙ ድረ ገጽ (ዌብ ፖርታል) ላይ ማውጣት እና ለተለያዩ አገራት ኤምባሲዎች ማሳወቅ ይቻላል፣

ሐ/ የመጫረቻ ሰነድ የማቅረቢያ ጊዜው የጨረታው ማስታወቂያ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ ለማድረግና እጩ ተዳዳሪዎች የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳባቸውን ማዘጋጀት እንዲችሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.9 ላይ በተገለፀው መሠረት በቂ ጊዜ መስጠት አለበት፣

መ/ የዕቃና የአገልግሎት ፍላጎት መግለጫ የአገር ውስጥ ደረጃዎችን ያሟላ እና የአለም አቀፍ ደረጃዎችን ወይም በአለም አቀፍ ንግድ በስፋት የሚሰራበትን ደረጃ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፣

ሠ/ ዕጪ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ዋጋቸውን እንዲሁም የሚያቀርቡትን ማናቸውንም የዋስትና ሰነድ በኢትዮጵያ ብር ወይም በመጫረቻ ሰነዱ በተመለከተውና በአለም አቀፍ ንግድ በስፋት በሚሰራበት የገንዘብ ዓይነት እንዲያቀርቡ መፈቀድ አለበት፣

ረ/ የግዥ ፍላጎቱን ለማሟላት አሸናፊው የውጭ አገር ተጫራች ከአገር ውስጥ የሚጠቀመው ግብዓት በሚኖርበት ጊዜ ከአጠቃላይ የውሉ ክፍያ በብር ሊከፈል የሚገባው መጠን በዋጋ ማቅረቢያው ሰንጠረዥ ላይ መመልከት ይኖርበታል፣

ሰ/ በዓለም አቀፍ ግዥ የሚፈፀሙ ውሎች በዚህ መመሪያ የተገለጹትን ድንጋጌዎች እስካልተቃረነ ድረስ ዓለም አቀፍ ንግድ የሚሰራባቸውን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች ተመርኩዘው መፈጸም አለባቸው፣

ሸ/ በውሉ በተለየ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር በውል አፈጻጸም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ ሕግ የሚዳኙ ይሆናል።

**19. ሌሎች ዓለም አቀፍ ግዥዎች**

19.1. በግዢው ሂደት የውጭ ኩባንያዎች ካልተሳተፉበት በቂና ውጤታማ ውድድር ሊኖር አይችልም ተብሎ ሲታመን በዚህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ለብሔራዊና ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የተገለጹት ሌሎች አሰራሮች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ የሁለት ደረጃን፣ የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያን፣ የውስን ጨረታን፣ የዋጋ ማቅረቢያንና ከአንድ አቅራቢ የግዥ ዘዴን በመጠቀም ዓለም አቀፍ ግዥ መፈጸም ይችላል፣

19.2. በንዑስ አንቀጽ19.1 ላይ በተገለጸው መሠረት ከዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች በመጠቀም ዓለም አቀፍ ግዥ መፈጸፀም የሚቻለው ለየግዥ ዘዴው የተመለከተውን ሁኔታ እና የተፈቀደውን የገንዘብ መጠን መሠረት በማድረግ ይሆናል።

## 20. <u>በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች</u>

ተቋሙ በሁለት ደረጃ ግዥ ለመፈጸም የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡-

20.1. ለሚገዙት ዕቃዎችና አገልግሎቶች በቂ ዝርዝር ማዘጋጀት በተቋሙ ደረጃ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት ባህሪያቸውን ለይቶ ለማሳየት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜና የተቋሙን የግዢ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል መፍትሄ ለመፈለግ፣

20.2. ግዢው የሚካሄደው በገበያ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ለማምረት ወይም የምርምርና የልማት ወጪዎችን ለመተካት እስካልሆነ ድረስ ተቋሙ የምርርምር የሙከራ የጥናትና የልማት ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ውል መፈጸም ሲፈልግ፣

20.3. ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ በሚገዙት ዕቃዎች የግንባታ ዘርፍ ስራዎች የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ባህሪ ወይም ተፈጥሮ ግልጽ አለመሆን ምክንያት ዕጩ ተወዳዳሪዎች በጨረታው ያልቀረቡ እንደሆነ ወይም የቀረቡት ተጫራቾች ውድቅ ሲደረጉና ይህም የሆነው ተቋሙ የተሟላ ዝርዝር ማዘጋጀት ባለመቻሉ መሆኑ ሲታመን፣

20.4. የሚገዙትን ዕቃዎች የግንባታ ዘርፍ ስራዎች የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ባህሪ ወይም ተፈጥሮ አስመልክቶ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ጋር ድርድር ማደረግ ሲያስፈልግ፡፡

## 21. <u>የሁለት ደረጃ ጨረታ አፈጻጸም</u>

21.1. ጨረታው የሚከናወነው በሁለት ደረጃ የጨረታ ዘዴ ሲሆን በመጀመሪያው ዙር ዕጩ ተወዳዳሪዎች ዋጋን ያልጨመረ የመወዳደሪያ ሃሳብ እንዲያቀርቡ በግልጽ ጨረታ ጥሪ ይደረጋል፡፡ የጨረታው ሰነድ ከቴክኒክ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መግለጫዎች ጥራት ወይም የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ሌሎች ባህሪያት እንዲሁም የአቅርቦቱን ውል ቃሎችና እና ሁኔታዎች ሊይዝ የሚገባ ሲሆን አግባብነት እስካለው ድረስ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን የሞያና የቴክኒክ ችሎታ እንዲገልጹ የሚገልጽ ሊሆን ይችላል፣

21.2. ተቋሙ በመጀመሪያ ዙር የቀረቡትን የመወዳደሪያ ሃሳቦች ከግዢ ፍላጎቱ አንጻር በመገምገም ተቀባይነት ያለው የመወዳደሪያ ሃሳብ ያቀረቡ ተጫራቾችን ይለያል፡፡ በዚህን ወቅት ተቋሙ እንዳስፈላጊነቱ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ጋር ስላቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ የተወዳዳሪዎችን የጨረታ መረጃና የባለቤትነት መብት ጠብቆ ውይይት ሊያደርግ ይችላል፣

21.3. ተቋሙ በመጀመሪያው ዙር የቀሩት የመወዳደሪያ ሃሳቦች ከግዢ ፍላጎት አንጻር በመገምገም ፍላጎቱን በተሻለ ሊያሟላ የሚችል አንድ ወጥ የሆነ ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡የተዘጋጀውን ዝርዝር በመጀመሪያው ዙር ተቀባይነት ያለው የመወዳደሪያ ሃሳብ ላቀረቡ ተጫራቾች ለማሳወቅ ተጫራቾች ዋጋን ጨምሮ በተሻሻለው ዝርዝር መሰረት የመጫረቻ ሃሳባቸውን እና የጨረታ ማስከበሪያ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል፣

21.4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21.3 በተገለጸው መሰረት ተቋሙ አዲስ ዝርዝር ሲያዘጋጅ በመጀመሪያ የጨረታ ሰነድ ውስጥ ከተቀመጡት ማናቸውም የዕቃ ወይም የአገልግሎቱ የቴክኒክ ወይም የጥራት ባህሪያትና ሰነዶቹን ለመገምገምና ለማወዳደር እንዲሁም አሸናፊውን ለመምረጥ ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ ማናቸውንም ለመሰረዝ ወይም ለማሻሻል ወይም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚስማማ አዲስ ባህሪያና መስፈርቶችን መጨመር ይችላል። እንደዚህ ያሉ ማናቸውም ስረዛዎች ማሻሻያዎች ወይም ጭማሪዎች የመጨረሻ ማወዳደሪያ ሀሳብ እንዲቀርብ በሚተላለፍ ጥሪ ለተጫራቾች መገለጽ አለባቸው፣

21.5. በተሻሻለው ዝርዝር መሰረት በሁለተኛው ዙር ጨረታ መሳተፍ ያልፈለጉ ተጫራቾች እራሳቸውን ከውድድሩ ማግለል ይችላሉ፣

21.6. ተቋሙ በሁለተኛው ዙር የቀረቡ የመጫረቻ ሠነዶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.19(2) በተቀመጠው መሠረት በመገምገም አሸናፊውን መለየት ይቻላል፣

21.7. ተቋሙ በጨረታው ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ካገኘው አቅራቢ ጋር ከዋጋ በስተቀር ድርድር ሊያደርግ ይችላል።

**22. <u>በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ</u>**

22.1. በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17፣ አንቀጽ 18፣ አንቀጽ 20 እና አንቀጽ 21 የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆነው እንደግዥው ዓይነት ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት ይከተላል፣

22.2. በንዑስ አንቀጽ 22.1 የተመለከተው ቢኖርም ለሁለት ደረጃ ጨረታ የሚደረገው የጨረታ አፈጻጸም የሚከተሉትን ልዩ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል፦

22.2.1. በጨረታ ጥሪው ላይ ግዥው በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈጸም መሆኑ መገለጽ ይኖርበታል፣

22.2.2. በመጀመሪያው ዙር ጨረታ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ዋስትና እንዲያቀርቡ አይጠየቁም፣

22.2.3. በመጀመሪያ ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የተቋሙን አጠቃላይ ፍላጎት የሚገልጽ ሆኖ አላማው ከዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ሀሳቦች መሠረት ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት ስለሆነ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ መጠይቆችን እና መግለጫዎችን ማካተት ይኖርበታል፣

22.2.4. በመጀመሪያው ዙር ጨረታ ላይ የተጫራቾች መገኘት ሳያስፈልግ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበው የቴክኒክ ሀሳብ ማቅረቢያ ሰነድ በጨረታ ጥሪው በተገለጸው ሁኔታ እንዲከፈት ይደረጋል፣

22.2.5. የመጀመሪያው ዙር ግምገማ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን ሀሳብ በመመርመር ለሁለተኛው ዙር ጨረታ የሚያገለግለውን የፍላጎት መግለጫ እና በጨረታው ሊሳተፉ የሚገባቸውን ተጫራቾች መለየት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪም፡-

ሀ/ በግምገማው ወቅት እንደአስፈላጊነቱ ከሁሉም ወይም ከተወሰኑ ወይም ከአንድ ከተለየ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር ተቋሙ ውይይት ሊያደርግ ይችላል፣

ለ/ ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) ላይ በተገለፀው መሠረት የሚደረገው ውይይት ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሰጡትን ሀሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ እና በተሻለ የዳበረ ሀሳብ ለማመንጨት ያለመ ሊሆን ይገባል፣

22.2.6. በሁለተኛው ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ እስከተቻለ ድረስ ከዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 እና 18 ለግልፅ ጨረታ የተገለፀውን አሰራር መከተል ይኖርበታል፤

22.2.7. በመጀመሪያው ዙር ተቀባይነት ያገኙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሁለተኛው ዙር ውድድር እንዲሳተፉ ጥሪ የሚደረግላቸው ሲሆን፣ የጨረታ ዋስትና እንዲያቀርቡም ይደረጋል፤

22.2.8. ተቋሙ ለሁለተኛው ዙር የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መላክ ወይም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ቀርበው እንዲወስዱ ማድረግ ይኖርበታል፤

22.2.9. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 22.2.7 ላይ በተገለፀው መሠረት ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚተላለፈው ጥሪ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዱን ለመውሰድ ሊያሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች በግልፅ ሊያመለክት ይገባል።

## 23. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ

23.1. ተቋሙ ግዥው ከሚኖረው የተለየ ባህርይ አንፃር በቅድሚያ የተወዳደሪዎችን ብቃት መሠረት በማድረግ ግምገማ ማድረግ አለብኝ ብሎ ሲያምን እንደግዥው ዓይነት ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ሊያወጣ ይችላል፤

23.2. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ የሚያስፈልጋቸው ግዥዎች ከሚከተሉት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱን የሚያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡-

ሀ/ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ወይም በባህሪው ውስብስብ የሆነ የዲዛይን፣ የማምረትና የተከላ ሥራ በአንድ ድርጅት መጠናቀቅ ያለበት የግንባታ፣ የማምረቻ መሳሪያ ወይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ግዥ ሲሆን፣ ወይም

ለ/ የሚቀርበው ዕቃ ወይም መሣሪያ ጥራትና ጠቀሜታ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው እና የተከላ አገልግሎትን ያካተተ ሲሆን፣ ወይም

ሐ/ የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ግዥ በመሆኑ ብቃታቸው በቅድመ ብቃት ምዘና የሚረጋገጥ ተጫራቾች ብቻ በውድድሩ ተካፋይ መሆን እንደሚገባቸው ሲታመንበት፣

23.3. ጨረታው የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ጥሪ መሆኑ በማስታወቂያው ላይ መገለጽ ይኖርበታል፤

23.4. የቅድመ ብቃት ግምገማ ለማድረግ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የቅደመ ብቃት ጨረታ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን የቅድመ ብቃት ጨረታ መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት በማድረግ ይሆናል። የቅድመ ብቃት መምረጫ መስፈርት እንደግዥው ባህርይና ዓይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ተወዳዳሪ ድርጅቶቹ እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት ማስረጃ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማካተት ይኖርበታል፣

ሀ/ በተመሳሳይ ሥራ ወይም ዕቃ ማምረት ላይ ድርጅቱ ያለው ልምድ፣

ለ/ ድርጅቱ ሥራውን ለማከናወን ወይም ዕቃውን ለማምረት የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል፣ ማሽነሪ የማምረቻ መሣሪያ ብዛት እና የተሟላ እንፍራስትራክቸር ያለው መሆኑን፣

ሐ/ ድርጅቱ አሁን በመሥራት ላይ ያለው የግንባታ ሥራ ወይም በማምረት ላይ ያለው ዕቃ ብዛት ወይም መጠን፣

መ/ ድርጅቱ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ የሚያስችል በቂ የገንዘብ አቅም እና መልካም ዝና ያለው መሆኑን፣

23.5. የተጫራቾች ግምገማ የሚከናወነው ለቅድመ ብቃት ማረጋገጫ በተቋሙ የተዘጋጀውን መስፈርት መሠረት በማድረግ ይሆናል፣

23.6. ለቅድመ ብቃት ውድድሩ ያመለከቱ ተጫራቾች በሙሉ የግምገማ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ ምንም ዓይነት የቁጥር ገደብ ሳይደረግ በሚቀጥለው ውድድር እንዲሳተፉ መደረግ አለበት፤

23.7. ተቋሙ በቅደመ ብቃት ውድድር የሚሳተፉ ድርጅቶች በሽርክና ወይም በጋራ መወዳደር እንዲችሉ ሊፈቅድ ይችላል። ሆኖም የቅደመ ብቃት ውድድሩን በግል ያለፉ ተወዳዳሪዎች በግዥው ሂደት የሚኖራቸውን ውድድር እንደማያጠብ በመ/ቤቱ ካልታመነ በስተቀር በጋራ ወይም በሽርክና የመጫረቻ ሰነዱን እንዲያቀርቡ መፈቀድ የለበትም፣

23.8. በንዑስ አንቀጽ 23.6 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ወይም በሽርክና ለቅድመ ብቃቱ ውድድር ቀርበው ይህንኑ መሠረት በማድረግ በተካሄደ ግመገማ ለሚቀጥለው ጨረታ ያለፉና የተመረጡ ተጫራቾች በጨረታው በግል እንዲወዳደሩ አይፈቀድላቸውም፣

23.9. የቅድመ ብቃቱ ግምገማ ውጤት እንደታወቀና በመ/ቤቱ ተቀባይነት እንዳገኘ ውጤቱ በጨረታው እንዲሳተፉ ለተመረጡትና ላልተመረጡት ተጫራቾች በእኩል ሁኔታ ሊገለጽላቸው ይገባል።

23.10. አንድ ተጫራች በጨረታው ግምገማ አሸናፊ ለመሆን ቢችልም ለቅድመ ብቃት ውድድር የሰጠው መረጃ የተሳሳተ ከሆነ ወይም በቅድመ ብቃት ውድድሩ ወቅት የነበረው ብቃት

ባለመኖሩ ውሉን በሚጠበቅበት ሁኔታ ለመፈጸም አለመቻሉ በበቂ ሁኔታ ከተረጋገጠ ተቋሙ ድርጅቱ ውሉን እንዲፈርም ላይፈቅድ ይችላል፣

23.11. በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተመለከተውን ሥርዓት በመከተል የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ውድድሩ ተቀባይነት ላገኙት ተጫራቾች በየአድራሻቸው እንዲላክላቸው ወይም ከተቋሙ ቀርበው እንዲወስዱ የሚደረግ ሲሆን፣ ቀሪው የግዥ አፈፃፀም ሥርዓት በዚህ መመሪያ የተደነገገውን አሰራር ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

**24. <u>በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ</u>**

24.1. ተቋሙ የምክር አገልግሎት ግዥን የመወዳደሪያ ሀሳብ በመጠየቅ መፈፀም የሚኖርበት ሲሆንና የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ከብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺህ) በላይ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25 መሠረት የፍላጎት መጠየቂያ ጥሪ በማካሄድ መፈጸም አለበት፣

24.2. የመወዳደሪያ ሀሳብ ለማቅረብ የሚጋበዙት አማካሪዎች አመራረጥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ይፈፀማል፡-

ሀ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25 መሠረት በወጣው የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጥሪ መሠረት ፍላጎታቸውን ከገለፁ አማካሪዎች ውስጥ የተሻለ ብቃት ያላቸውን በመምረጥ፣

ለ/ የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ አማካሪዎች ውስን ሲሆኑ እነዚህን አማካሪዎች በሙሉ በመጋበዝ፣

ሐ/ የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ከብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺህ) በታች ሲሆን ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ በመምረጥ፣

24.3. የመወዳደሪያ ሀሳብ ለማቅረብ የሚጋበዙት አማካሪዎች ቁጥር እስከተቻለ ድረስ ከሦስት ያላነሰ እና ከሰባት ያልበለጠ መሆን ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ/ የተቋሙን ስምና አድራሻ፣

ለ/ የሚፈለገው አገልግሎት የሚያሳይ የማጣቀሻ ፅሁፍ፣

ሐ/የጥቅም ግጭትን ሊያስከትል የሚችል የምክር አገልግሎት በሚሆንበት ጊዜ ለዚህ ዓይነቱ ውድድር የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳደሪዎች ከምክር አገልግሎቱ በማስከተል ከምክር አገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ከሚከናወኑ የዕቃ አቅርቦትና የግንባታ ሥራዎች ራሳቸውን ማግለል የሚገባቸው መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ፣

መ/ የመወዳደሪያ ሀሳቦችን መገምገሚያ መስፈርቶችን፣ ለዋጋና ለሌሎች መስፈርቶች የሚሰጠውን ነጥብ፣ በመስፈርቶቹ የመወዳደሪያ ሀሳብ በሚገመገምበት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉበትን አኳኋን፣

ሠ/ የመወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርብበትን ቦታና የመጨረሻ ቀን፣

24.4. ተቋሙ የመወዳደሪያ ሀሳበ እንዲያቀርቡ ለተመረጡ አማካሪዎች የጥሪ ደብዳቤ በተመሳሳይ ጊዜ በአድራሻቸው መላክ አለበት፡፡ ለግዥው የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ያለ ክፍያ ሊሰጥ እንደሚገባ ተቋሙ ሲያመን ከጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ጋር የጨረታ ሰነዱን ሊልክላቸው ይችላል፣

24.5. ለመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ተቋሙ ያዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ በመጠቀም እንዲሁም በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ የተቀመጠውን ሥርዓት በመከተል የሚዘጋጅ መሆን ይኖርበታል፣

24.6. ተቋሙ ከተመረጠው አማካሪ ጋር የሚያደርገው ድርድር መሠረታዊውን የጨረታ ይዘትና የሥራ ጥራት የማይቀይር ሆኖ ስለስራው ይዘት፣ ስለአሰራር ዘዴው፣ በሥራው ስለሚሰማራው የሰው ኃይል እና መሣሪያ፣ ስለሪፖርት አቀራረብ እና ይዘት በመሳሰሉት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፣

24.7. በንዑስ አንቀጽ 24.6 መሠረት የሚደረገው ስምምነት የተቋሙን ጥቅም የሚጎዳ ወይም ለተመረጠው አማካሪ ከሌሎች ተጫራቾች አንፃር ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚሰጠው መሆን የለበትም፣

24.8. በንዑስ አንቀጽ 24.9ሥር የተገለጹት የመረጣ ዘዴዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች የጨረታ አፈጻጸም ሂደቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17ሥር የተገለጹትን የግልጽ ጨረታ አሰራሮች በመከተል የሚፈጸሙ ይሆናል፣

24.9. ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ 24 (10፣ 12፣ 13፣ 14 እና 15) በተገለጹት የመምረጫ ዘዴዎች ለሚፈጸሙ ግዥዎች የሚቀርበው የመጫረቻ ሰነድ በቴክኒክና በዋጋ ማቅረቢያ ተለይቶ በሁለት ኤንቬሎፕ ታሽጎ መቅረብ የሚኖርበት ሲሆን ለምክር አገልግሎቱ የሚዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት እና የሚደረገው ግምገማ የሚከተለውን አሰራር ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

24.10. <u>በጥራት እና በዋጋ ላይ የተመሰረተ መረጣ</u>

24.10.1. ተቋሙ ለምክር አገለግሎት የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጅበት፣ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርበውን እያንዳንዱን የቴክኒክ ሃሳብ በሚገመግምበት እና በሚያወዳድርበት ወቅት የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ/ ከሚሰጠው ሥራ ጋር በተገናኘ አማካሪው ያለውን ልምድ፣

ለ/ በሥራ ላይ እንዲውል የቀረበውን የጥናት ዘዴ ደረጃ፣

ሐ/ ምክሩ ለተቋሙ የሚያስገኘውን እውቀት፣

መ/ የውጭ ተወዳዳሪዎች በሚያቀርቧቸው የመወዳደሪያ ሃሳቦች ኢትዮጵያውያን ዜጎች በምክር ሥራው ሂደት በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ፣

24.10.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 24.10.1 ላይ ለተመለከቱት መስፈርቶች ተቋሙ እንደሚገባው የምክር አገልግሎት ዓይነት ለእያንዳንዱ መስፈርት ከዚህ በታች በተገለጸው መሠረት ነጥብ መስጠት ይኖርበታል፣

ሀ/ የአማካሪው ልዩ ልምድ ............................................ ከ5 እስከ 10 ነጥብ

ለ/ ሥራ ላይ ይውላል ተብሎ የቀረበው የምክር ዘዴ..................ከ20 እስከ 50 ነጥብ

ሐ/ ዕውቀት የማሸጋገር ችሎታ.......................................... ከ5 እስከ 10 ነጥብ

መ/ በምክር አገልግሎት ለሚሳተፉ ቁልፍባለሙያዎች......... ከ30 እስከ 60 ነጥብ

ሠ/ የኢትዮጵያውን ተሳትፎ............................................. ከ5 እስከ 10 ነጥብ

24.10.3. በቴክኒክ ብቃት 70% (ሰባ በመቶ) በታች ያገኙ ተወዳዳሪዎች ውድቅ ተደርገው 70% እና ከዚያ በላይ የሚያገኙት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት ይከፈታል፣

24.10.4. በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾች የዋጋ ፖስታ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት፣

24.10.5. የምክር አገልግሎቱ የሚገኘው ከውጭ አማካሪዎች ካልሆነ በስተቀር የአገር ውስጥ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ ለግምገማ ሲባል የአገር ውስጥ ታክስን ይጨምራል። ከዚህ በላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገር ውስጥ እና የውጭ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ የመጓጓዣ፣ የትርጉም፣ የጽሕፈት ሥራ ወጪን እና የመሳሰሉትን ሊጨምር ይችላል፣

24.10.6. ዝቅተኛ የመጫረቻ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ ለዋጋ ሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ከሆነ፣ በተነፃፃሪ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ አነስተኛ ነጥብ ይሰጣል ሌሎች ተወዳዳሪዎችም የሚያገኙት ነጥብ ባቀረቡት ዋጋ ላይ በመመስረት ተሰልቶ የሚወሰን ይሆናል፣

24.10.7. የቴክኒክ ግምገማ የነጥብ ድርሻ 80% (ሰማንያ በመቶ)፣ የዋጋ ግምገማ የነጥብ ድርሻ ደግሞ 20% (ሃያ በመቶ) ይሆናል፣

24.10.8. ለቴክኒክ ብቃት ደረጃ እና ለዋጋ የተሰጡትን ነጥቦች በማዳመር በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ተወዳዳሪ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፣

24.10.9. በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈጸም የምክር አገልግሎት ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 የተገለጸውን የግዥ አፈጻጸም ሂደት በተጨማሪነት መሠረት ማድረግ ይኖርበታል።

## 24.11. በሚከናወነው የሥራ ጥራት ላይ የተመሰረተ መረጣ

24.11.1. በሥራ ጥራት ላይ የተመሰረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አገልግሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ይሆናል፡-

ሀ/ የምክር አገልግሎቱ ውስብስብና የተለየ የሙያ ብቃት የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚሁ ግዥ የተሟላ ማጣቀሻ ሰነድ ወይም ቢጋር ማዘጋጀት የማይቻል ሲሆን ወይም ከአማካሪው የሚገኘውን የምክር አገልግሎት ዓይነት ለይቶ ማወቅ የማይቻል ሲሆን ወይም አማካሪው የራሱን የፈጠራ ችሎታ ተጠቅሞ የመወዳደሪያ ሃሳብ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን፣

ለ/ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን አማካሪዎች ማግኘት አስፈላጊ በሚሆንባቸው እና የወደፊት ውጤታቸው አሳሳቢ የሚሆን ከፍተኛ ጉዳዮች ሲሆኑ፣

ሐ/ የምክር አገልግሎቱ በተለያዩ አማራጭ መንገዶች ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ ምክንያት የሚቀርቡትን ሃሳቦች በተመሳሳይ ሁኔታ ማወዳደር አስቸጋሪ እንደሚሆን ሲታመን፣

24.11.2. የቴክኒክ ሃሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ ይደረጋል፣

24.11.3. በቴክኒክ ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ያገኘው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፣

24.11.4. በንዑስ አንቀጽ 24.11.3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ከተቋሙ የመክፈል አቅም በላይ ከሆነና በቴክኒክ ግምገማው ውጤት ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ከተቋሙ የመክፈል አቅም ጋር የሚመጣጠን ከሆነ ግዥውን ሁለተኛ ከወጣው ተጫራች መፈፀም ይቻላል፣

24.11.5. በጨረታ አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር የውል ስምምነት እንደተፈረመ የሌሎች የተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ሳይከፈት ለተጫራቾች ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

24.11.6. ከላይ በዚህ አንቀጽ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጥበቃ አገልግሎትን በሚመለከት ኤጀንሲው በግልጽ ጨረታ ከተወዳደሩት ለመስሪያ ቤቱ ሰነድ ደህንነት አንጻር የተቋሙን ዋና ዳይሬክተር በማስፈቀድ አስተማማኝ የጥበቃ አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅት ጋር ስምምነት ማድረግ ይችላል፡፡

## 24.12. በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ

ሀ/ በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚፈለገው የምክር አገልግሎት ውስብስብነት የሌለው፣ በትክክል ሊገለጽ የሚችል ሲሆን እና ለዚሁ ተግባር የተፈቀደው በጀት ጣሪያ ያለው ከሆነ ነው፣

ለ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.18.3 ‹‹ሀ›› መሠረት የቴክኒክ ሃሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ ይደረጋል፣

ሐ/ የቴክኒክ ግምገማው በንዑስ አንቀጽ 24.10.1፣ 24.10.3 እና 24.10.4 ላይ የተመለከቱትን ሥርዓቶች ተከትሎ የሚፈጸም ይሆናል፣

መ/ በቴክኒክ ግምገማው ተፈላጊውን መስፈርት ያሟሉ ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈት ይደረጋል፡፡ ለጨረታው በእያንዳንዱ ተጫራች የቀረበውን ዋጋ በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት፣

ሠ/ ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ያቀረቡ ተጫራቾች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

ረ/ ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ዋጋ ያቀረበና በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘ ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል እንደአስፈላጊነቱም ዋጋን ያልጨመረ ድርድር ሊደረግ ይችላል፣

## 24.12. በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሰረተ መረጣ

24.12.1. በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሲውል የሚችለው የሚገዛው የምክር አገልግሎት፣የግንባታ ግዢ እንዲሁም የባለሙያውን ልዩ ችሎታ የማይጠይቅ፣ ውስብስብ ያልሆነና ስታንዳርድ ያለው ወይም በተመሳሳይ ወጥ በሆነ አሰራር ሊከናወን የሚችል ሲሆን ነው፣

24.12.2. ተቋሙ በዚህ የመረጣ ዘዴ ተጫራቾችን ለመገምገም ሲፈልግ ዝቅተኛውን የቴክኒክ መመዘኛ ነጥብ መጠን (80% እና ከዚያ በላይ) በመወሰን ከአቅራቢዎች ዝርዝር ለተመረጡ ተጫራቾች በሚሰጠው የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ሰነድ ላይ ይህንኑ ነጥብ በግልጽ ማመልከት አለበት፣

24.12.3. የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ በማድረግ የቴክኒክ ግምገማ መከናወን ይኖርበታል፡፡በግምገማው ውጤት ለቴክኒክ ብቃት የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት ያላሟሉ ተወዳዳሪዎች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

24.12.4. በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾች የዋጋ ፖስታ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት፣

24.12.5. በቴክኒክ ግምገማ ውጤታቸው ለዋጋ ውድድር ያለፉት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈት ይደረጋል፡፡ ለጨረታው በተጫራቾች የቀረበው

ዋጋ በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁት መደረግ አለበት፣

24.12.6. በቴክኒክ ግምገማ ለብቃት ማረጋገጫ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት ካሟሉት ተወዳዳሪዎች መካከል አነስተኛ ዋጋ የሰጠው ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል።

24.13. <u>በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሰረተ መረጣ፡</u>

ሀ/ በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሰረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ለአማካሪው የሚሰጠው ሥራ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት የመወዳደሪያ ሀሳቦችን ለማዘጋጀት እና ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜና ወጪ ከሥራው ጋር የማይመጣጠን ሲሆን ነው፤

ለ/ ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው የምክር አገልግሎቱ ወጪ ከብር 50 ሺህ የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ነው፣

ሐ/ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚዘጋጀው ማጣቀሻ /ቢ.ጋር/ አማካሪው ያለውን የሥራ ልምድና የብቃት ደረጃ እንዲገልጽ የሚጠይቅ መሆን አለበት፣

መ/ ከአቅራቢዎች ዝርዝር ወይም ተቋሙ ያለውን መረጃ በመጠቀም በውድድሩ እንዲሳተፉ በመረጣቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በሚከናወን ግምገማ የተሻለ ሆኖ የተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ የቴክኒክና የዋጋ ማቅረቢያ ሀሳቡን በአንድ ላይ እንዲያቀርብ በማድረግና በመደራደር በሚደረሰበት ስምምነት መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

24.14. <u>አንድ አማካሪ የሚመረጥበት ሁኔታ</u>

ተቋሙ የምክር አገልግሎት ግዢን ከአንድ አማካሪ ለመፈጸም የሚችለው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 28 (ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ) የተገለጹት ሁኔታዎች ሲረጋገጥ ብቻ ነው

24.15. <u>በቂ ጊዜ ስለመስጠት</u>

ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመወዳደሪያ ሃሳብ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጋቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው የሚገባ ሲሆን የጊዜ ገደቡ በዚህ መመሪያ አባሪ 3 ላይ በተመለከተው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

24.16. ተቋሙ አንደኛ ሆኖ ከተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመወዳደሪያ ሀሳብ ውስጥ የተመለከተውን የአገልግሎቱን ባህሪ፣ መጠንና፣ አደረጃጀት የሚመለከት ድርድር ማድረግ ይችላል፣

24.17. ተቋሙ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል በአሸናፊነት ሊመርጥ የሚችለው በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ በተመለከተው የመገምገሚያ መስፈርት መሠረት በሚካሄደው ግምገማ ያቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖ የተገኘውን ዕጩ ተወዳዳሪ ነው

## 25. የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ

25.1. ተቋሙ የሚገዛው የምክር አገልግሎት ግምታዊ ዋጋ ከብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺህ) የሚበልጥ ሲሆን በምክር አገልግሎቱ አቅርቦት ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸውን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በመጋበዝ ጥሪ ማድረግ ይኖርበታል፤

ሀ/ ለፍላጎት መግለጫ የሚደረገው ጥሪ እንደሁኔታው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.2 ወይም 18.5 (ሀ) እና (ለ) ላይ የተመለከተውን ተከትሎ የሚፈጸም ሲሆን በተጨማሪነት ጥሪው የተደረገው ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች ፍላጎታቸውን እንዲገልጹ መሆኑን ማሳወቅ ይኖርበታል፣

ለ/ የፍላጎት መግለጫ ጥሪው የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት ዓይነት፣ የሚጠበቀውን ውጤት፣ ጊዜውን፣ አማካሪው ሊኖረው የሚገባውን ብቃት፣ የሥራ ልምድ እና የመሳሰሉትን የያዘ እና ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያቀርቡት የሚገባውን መረጃ ዝርዝር እና የሚያቀርቡበትን ቦታና ጊዜ የሚገልጽ መሆን አለበት፣

ሐ/ ፍላጎታቸውን ያሳወቁ ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት መረጃ ተገምግሞ የተፈለገውን የምክር አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ ብቃት ያላቸው በቅደም ተከተላቸው መሠረት እስከተቻለ ድረስ ከሦስት ያላነሱ እና ከሰባት ያልበለጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመርጠው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24መሠረት የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን እንዲያቀረቡ መደረግ ይኖርበታል፣

## 26. የውስን ጨረታ ግዥ አፈጻጸም፣

የውስን ጨረታ ከግልጽ ጨረታ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተቋሙ የውስን ጨረታ ግዥን መፈጸም የሚችለው የሚከተሉትን ልዩ አሰራሮች በመከተል ይሆናል

26.1. ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ እንዲሁም የግዢው መጠን በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን በውስን ጨረታ የሚፈጸም ግዥ ወይም በተደጋጋሚ ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪ ያልተገኘ ሲሆን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 እና 18 ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ጨረታ የተፈቀደውን ዝርዝር የአፈጻጸም ሥርዓት ተከትሎ የሚከናወን ይሆናል፣

26.2. በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ይከናወናል፣

26.2.1. የጨረታ ጥሪው በቀጥታ ለዕጩ ተወዳዳሪው በአድራሻው የሚላክ ሆኖ፡-

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ፣ የምክር ወይም ተፈላጊ ሌላ አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን የጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ለሁሉም አቅራቢዎች በአድራሻቸው ተዘጋጅቶ መላክ ይኖርበታል፣

ለ/ በጨረታው ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆንም ግዥው በንዑስ አንቀጽ 26.3በተቀመጠው የገንዘብ መጠን ገደብ ውስጥ ከሆነ ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች መመረጥ ይኖርባቸዋል፣

26.2.2. ተቋሙ በውስን ጨረታ የተጋበዙ ተጫራቾችን ማንነት ለሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሳወቅ የለበትም፣

26.2.3. በውስን ጨረታ የተጋበዙት ተጫራቾች በሙሉ ከጨረታ መቆያ ጊዜ ገደቡ በፊት የመጫረቻ ሰነዳቸውን ካቀረቡ የጊዜ ገደቡ እስከሚጠናቀቅ መጠበቅ ሳያስፈልግ ተቋሙ አዲሱን የጨረታ መክፈቻ ጊዜ ለሁሉም ተጫራቾች በማሳወቅ እና እንዲገኙ በመጋበዝ ጨረታው እንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል፣

26.2.4. ተቋሙ ለግዥው ለተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍያ መጠየቅ አያስፈልግም ብሎ ሲያምን ከጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ጋር የጨረታ ሰነዱን አያይዞ ሊልክ ይችላል፣

26.2.5. ተቋሙ በውስን ጨረታ ግዥ የሚፈጽመው ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ሲሆን የጨረታ ማስከበሪያ መጠየቅ ቁጥራቸው ውስን የሆኑትን ተጫራቾች በጨረታው ውድድር እንዳይሳተፉ ይደረጋል ብሎ ሲያምን የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ ሳያስፈልግ ዕጩ ተጫራቾች በዚህ መመሪያ አባሪ 5 የተመለከተውን የስምምነት ማረጋገጫ ፎርመው ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይችላል፣

26.3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 26.2 የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የግዥው መጠን በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ መጠቀም የሚቻለው የሚገዛው ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም አገልግሎተ ጠቅላላ ዋጋ ከሚከተለው የማይበልጥ ሲሆን ብቻ ነው፣

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዥ ........................ ከብር 6,000,000.00

ለ/ ለዕቃ ግዥ................................................ ከብር 1,500,000.00

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ ............................. ከብር 900,000.00

መ/ ለአገልግሎት ግዥ....................................... ከብር 1,200,000.00

ሠ/ የግንባታ ዕቃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት የተቋሙ በሚሆንበት የግንባታ ሥራ ውል ለግንባታ ዕቃዎች ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው ከላይ ለግንባታ ሥራ ግዥ የተፈቀደው የገንዘብ ጣሪያ ይሆናል፣

26.4. በተደጋጋሚ ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪ ያልተገኘ ሲሆን ግዥን በውስን ጨረታ ለመፈጸም የሚከተሉት ሁኔታዎች በቅደም ተከተል መሟላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፦

ሀ/ ግዥውን ለመፈጸም የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለሁለት ጊዜያት ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ ወይም በድጋሚ በወጣ ጨረታ የቀረቡት ተጫራቾች በተቋሙ የተዘጋጀውን የቴክኒክ ፍላጎት ያላሟሉ መሆኑን፣

ለ/ ተቋሙ የጨረታ ጥሪውን፣የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ መጠን እና ዓይነት እንዲሁም ሌላ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለመሳተፍ እንዳይችሉ የሚገድቡ ሁኔታዎች በአሰራሩ ወይም በጨረታ ማስታወቂያው እና ሰነዱ ውስጥ አለመኖራቸውን፣

ሐ/ ተቋሙ በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ ግዥው ቢጋበዙ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲያምን፣

መ/ እስከተቻለ ድረስ በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በግልጽ ጨረታ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ያልሁኑበትን ምክንያት በማጣራት ምክንያታቸው ሕጋዊ እና የተቋሙን ጥቅም ለመጉዳት ያለመ አለመሆኑን ማረጋገጥ ሲቻል፣

26.5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 26.1፣ 26.2፣ 26.3 እና 26.4 ሥር የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ17 ላይ የተመለከተውን የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የአፈፃፀም ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፣

26.6. በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ የሚፈጸመው የውስን ጨረታ የምክር አገልግሎቶች ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24 ላይ የተገለጹትን ተጨማሪ አሰራሮች ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል።

**27. <u>በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ፣</u>**

27.1. በዚህ መመሪያ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ እና የሚገዙትም ለገበያ የተዘጋጁ ዕቃዎች ወይም የታወቀ ገበያ ያላቸው የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፣ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ሲሆን በተቋሙ አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም አለባቸው። ሆኖም ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ እና ዋጋቸው ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ 27.2 በተመለከተው ገደብ ውስጥ ይሆናል ተብሎ የሚገመቱ ግዥዎችን በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ለመፈጸም ይችላሉ፣

27.2. ከሚከተሉት የገንዘብ መጠኖች የማይበልጡ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸሙ ግዥዎችን ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ መቅረብ ሳያስፈልግ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚሰጠው ውክልና መሠረት እንዲፀድቁ በማድረግ ግዥ መፈጸም ይችላል፣

ሀ/ ለግንባታ ሥራ ግዥ ................................ እስከ ብር500,000.00

ለ/ ለዕቃ ግዥ ........................................ እስከ ብር 200,000.00

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ.......................... እስከ ብር 120,000.00

መ/ ለአገልግሎት ግዥ................................ እስከ ብር 150,000.00

ሠ/ የግንባታ ዕቃዎች የማቅረብ ኃላፊነት የተቋሙ በሚሆንበት ጊዜ ለግንባታ ዕቃዎች ግዥ ተግባራዊ የሚሆነው የግንባታ ስራ ግዥ የተፈቀደው የገንዘብ መጠን ይሆናል፣

27.3. ተቋሙ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈጽም በውድድሩ ተሳታፊ የሚሆኑት አቅራቢዎች ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የሚመርጥ ሆኖ እስከተቻለ ድረስ ቁጥራቸው ከሶስት ማነስ አይኖርበትም። ውድድሩንም ፍትሐዊ ለማድረግ አፈጻጸሙ የሚከተለውን አሰራር መከተል ይኖርበታል፣

ሀ/ ተቋሙ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡት ሁሉም ተሳታፊዎች በዙር የመወዳደር ዕድል ማግኘታቸውን እና ለተቋሙ ጠቃሚ የሆነ የተለየ ሁኔታ መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር አንድ ወይም የተወሰኑ አቅራቢዎችን ብቻ በተደጋጋሚ መጋበዝ አይኖርባቸውም፣

ለ/ ተቋሙ የዋጋ ማቅረቢያ በመስጠት እና ዋጋ በመወሰን ሂደት ሊፈጠር የሚችል መመሳጠርን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር መከተል እና ከታች በንዑስ አንቀጽ 27.7 በተመለከተው መሠረት በየጊዜው ጥብቅ የዋጋ ቁጥጥር ማድረግ ይገባዋል፣

27.4. እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት አንድ የመወዳደሪያ ዋጋ ብቻ ሆኖ ያቀረበውን ዋጋም መለወጥ አይፈቀድለትም። ዕጩ ተወዳዳሪው በሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ ላይ በተቋሙ እና በዕጩ ተወዳዳሪው መካከል ምንም ዓይነት ድርድር ሊደረግ አይችልም፣

27.5. ተቀራራቢ የጥራት ደረጃ ያላቸውና በተቋሙ የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ አቅርቦቶችን በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች አሸናፊ አድርጎ መምረጥ ያስፈልጋል፣

27.6. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጸም ግዥ የሚደረገው የዋጋ ውድድር ታክስን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፣

27.7. ተቋሙ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድረ-ገጽ የሚያወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር በግዥ ሥራ ክፍሉ የሚካሄድ የገበያ ጥናትን በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማመን ይኖርበታል፣

27.8. ተቋሙ የዋጋ ማቅረቢያ በመሰብሰብ ለሚፈጽሙት ማናቸውም ግዥ እስከተቻለ ድረስ በተቋሙየሚዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መጠቀም ይኖርባቸዋል፣

27.9. ተቋሙ ከዚህ በታች የተገለጹት ሁኔታዎች መሟላታቸው ተረጋግጦ የዋጋ መጠየቂያ ለመላክና የዋጋ ማቅረቢያ ለመቀበል የሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፣

ሀ/ የሚዘረጋው የኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ መረጃ ሊደርሰው ከሚገባው አካል እና መረጃው ሊታወቅ ከሚገባው ቀን እና ሰዓት ውጪ በማንኛውም አካል ሊታይ እንደማይችል የሚያረጋግጥ የተሟላ የመረጃ ደህንነት ሲኖረው ፣

ለ/ በዋጋ ማቅረቢያ ሊወዳደሩ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሙሉ በዘዴው ለመጠቀም የሚያስችል ዕውቀት እና ዝግጁነት ያላቸው መሆኑ ሲያረጋግጥ፣

ሐ/ ከላይ በፊደል ተራ ‹‹ለ›› የተቀመጠው ቢኖርም በኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ ዋጋ መስጠት የማይችሉ በተለመደው አሰራር በፖስታ ዋጋ ሊሰጡ እንዲችሉ አማራጭ የተዘጋጀላቸው ሲሆን፣

27.10. በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ለሚከናወኑ ግዥዎች አቅራቢው የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ (ፕሮፎርማ) እና ተቋሙ ለአቅራቢው የግዥ ትእዛዝ የሰጠበት ደብዳቤ እንደውል ስለሚቆጠሩ ተጨማሪ ውል መዋዋል አስፈላጊ አይሆንም፣

27.11. በዚህ አንቀጽ ለመጠቀም ሲባል ተቋሙ በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍሎ መግዛት አይኖርበትም፣

27.12. በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዥ ለዕጩ ተወዳሪዎች የሚላከው መጠየቂያ የሚቀርበውን ዕቃ ወይም የግንባታ ስራ ወይም ምክር ወይም ሌላ አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት የማቅረቢያ የውል ቃሎች እና ጊዜ እንዲሁም ሌሎች የተቋሙ ፍላጎቶች ዝርዝር የሚገልጽ መሆን አለበት፣

27.13. ተቋሙ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ለማዘጋጀት የሚያስችል በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል።

## *28. ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ*

ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈጸም የሚሰጠው ውሣኔ የሚከተሉትን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣

28.1. በዚህ መመሪያ የተገለጸው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፤

ሀ/ ዕቃው የግንባታ ዘርፍ ስራው የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ/ ለዕቃዎች ወይም ለተገጣሚዎች ተጨማሪ መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት ሲፈለግ ወይም ከሌላ አቅራቢ ግዥው ቢፈጸም የሚገዛው ተገጣሚ መሳሪያ ወይም አገልግሎት ተቋሙ ከሚጠቀምበት መሳሪያ ወይም አገልግሎት የማይጣጣም ሆኖ መገኘቱ ከመጀመሪያው አቅራቢ መለዋወጫዎችን አገልግሎቶችን ወይም ተገጣሚዎችን መግዛት አስፈላጊ ሲሆን፣

ሐ/ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በመጀመሪያ ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ስራዎች ማሰራት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነና በቴክኒክ ወይም በኢኮኖሚ

ምክንያቶች እነዚህን ተጨማሪ የግንባታ ስራዎች ከመጀመሪያው ውል ነጥሎ ማሰራት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፣

መ/ የመጀመሪያው የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ውል አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ በመጠናቀቁ እና ውሉ እንዲራዘም ማድረግ ቁጠባንና ቅልጥፍናን የሚያስገኝ መሆኑ መረጋገጡ አገልግሎቱን መቀጠል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ሠ/ በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ከባድ ችግር የሚፈጥርና በተቋሙ ስራ አፈጻጸም ላይ ጉዳትን የሚያስከትል በመሆኑ ምክንያት በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የተፈቀደ ግዥ፣

ረ/ ተቋሙ ለሚኖረው የተለየ የግዥ ፍላጎት ማሟያ ከገበያ የለቀማ ግዢ መፈጸም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፣

ሰ/ ለአጭር ጊዜ የሚቆይና ለተቋሙ ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ የሚፈጸም የዕቃ ግዥ ሲሆን ነው፡፡ይህ ንዑስ አንቀጽ የሚያገለግለው በመደበኛ አቅራቢነት ያልተሰማሩ ሰዎች ለሚሸጧቸው ዕቃዎች ሲሆን በመደበኛ አቅራቢነት ከተሰማሩ አቅራቢዎች አዘውትሮ የሚፈጸሙ ግዥዎችን አይጨምርም ፣

28.2. አሸናፊው ከተመረጠ በኃላ በተፈረመው ውል የመጀመሪያው ግዥ የተከናወነባቸው አይነት ተመሳሳይ ስራዎች ወይም አቅርቦቶች በድጋሚ እንዲቀርቡ ወይም እንዲሰሩ ማድረግ በማስፈለጉ በዚህ መመሪያ 28.1 (መ እና ሠ) በተገለጸው መሰረት በዓይነትና በዋጋ አንድ የሆኑ ዕቃዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን እና የምክር አገልግሎቶችን ቀደም ሲል እነዚህን ካቀረበ ተጫራች መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ሲታመንበት ከአቅራቢው ፈቃደኛነት ላይ በመመስረትና የሚከተሉትን አሰራሮች በመከተል ተጨማሪ ግዥ ለመፈጸም ይቻላል፤

ሀ/ በተጨማሪነት የሚታዘዘው ዕቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም የምክር አገልግሎት ግዥ መጠን ቀደም ሲል ከተገዛው ከ25% (ሃያ አምስት በመቶ) መብለጥ የለበትም፣ የቤት ኪራይ ሲሆን የውሉን ጊዜ እስከ 50% ማራዘም ይቻላል፡፡

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ተጨማሪ ግዥ ለማዘዝ የቀድሞው ግዥ ውል ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ወይም ውሉ ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ በሚቀጥሉት 6 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ የግዥ ትዕዛዙ መተላለፍ ይኖርበታል፣

ሐ/ በዚህ መሠረት ለሚፈፀም ግዥ በመጀመሪያው ውል ከነበረው የነጠላ ዋጋ የበለጠ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ አይፈቀድም፣

መ/ ከላይ በፊደል ተራ (ሐ) የተቀመጠው ቢኖርም የመጀመሪያው ውል የዋጋ ማስተካከያ የሚፈቅድ ከሆነ እና የዋጋ ማስተካከያ ይደረግባቸው የተባሉ ግብዓቶች በተጨማሪው ውል ውስጥ የሚገኙ ከሆነ በመጀመሪያው ውል ላይ በተመለከተው የዋጋ ማስተካከያ አሰራርና ስሌት መሠረት የዋጋ ማስተካከያ በማድረግ ግዥው ሊፈጸም ይችላል፣

28.3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 28.1(ለ) በተገለጸው መሠረት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን አረጋግጠው ያልታሰቡና በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎችን ማሰራት ይችላሉ፣

ሀ/ ተቋሙ በተጨማሪነት እንዲሰሩ የታሰቡት ሥራዎች በመጀመሪያው ውል ውስጥ መካተት ይገባቸው የነበሩ እና ሥራዎቹን ነጣጥሎ ማሰራት ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ወይም የተቋሙን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፣

ለ/ በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ሥራ የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% (ሰላሳ በመቶ) የበለጠ መሆን የለበትም፣

ሐ/ በተጨማሪነት የሚታዘዙት የግንባታ ሥራዎች የነጠላ ዋጋ በመጀመሪያው ውል ውስጥ ሊገኝ የሚችል ከሆነ የተጨማሪው ሥራ በመጀመሪያው ውል ውስጥ ባለው ነጠላ ዋጋ መሠረት ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን የነጠላ ዋጋው በመጀመሪያው ውል ውስጥ የማይገኝ ከሆነ በድርድር ስምምነት ላይ የሚደረስበት ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን መ/ቤቱ ማረጋገጥ አለበት፣

28.4. ተቋሙ ለሚጠቀምበት ዕቃ የሚያስፈልገው መለዋወጫ የሚገኘው ቀደም ሲል ዕቃውን ከሸጠው አቅራቢ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ሆኖም ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈፃፀም በቅድሚያ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፣

ሀ/ ተቋሙ በቂ የገበያ ጥናት ማድረግ እና ሌላ የተሻለ አማራጭ ገበያ ላይ የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፣

ለ/ ተቋሙ ለሚጠቀምበት ዕቃ ከሚገዛው መለዋወጫ ብዛት፣ ተደጋጋሚነት እና የገንዘብ መጠን አንፃር ወደፊት ሌላ አማራጭ መፈለግ የሚያስፈልገው መሆኑንና አለመሆኑን መወሰን ይኖርበታል፣

28.5. ከገበያ በለቀማ የሚፈጸመው ግዥ ለጥናትና ለምርምር አገልግሎት የሚፈለግ፣ እና ከመደበኛ አቅራቢዎች የማይገኝ፣ ወይም በለቀማ ቢገዛ ለተቋሙ የኢኮኖሚ ጥቅም እንደሚያስገኝ ሲረጋገጥ የሚከተሉትን አሰራሮች በመከተል የለቀማ ግዥ መፈፀም ይቻላል፤

ሀ/ በንዑስ አንቀጽ 28.1 (ሠ) በተገለጸው መሰረት ግዥውን በለቀማ መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስታወሻ ለመ/ቤቱ የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ ወይም በኃላፊው ውክልና ለተሰጠው አካል ቀርቦ መፈቀድ ይኖርበታል፣

ለ/ ተቋሙ ግዥውን በለቀማ ሊገዙ የሚችሉ ብዛታቸው ከሦስት ያላነሱ አካላት ያሉት ጊዜያዊ ኮሚቴ መቋቋም ይኖርበታል፣

ሐ/ የተቋቋመው ጊዜያዊ ኮሚቴ ግዥውን በጋራ በመሆን ማከናወን ያለበት ሲሆን ግዥውን ለማከናወን በቂ አቅርቦትና የሚኖርበትን ገበያ እና የገበያ ዕለት በመምረጥ ለሚመለከተው ኃላፊ ያሳውቃል፣

መ/ ጊዚያዊው ኮሚቴው በጋራ በመሆን በገበያው ውስጥ ካለው አቅርቦት የተሻለ ጥራት እና ዋጋ ያለውን ወይም ያላቸውን ሻጮች በመምረጥ ዋጋ ተደራድሮ ግዥውን ይፈፅማል፣

ሠ/ በግዥው አፈፃፀም ሒደት የተፈፀሙትን ግዥዎች ብዛትና አይነት፣ ግብይቱ የፈፀመበትን ቦታ፣ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን የሻጮችን ሙሉ ስም እና አድራሻ የሚገልፅ ሰነድ ተዘጋጅቶ ሻጮች በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ መደረግ ይኖርበታል፣

ረ/ በለቀማ የተገዙ ግዥዎች በሚጓጓዙበት ወቅት እንዳይበላሹ እና እንዳይጠፉ በጥንቃቄ መያዝ እና በተቻለ ፍጥነት የሚመለከተው ክፍል እንዲረከባቸው መደረግ ይኖርበታል፣

ሰ/ ጊዜያዊው ኮሚቴ አጠቃላይ የለቀማ ግዥ አፈፃፀሙን የሚገልፅ ቃለ-ጉባኤ በማዘጋጀት ተፈራርሞ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፣

28.6. በግዥ መመሪያው ከሚወሰን የገንዘብ መጠን ያልበለጡ ጥቃቅን ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ በሚፈጸም የግዥ ዘዴ መሰረት ተቋሙ በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ያልበለጡ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር የተያያዙ የቀጥታ ግዥዎችን ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት መፈፀም ይችላል። ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈጸሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) መብለጥ አይኖርበትም፣

28.7. ተቋሙ ለሚኖረው የተለየ የግዥ ፍላጎት ማሟያ ከገበያ በለቀማ ግዥ መፈፀም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና በግዥ መመሪያው ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን ያልበለጡ ጥቃቅን ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ በሚፈጸም የግዥ ዘዴ በመጠቀም ከሚፈጸም ግዥዎች ካልሆነ በስተቀር ተቋሙ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጽመው ግዥ ሊገዛ ያሰበውን የግዥ አይነትና መጠን በመግለፅ አቅራቢው ሐሳቡን እንዲሰጥ በደብዳቤ ሊጠይቅ ይገባል። በዚህ መልኩ የሚላከው ደብዳቤ እንደአስፈላጊነቱ ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ እና አቅራቢው ዋጋን ጨምሮ የተሟላ ሐሳቡን እንዲያቀርብ የሚያስችለውን መረጃ ያካተተ መሆን አለበት፣

28.8. ተቋሙ ከአቅራቢው በፅሁፍ የቀረበለትን ዋጋን የጨመረ ሒሳብ ተቀብሎ በመመርመርና የዚህን መመሪያ አንቀፆች እንደማይጥስ በማረጋገጥ ዋጋን ጨምሮ ድርድር ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ከለየ በኋላ ድርድር ማድረግ ይችላል፣

28.9. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 28.9 ላይ በተመለከተው መሰረት ድርድር ለማድረግ ተቋሙ ተደራዳሪዎችን መምረጥ እና ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈጸም ሲፈልጉ ግዥውን መፈጸም ያስፈለገበትን ምክንያት እና የሚገዛውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት ፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያብራራ መግለጫ ማዘጋጀትና ዋጋን ጨምሮ ከአቅራቢው ጋር መደራደር የሚያስፈልገው ሲሆን የሚደረገው ድርድር በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚሠጠውን አቅጣጫና የድርድር አትኩሮት ነጥቦች መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፣

28.10. ተቋሙ ለሚኖረው የተለየ የግዥ ፍላጎት ማሟያ ከገበያ በለቀማ ግዥ መፈፀም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና በግዥ መመሪያው ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን ያልበለጡ ጥቃቅን ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ በሚፈጸም የግዥ ዘዴ በመጠቀም ከሚፈጸም ግዥዎች ካልሆነ በስተቀር ተቋሙ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈፅመው ግዥ የውል ስምምነት መፈረም ይኖርበታል፣

28.11. ተቋሙ ይህ የግዥ ዘዴ በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካካል ውድድር እንዳይኖር ወይም በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካካል ልዩነት ለመፍጠር ታስቦ ጥቅም ላይ ያልዋለ እንደሆነ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፣

28.12. ተቋሙ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 10 መሰረት ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈጸም ሲፈልጉ ግዥውን መፈጸም ያስፈለገበትን ምክንያትና የሚገዛውን ዕቃ፣ ወይም አገልግሎት ጥራት ብዛት የማቅረቢያ ጊዜ እና ሁኔታዎች የሚያብራራ መግለጫ ማዘጋጀትና ዋጋን ጨምሮ ከአቅራቢው ጋር በግልጽ መደራደር አለበት፣

28.13. ተቋሙ ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈጸም የሚችለው ግዥው ለመፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት እና የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት ፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያብራራ መግለጫ ማዘጋጀትና ዋጋን ጨምሮ ከአቅራቢው ጋር በግልጽ በመደራደርና ድርድሩ ከተካሄደ በኋላ ግዥ ለመፈጸም የሚደረሰው ስምምነት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በሚፈረም ውል ከተረጋገጠ በኃላ ይሆናል፡፡

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ግዥ

**29. የማዕቀፍ ግዥ**

29.1. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስቀድሞ የግዥ ፍላጎት ዕቅድ ለመንግስት ግዥ ኤጀንሲ በማቅረብና በማስፈቀድ የማዕቀፍ ግዥ ውል ስምምነት ካደረጉት ድርጅቶች የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ መፈጸም ይቻላል፣

29.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 29.1. የተገለጸው ቢኖርም በተቋሙ የማዕቀፍ ግዥ ሊፈጸም የሚችልው የተቋሙን የበላይ አመራር በማስፈቀድ፣

ሀ/ በግልጽ ጨረታ ወጥቶ የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅራቢ ያልተገኘ ሲሆን ወይም የቀረበው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ዋጋ ከገበያ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር የተጋነነ ሲሆንና ተቋሙ ግዢውን ከማዕቀፍ ግዥ ቢፈጽም የተሻለ ጥቅም የሚያስገኝ ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ ተፈላጊውን ዕቃ ወይም አገልግሎት በአጭር ጊዜ ማግኘት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

29.3. ተቋሙ የማዕቀፍ ግዥ ሊፈጽም የሚችለው የመንግስት ግዥ ኤጀንሲ የማዕቀፍ ግዥን አስመልክቶ ያስተላለፈውን መመሪያና አሰራር በመከተል ይሆናል።

## ክፍል ሰባት

## የውል አስተዳደር

### 30. ውልን ተፈፃሚ ማድረግ

30.1. ተቋሙ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመው በስተቀር ከአቅራቢዎች ጋር የተደረጉ የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይኖርበታል፣

30.2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 30.1 ላይ የተመለከተውን ተግባራዊ ለማድረግ ውሉ የሚያስቀምጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም ይኖርበታል፡-

ሀ/ ውሉ ቅድሚያ ክፍያ እንዲፈፀም የሚያዝ ከሆነ በዚህ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት አቅራቢው የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንዲያሲዝ በማድረግ የቅድሚያ ክፍያውን በወቅቱ መፈፀም፣

ለ/ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ሊከፈትላቸው ለሚገባ ግዥዎች ተገቢው ፎርማሊቲ መሟላቱን በማረጋገጥ ሌተር ኦፍ ክሬዲቱን በፍጥነት መክፈት፣

ሐ/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 30.2 በፊደል ተራ "ሀ እና ለ" ከተቀመጡት በተጨማሪ ተቋሙ ሊፈፅመው የሚገቡ ተግባራትን በውሉ መሰረት በወቅቱ ማከናወን፣

30.3. ተቋሙ ውሉን ተፈፃሚ ለማድረግ በአቅራቢው ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመለየት አቅራቢው በውሉ መሰረት ተግባራቱን በወቅቱ መፈፀሙን ተከታትለው ማረጋገጥ ይኖርበታል፣

30.4. ተቋሙ የውሉ ቅድመ ሁኔታች ተሟልተው ውሉ ተፈፃሚ መሆን የጀመረበትን ቀን መዝግቦ መያዝ እና እንደ አስፈላጊነቱም አቅራቢው እንዲያውቀው ማድረግ ይኖርበታል፣

30.5. ተቋሙ የግንባታ ዘርፍ ስራ ግዥ ሲፈፅም ክፍያ የሚፈፀመው የግንባታውን የክንውን ደረጃ መሠረት አድርጎ እና የሚከተለውን አፈፃፀም ተከትሎ መሆን ይኖርበታል፣

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈፀመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ ይሆናል፣

ለ/ በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 17.26.9 ከተመለከተው በተጨማሪ ለማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ስራ በክፍያ የምስክር ወረቀት መሠረት ከሚፈፀመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ሥራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% (አምስት በመቶ) በመያዣ መልክ ተቀንሶ ይያዛል፣

ሐ/ የግንባታ ስራው ሲጠናቀቅ እና ጊዜያዊ ርክክብ ሲደረግ በዚህ ንዑስ አንቀፅፊደል ተራ (ለ) መሠረት ከተያዘው ገንዘብ ላይ 50% (ሃምሳ በመቶ) ለሥራ ተቋራጩ ይለቀቃል፡፡ ቀሪው 50% (ሃምሳ በመቶ) ለአንድ አመት የጥገና ጊዜ ተይዞ ይቆያል፡፡ ሆኖም የሥራ ተቋራጩ ለ12 ወራት የሚቆይ በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ካቀረበ የተያዘው ገንዘብ ሊለቀቅለት ይችላል፣

መ/ አማካሪ መሐንዲሱ የክፍያ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ከሥራ ተቋራጩ ተዘጋጅቶ በቀረበለት በ 7(ሰባት) የሥራ ቀናት ውስጥ የምርመራውን ሥራ ማጠናቀቅ ይኖርበታል፣

ሠ/ የክፍያ የምስክር ወረቀት በአማካሪ መሐንዲሱ ተረጋግጦ በቀረበ ቢያንስ በ30 (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ መ/ቤቱ ተገቢውን ክፍያ ለሥራ ተቋራጩ መፈፀም አለበት፣

ረ/ አማካሪ መሐንዲሱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ከቀረበለት በኋላ ያለበቂ ምክንያት በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (መ) ላይ ከተጠቀሰው ጊዜ ያሳለፈ እንደሆነ በመዘግየቱ ምክንያት ተቋራጩ በመ/ቤቱ ላይ ለሚያቀርበው ማንኛውም ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ አማካሪ መሐንዲሱ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የአማካሪ መሐንዲሱ ኃላፊነት ለአገልግሎቱ ከሚከፈለው ዋጋ ሲበልጥ አይችልም፣

ሰ/ ተቋሙ ያለበቂ ምክንያት በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሠ) ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በአማካሪ መሐንዲሱ በቀረበለት ማረጋገጫ መሰረት ክፍያ ባይፈፅም ተቋራጩ በውሉ መሰረት ለሚያቀርበው ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## 31. <u>የውል አፈፃፀምን መከታተል</u>

31.1. የተቋሙን የውል አፈፃፀምን የሚከታተል አካል መለየት ወይም የውል ክትትል በተለያዩ አካላት በቅንጅት የሚፈፀም በሚሆንበት ወቅት አካላቱ ተግባራቸውን በግልፅ እንዲያውቁ ማድረግ ይኖርባቸዋል፣

31.2. የውል አፈፃፀምን የሚከታተለው የተቋሙ አካል አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፣

31.3. ተቋሙ በውል ስምምነቱ መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ የሚከተሉትን የውል አስተዳደር ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል፡-

ሀ/ ተከታታይ ክፍያዎችን በወቅቱ መፈፀም፣

ለ/ አቅራቢው የውል ግዴታውን እየተወጣ እንደሚገኝ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በወቅቱ መስጠት፣

ሐ/ አቅራቢው የውል ግዴታውን መወጣት እንዲችል ሕጋዊ የሆነ እገዛ በማድረግ የውሉ አፈፃፀም የተሳካ እንዲሆን ማድረግ ይኖርበታል፣

31.4. በውል አፈፃፀም ወቅት እንደሁኔታው የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያ የተቋሙን ጥቅም የሚጎዳ እና በጨረታው ከተወዳደሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንፃር ለአቅራቢው የተለየ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም፣

31.5. በውል አፈፃፀም ክትትል ወቅት ተቋሙ በተለይ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም ይኖርበታል፡-

ሀ/ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የውል ስምምነቱን ሁኔታዎች ጠብቆ በወቅቱ መክፈት፣

ለ/ ተቀባይነት የሚኖራቸውን የሌተር ኦፍ ክሬዲት ማስተካከያ ጥያቄዎች ተቀብሎ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣

ሐ/ ተገቢው አገልግሎት ከመገኘቱ በፊት የውል ማስከበሪያ፣ የሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ የዋራንቲ መጠቀሚያ ጊዜዎች እንዳያልፉ ጥንቃቄ እና ክትትል ማድረግ፣

መ/ የግንባታ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ መገንባታቸውን፣ የዕቃ አቅርቦቶች እና አገልግሎቶች በውሉ ጊዜ ውስጥ ለመከናወናቸው ክትትል መደረጉን እና ሪፖርት መቅረቡን፣

ሠ/ ከዉል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ከአቅራቢዎች ምንም ዓይነት የይገባኛል ጥያቄዎች እንዳይፈጠሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ፣

31.6. ተቋሙ በውል አፈፃፀም ወቅት ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን መለየት እና አገልግሎቶቹ የውል አፈፃፀሙን በሚያግዝ መልኩ መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለበት::

## 32. <u>ውል ማጠናቀቅ</u>

32.1. ተቋሙ ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረመው ውሎችና እና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢውን ዕልባት በወቅቱ አግኝተው ውሉ መጠናቀቁን ማረጋገጥ አለበት ለዚህም፡-

ሀ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት የሚገባውን የግንባታ ዘርፍ ስራ፣ ዕቃ፣ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ማቅረቡን፣

ለ/ በውሉ መሰረት የተያዙ ዋስትናዎች፣ ዋራንቲዎች ተገቢው ክትትል የተደረገባቸው እና አስፈላጊ በሆነ ወቅት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን፣

ሐ/ በውሉ መሰረት ለአቅራቢዎች ሊከፈል የሚገባ ክፍያ የተጠናቀቀ መሆኑን፣ ለተከፈሉ ክፍያዎች ሁሉ በውሉ መሰረት አገልግሎት መገኘቱን፣

መ/ ከሶስተኛ ወገን ማለትም ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ ከአጓጓዦች፣ ከጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከጉምሩክ አስተላላፊዎች፣ ከባንክ እና ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የተያያዙ የተቋሙን ጥቅሞች መከበራቸውን እና የተቋሙን ግዴታዎች የተፈጸሙ መሆኑን ማረጋገጥ አለባት፣

32.2. ተቋሙ ከአቅራቢው እና ከሦስተኛ ወገን ጋር ያሉ ያልተጠናቀቁ ሒሳቦችን በመዝጋት እንደአስፈላጊነቱ የውል አፈጻጸም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ሌሎች ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 33. መደበኛ ያልሆኑ የግዥ ጥያቄዎችን መመርመር፣

33.1. ተቋሙ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን የግዥ አፈጻጸም ስርዓቶች ሊጠብቅ ያልቻለ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዥ መፈፀም የሚቻለው በበቂ ምክንያት ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ጥያቄያቸውን አቅርበው ሲፈቅድላቸው ብቻ ነው፣

33.2. የግዥ የስራ ክፍል ከላይ በንዑስ አንቀፅ 33.1 በተገለጸው መሠረት ለሚያቀርቡት የልዩ ፈቃድ ጥያቄ የወሰዱት አማራጭ ከወጪ፣ ከጥራት፣ ከጊዜ እና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያካተተ መግለጫ አግባብ ካላቸው ደጋፊ ሰነዶች ጋር ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ማቅረብ አለባቸው፣

33.3. በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ውሳኔ የሚሰጠው የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ እና እንደ አስፈላጊነቱ ከሚመለከታቸው ክፍሎች የሚቀርቡት አስተያየት መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

### 34. የግዥ ሠነዶች

34.1. ተቋሙ የሚገዛ ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች አጭር መግለጫ፣ የጨረታ ማስታወቂያ፣ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ወይም የዋጋ ማቅረቢያ፣ያቀረቡ አቅራቢዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ስምና አድራሻ እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያስባቸውን የግዥ ሰነዶች ይዞ ማቆየት ይኖርበታል፣

34.2. በግዥ ሂደቱ ላይ አቤቱታ ቀርቦ ከሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ፣

34.3. ከግልጽ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ዘዴዎች የተመረጠበት ምክንያት መያዝ አለበት፣

34.4. የግዥ ሰነዶች በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ደንብ ወይም መመሪያ ላይ ለፋይናንስ ሰነዶች የቆይታ ጊዜ ከሚገለፀው እኩል የቆይታ ጊዜ ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍልዘጠኝ

## የተቋሙ ግዥ ሥነ-ምግባር

### 35. ከግዥ ባለሙያ የሚጠበቅ ሙያዊ ሥነ- ምግባር

ማንኛውም ከተቋሙ ግዥ አፈጻጸም ጋር ግንኙነት ያለው ሠራተኛ ወይም ኃላፊ የሚከተሉትን የስነ ምግባር መርሆዎች ተከትለው ተግባራቸውን ያከናውናሉ፤

35.1. በተቋሙ ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተሰማራ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተገናኘ የሚሰጠው ውሳኔ በማንኛውም መልኩ ራሱን ወይም ቤተሰቡን ሊጠቅም የሚችል መሆኑን ሲረዳ ከሥራው ጋር የተገናኘ የጥቅም ግጭት መኖሩን በጽሑፍ በማሳወቅ ከግዥ ሂደቱ ሥራ ራሱን ማግለል ይኖርበታል፣

35.2. ተቋሙ በግዥ ሥራ ላይ የተሳተፈ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ከማንኛውም ምንጭ መረጃ ሲደርሰው፡-

35.2.1. ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በቀረበው የጥቅም ግጭት ጉዳይ ላይ አስተያየት በፅሑፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

35.2.2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 35.2.1 በተሰጠው የጽሑፍ አስተያየት እና ተገቢ ነው ብሎ ባመነባቸው መንገዶች ተጨማሪ መረጃ በማሰባሰብ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ከያዘው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ወይም እንደሌለው ይወስናል፣

35.2.3. ከላይ በአንቀጽ 35.2.2 ላይ በተጠቀሰው መሰረት የተቋሙ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት መኖሩን ሲረጋገጥ፣

ሀ/ ሠራተኛውን ወይም ኃላፊውን ከሂደቱ እንዲገለል ያደርጋል፣

ለ/ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በሂደቱ ተሳትፎባቸው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች እንደገና እንዲታዩ ያደርጋል፣

ሐ/ሠራተኛው ወይም ኃላፊው የጥቅም ግጭቱን ያላሳወቀው ከግንዛቤ ጉድለት ነው ብሎ ካመነ በስተቀር በሠራተኛው ወይም በኃላፊው ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣

35.3. በተቋሙ ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሳተፍ ማንኛውም የተቋሙ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም አቅራቢዎች እኩል የመወዳደርና ውል የመፈጸም ዕድል እንዳያገኙ የሚያደርግ ማንኛውንም ተግባር መፈጸም የለበትም:: ለዚህም፡-

ሀ/ በጨረታ ጥሪ ሁሉም ዕጩ ተወዳሪዎች በቂ መረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በጨረታው ለመሳተፍ እና ተመራጭነት ሊያገኝ የሚችል የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት የሚያስችል የተሟላ እና ግልጽ መረጃ መያዙን ማረጋገጥ፣

ለ/ በጨረታ ሰነድ የተገለጸው ማንኛውም የመወዳደሪያ መስፈርም ሆነ የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር የተወሰነ ዕጩ ተወዳዳሪን ሊጠቅም በሚችል መልኩ አለመዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

ሐ/ የጨረታው ውጤት ለሁሉም ተሳታፊዎች በእኩል ጊዜ መገለጹን ማረጋገጥ፣

መ/ በውል ሰነድ ዝግጅት ለአቅራቢዎች የሚሰጠው ኃላፊነት ግዴታቸውን ሆነ ብሎ ለማቅለል ወይም ለማክበድ ያላለመ እና እስከተቻለ ድረስ ተመሳሳይ ውል ለሚፈርሙ አቅራቢዎች ተመሳሳይ ይዘት ያለው ውል ሆኖ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

ሠ/ በውል አፈጻጸም ወቅት ክፍያን ፣ ቁጥጥርን፣ የመረጃ ልውውጥ እና የመሳሰሉት ተግባራት በእኩል ለሁሉም አቅራቢዎች ተግባራዊ መሆቸውን ማረጋገጥ፣

35.4. በተቋሙ ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሳተፍ ማንኛውም የተቋሙ ሠራተኛች ወይም ኃላፊዎች በግዥ ሥራቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ወይም ሊያሳድር የሚችል ምንም ዓይነት ስጦታ ከሶስተኛ ወገን መቀበል የለባቸውም፡፡ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም የተቋሙ ሠራተኞች ወይ ኃላፊዎች የሚከተሉትን ያካተተ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡-

ከዚህ በታች በፊደል ተራ /ሠ/ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ/ የገንዘብ ዋጋ ያለውን ስጦታ በተለይ ለተቋሙ አቅራቢ/ዕጩ አቅራቢ ከሆነ አካል አለመቀበል፣

ለ/ የሥራ ዕድል ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ አለመቀበል፣

ሐ/ በግል በሚደረግ ግዥ ላይ ለተቋሙ አቅራቢ/ዕጩ አቅራቢ ከሆነ አካል የተለየ የዋጋ ቅናሽ ወይም አገልግሎት አለመቀበል፣

መ/ በሥራው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የግብዣ ፕሮግራም አለመቀበል፣ ሆኖም ጉዞን ያላካተተ እና ጋባዡ ከተቋሙ ጋር ካለው የሥራ ግንኙነት ጋር የማይገናኝ ሲሆን ሊቀበል ይችላል፣

ሠ/ ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተቀመጠው ቢኖርም ሠራተኛው ወይም ኃላፊው አቅራቢው/ ዕጩ አቅራቢው ለማስታወቂያነት አገልግሎት የሚያዘጋጀው የውስጥ እሴት እንጂ የገበያ ዋጋ የሌላቸው በነጻ የሚታደሉ ስጦታዎችን መቀበል ይችላል፣

35.5. የተቋሙ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በስራ አጋጣሚ የሚመለከታቸውን የተፈጠሩ ወይም ሊፈጠሩ የታሰቡ የሙስና ተግባራትን ጉዳይ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ የሚኖርበት ሲሆን ለዚህም አንቀጽ አፈጻጸም፡-

ሀ/ የሚያደርገው ጥቆማ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ/ እራሱን የታሰበውን የሙስና ተግባር ሊደግፍ ከሚችል ማኛውም ተግባር መጠበቅ ይኖርበታል፣

35.6. የተቋሙ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከግዥ ሥራ ጋር በተገናኘ ያወቃቸውን የተቋሙን ወይም የዕጩ ተወዳሪውን ወይም የአቅራቢውን ሚስጥራዊ መረጃዎች መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም፡-

ሀ/ ውድድርን ሊገድብ የሚችል ወይም ለተወዳዳሪዎች ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚሰጥ ወይም የተቋሙን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል መረጃ በልዩ ሁኔታ በተቋሙ አመራሮች ካልተፈቀደ በስተቀር ለማንኛውም አካል አለመስጠት፣

ለ/ ተቋሙ በውል አፈጻጸም ወቅት ከአቅራቢዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የተቋሙን ውሳኔ እና መረጃ መጠበቅ፣

ሐ/ የዕጩ ተወዳሪዎችን መረጃ እና የግምገማ ሂደት ውጤት በተቋሙ ከመገለጹ በፊት ለማኛውመ አካል አለማሳወቅ፣

## 36. ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚጠበቅ ሥነ- ምግባር

በተቋሙ ግዥ የሚሳተፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የግዥ አፈጻጸሙን ለማዛባት የሐሰት ማስረጃ አለማቅረብ ወይም መገለጽ የነበረበትን መረጃ አለመግለጽ እንደሌለባቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ዋና ዋና የሥነ-ምግባር መርሆዎችን መከተል አለባቸው፡-

ሀ/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ በተቋሙ ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለተሰማራ የተቋሙ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ውሳኔ ለማዛባት ወይም ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ተቋሙ ሊከተለው የሚገባውን አሰራር ለማስለወጥ በመደለያ መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ ወይም ስጦታ ለመስጠት ቃል መግባት ወይም የስራ ዕድል ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት መስጠት የለበትም፣

ለ/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ የሚያውቀውንና የተቋሙ በግዥ አፈጻጸም ወይም በውል አስተዳደር ወቅት ለሚሰጠው ውሳኔ ይረዳዋል ብሎ የሚገምተውን ለተቋሙ መግለጽ አለበት፣

ሐ/ ተቋሙ የሚያደርገው የግዥ አፈጻጸም በመስኩ ከተሰማራ ሌላ ተወዳዳሪ ጋር በመነጋገር ዋጋ መስጠት፣ ተቋሙን ሊጎዳ የሚችል መረጃ መለዋወጥ ወይም በግዥ አፈጻጸሙ ለመሳተፍ የሌላ ተወዳዳሪን ሰነድ ወይም ሃሰተኛ ማስረጃ መጠቀም ወይም መረጃ መደበቅ የለበትም፣

መ/ በተቋሙ ግዥ አፈጻጸም ሂደት ያወቃቸውን ሊፈፀም የታሰበን ወይም የተፈጠረ የሙስና ተግባራት ለሚመለከተው አካል ማሳወቅና የሙስና ተግባሩ ተባባሪ ሆኖ አለመገኘት፣

## ክፍል አስር

## በተቋሙ ግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብ አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ

### 37. የኮሚቴ አባላት ስያሜና የስራ ዘመን

ሀ/ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ከእጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ከተጫራቾች በተቋሙ የግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብን አቤቱታ አጣርቶ ውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የኮሚቴ አባላቱም ሰብሳቢን ጨምሮ አምስት ባለሙያዎች የኮሚቴ አባላትን ከኤጀንሲው የሚሰይም ሲሆን፣ አንድ ባለሙያ ድምፅ የሌለው አባል ሆኖ በፀሐፊነት እንዲሰራ ይመደባል፣

ለ/ የኮሚቴ አባላት በተቻለ መጠን በስምምነት የውሳኔ ሃሳብ የሚያሳልፉ ሲሆን አስፈላጊ ሲሆን በድምጽ ብልጫ የውሳኔ ሃሳብ ሊተላለፍ ይችላል። የአባላት ድምጽ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ የኮሚቴው ሰብሳቢ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፣

ሐ/ የኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን ሶስት ዓመት ነው። ሆኖም የስራ አፈጻጸማቸውና ያላቸው ሥነ-ምግባር ታይቶ ለሌላ አንድ ተመሳሳይ የስራ ዘመን እንዲሰሩ ሊራዘምላቸው ይችላል፣

መ/ ለኮሚቴ አባልነት የሚሰየሙት በተቋሙ ግዥና ንብረት አስተዳደር በቂ እውቀትና ልምድ ያካበቱ፣ መልካም ባህሪና ስነ- ምግባር ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፣

### 38. የኮሚቴ ሰብሰባ

ሀ/ የኮሚቴ አባላት አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ሲኖር በ10 የስራ ቀናት ውስጥ በመመርመር የውሳኔ ሃሳብ ያርባል፣

ለ/ ከኮሚቴ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል፣

ሐ/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሰብሳቢው በስብሰባ ላይ የማይገኝ ሲሆን ስብሰባውን በጊዜያዊነት የሚመራለት ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል ሊወከል ይችላል፣

### 39. ከኮሚቴ አባልነት መልቀቅ

የኮሚቴ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በማንኛውም ጊዜ ከኮሚቴ አባልነት መልቀቂያ ማመልከቻ ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በማቅረብ ሲፈቀድላቸው መልቀቅ ይችላሉ።

## 40. የኮሚቴ አባልነት መቋረጥ

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የኮሚቴ አባልነት መቀጠል ሊያቋርጥ ይችላል፤

ሀ/ በአዕምሯዊ ወይም በአካላዊ ጉዳት ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ፣

ለ/ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ፣

ሐ/ የሥነ-ምግባር ወይም የዲሲፕሊን ጉድለት ከተገኘበት፣

መ/ ያለ በቂ ምክንያት በ3 (ሶስት) ተከታታይ የኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ ካልተገኘ፣

## 41. የጥቅም ግጭትን ስለመግለጽ

ማንኛውም የኮሚቴው አባል ከአቤቱታ አቅራቢ ወይም አቤቱታ ከቀረበበት ግዥ አፈጻጸም ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ግንኙነት ካለው ይህንኑ ለኮሚቴው በማሳወቅ ከኮሚቴው ስብሰባ ራሱን ማግለል አለበት፡፡

## 42. የኮሚቴ ስልጣን

ኮሚቴው ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ አሸናፊውን ተጫራች ከመምረጥ ወይም ውል ከመፈረም ጋር የተያያዙ ውሳኔ ሀሳቦችን ከማሳለፍ በስተቀር የሚከተሉት ስልጣኖች ይኖሩታል፣

ሀ/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ህግ ከሚያዘው ውጭ ስለመፈጸሙ ወይም ግዥ በትክክል ስላለማከናወኑ ወይም የግዥውን አመራር በትክክል ስላለመፈጸሙ ወይም የጥቅም ግጭት ወይም የሙስና ተግባር ስለመፈጸሙ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ከግዥው ጋር የተያያዘ መረጃዎች፣ ሰነዶች፣ መዝገቦችና መግለጫዎች ከግዥ የስራ ሂደት ወይም ከእጩ ተወዳዳሪው እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣

ለ/ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ተቋሙ ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የጽሁፍ ማስታወቂያ መላክ፣

ሐ/ የቀረበው አቤቱታ በተቋሙ ወይም በሌሎች ባለሙያዎች ዝርዝር የቴክኒክ ምርመራ ተደርጎበት ሪፖርት እንዲቀርብለት የማድረግ፣

መ/ ምስክሮችን የመጥራት ምስክሮችና ግዥው የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመሀላ እንዲሰጡ የማድረግ፣

ሠ/ ተቋሙ ከህግ ውጭ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን የውሳኔ ሃሳብ ለዋና ዳይሬክተሩ ማቅረብ፣

ረ/ ተገቢ ሆኖ ካላገኘው የተጫራቹን ወይም የእጩ ተወዳዳሪውን አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ ሃሳብ ማቅረብ፣

## 43. የኮሚቴው ተግባር

ኮሚቴው ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

ሀ/ ከዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ከተጫራች አቤቱታን መቀበል፣

ለ/ አቤቱታው ለኮሚቴው የቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪው ወይም ተጫራቹ ለስራ ሂደቱ አቤቱታውን አቅርቦ መልስ በተሰጠው 5 የሥራ ቀናት ውስጥ ወይም የግዥ ስራ ሂደት መልሱን አዘግይቶ ከሆነ አቤቱታው ለግዥ ሥራ ሂደት ከቀረበ ከ10ኛው ቀን በኋላ ባሉት 5 የሥራ ቀናት ውስጥ መሆኑን ማጣራት፣

ሐ/ አቤቱታው የቀረበው በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ከሆነ አቤቱታ ለቀረበበት የስራ ሂደት አቤቱታው የቀረበበት መሆኑንና ከግዥው አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ሰነዶችንና መግለጫዎች እንዲልክ እና በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የጽሑፍ ማስታወቂያ መላክ

መ/ የጽሑፍ ማስታወቂያ የደረሳቸው የስራ ሂደቶችና ሪጅኖች የግዥ ሂደት የተከናወነባቸውን ሰነዶች፣ ማስረጃዎችና መግለጫ እንዲልክ መከታተል፣

ሠ/ ከተቋሙ ተጠናቅረው የቀረቡትን አቤቱታዎችን ጭብጦች፣ ከስራ ሂደትና ከሪጅኖች የተሰጠውን ምላሽ፣ ማስረጃዎችን፣ ሰነዶችን እና መግለጫዎችን ከተቋሙ ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አኳያ በመመርመር የውሣኔ ማቅረብ፣

ረ/ ውሣኔው ለሚመለከታቸው አካላት በጽሑፍ እንዲደርስ ማድረግ፣

ሰ/ ስለተከናወኑ ተግባራት ለዋና ዳይሬክተሩ ሪፖርት ማቅረብ፣

# ክፍል አስራ አንድ

# ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወይም የግዥ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ የሚቀርብ አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት

## 44. የዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች አቤቱታ የማቅረብ መብት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ በዚህ መመሪያ የተመለከተውን በአግባቡ ባለመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት ወይም ኪሳራ ደርሶብኛል ወይም ሊደርስብኝ ይችላል የሚል

ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ጨረታው እንደገና እንዲታይለት ወይም ሂደቱ እንዲጣራለት ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወይም ለግዥ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 45. አቤቱታ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች

ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም፤

ሀ/ በግዥ መመሪያ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ በተወሰነው የግዥ ዘዴ ምርጫ ላይ፣

ለ/ በውስን ጨረታና በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈጸም ግዥ በተከናወነ የተጫራቾች አመራረጥ ወይም በጨረታ ሰነዱ ላይ አስቀድሞ በሰፈረ የተጫራቾች ማወዳደሪያ መስፈርት ላይ፣

ሐ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.20.1 ለአገር ውስጥ አቅራቢዎች፣ ምርቶች እና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች በተሰጠ ልዩ አስተያየት ላይ፣

መ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.19.3 መሰረት ጨረታን፣ የመጫረቻ ሰነድን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ለማድረግ በተሰጠ ውሣኔ ላይ፣

ሠ/ ተቋሙ የግምገማውን ውጤት ካሳወቀበት ወይም ለቀረበለት አቤቱታ ውሣኔውን በጽሑፍ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር 5(አምስት) የሥራ ቀን ካለፈ፣

ረ/ አቤቱታው የቀረበው ውል ከተፈረመ እና ውሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 46.1 ፊደል ተራ ‹‹ሀ›› የተጠቀሰውን 7 የሥራ ቀናት የጊዜ ገደብ ጠብቆ የተፈረመ ከሆነ፣

## 46. ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር የሚቀርብ አቤቱታ የሚጣራበት ሥርዓት

### 46.1. የግዥ ውል ከመፈረሙ በፊት፣

ሀ/ ተቋሙ የጨረታውን ወይም የአቤቱታውን ውጤት ለተጫራቾች ከገለጸበት ቀን ጀምሮ ተጫራቾች አቤቱታ ካላቸው ማቅረብ እንዲችሉ 7 የሥራ ቀናት ሊጠብቃቸው ይገባል፣

ለ/ በግዥ አፈጻጸም ሂደት ጉዳት ወይም በደል ደርሶብኛል የሚል አቅራቢ ወይም ተጫራች ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን የመጨረሻ ውሣኔ በይፋ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር 5 የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ለተቋሙ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፣

ሐ/ አቤቱታ ባቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እና በተቋሙ በስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር የግዥውን ሂደት በማገድ እና አቤቱታ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር 10 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔው የተሰጠበትን ምክንያት ወይም አቤቱታው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ የሚወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ በጽሑፍ ውሳኔ መስጠት አለበት፣

መ/ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ውሣኔውን በሰጠ በ5 የሥራ ቀናተ ውስጥ የውሣኔውን ቅጂ አቤቱታውን ላቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እንዲደርስ ማድረገ አለበት፡፡

46.2. <u>በሁለት ኤንቬሎፕ የቀረበ ጨረታ</u>

ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጫራቾች የቴክኒክና የዋጋ የመጫረቻ ሰነዳቸውን በተለያየ ሁለት ኤንቬሎፕ እንዲያቀርቡ በተደረገበት ጨረታ፣

ሀ/ የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ተቋሙ ለሁሉም በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑ ተጫራቾች የቴክኒክ ግምገማው አፈፃፀም፣

ለ/ ማንኛውም ተጫራች የቴክኒክ ግምገማው አፈፃፀም ይህንን የግዥ የአፈፃፀም መመሪያ እና የጨረታ ሰነዱን መሠረት አድርጎ አልተከናወነም የሚል ቅሬታ ካለው፣ ቅሬታውን በ5 የሥራ ቀን ውስጥ ማቅረብ እንደሚችል የተቋሙ የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾች በሚያሳውቅበት ደብዳቤ ላይ ማመልከት ይኖርበታል፣

ሐ/ የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት ለቀረበው አቤቱታ በተቋሙ የግዥ የስራ ሂደት የተሰጠው ውሣኔ የግዥ መመሪያውን እና የጨረታ ሰነዱን የጠበቀ አለመሆኑን ማረጋገጥ የሚችል ተጫራች የግዥ የስራ ሂደት ኃላፊን ውሳኔ ባወቀ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለኮሚቴው ሊያቀርብ ይችላል፣

መ/ የተቋሙን የዋጋ መወዳደሪያ ሃሳብ የያዘውን ኤንቨሎፕ ሊከፍት የሚችለው የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾቹ ካሳወቀ 5 ቀናት በኋላ ይሆናል፡፡ ሆኖም የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት ላቀረበው አቤቱታ የሥራ ሂደት ኃላፊ (የቡድን መሪ) በሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት በተገቢው ጊዜ ውስጥ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ ተቋሙ ኮሚቴው የመጨረሻ ውሣኔ ሃሳብ እስከሚሰጥ ድረስ የዋጋ መወዳደሪያ ሃሳብ የያዘውን ኤንቨሎፕ ሳይከፍት እንደታሸገ ማቆየት ይኖርበታል፣

46.3. አቤቱታ የቀረበበት ማናቸውም ግዥ የሚጣራው ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድና ይህንን መመሪያ መሠረት በማድረግ ብቻ ይሆናል፡፡

## 47. <u>የተቋሙን የግዥ አፈጻጸም ሂደትን ስለማገድ</u>

ሀ/ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር አቤቱታው ከዚህ በላይ በአንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ‹‹ለ›› ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ አቤቱታው ውሣኔ እስከሚያገኝ ድረስ ጨረታው ታግዶ እንዲቆይ ያደርጋል፤

ለ/ በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር የሚተላለፍ ማናቸውም ውሣኔ እንዲሁም የውሣኔው ምክንያቶች እና ሁኔታዎች የግዥውን ሥርዓት የሚያሳዩ ሰነዶች አካል ሆነው መያዝ አለባቸው፡፡

## 48. አቤቱታ ለኮሚቴው የሚቀርብበትና የሚጣራበት ሥርዓት

ሀ/ ለግዥ የስራ ሂደት አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር አሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ለአቤቱታው ውሣኔ ካልሰጠ ወይም ውሣኔ ተሰጥቶ አቤቱታ አቅራቢው በተሰጠው ውሣኔ ያልረካ እንደሆነ የሥራ ሂደቱ ውሣኔ በጽሑፍ ከተገለጸለት ወይም ውሣኔው በወቅቱ ካልተሰጠ ውሣኔው መሰጠት ከነበረበት ቀን ገደብ ማብቂያ ጀምሮ በሚቆጠር 5 የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ለአቤቱታ አጣሪና የውሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ በተቋሙ ግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፣

ለ/ ዕጩ ተወዳዳሪው ወይም ተጫራቹ አቤቱታውን ለግዥ አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ሲያቀርብ ለግዥ ስራ ሂደቱ ያቀረበውን አቤቱታ የሚያሳይ ደብዳቤ፣ በግዥ ስራ ሂደቱ ለአቤቱታው ውሣኔ ተሰጥቶ ከሆነ የውሣኔው ቅጂ፣ የአቤቱታውን ጭብጥና ተያያዥ ማስረጃዎችን በአባሪነት ማያያዝ ይኖርበታል፣

ሐ/ የተቋሙ ግዥ አፈጻጸም ላይ የግዥ አጣሪ ኮሚቴ አቤቱታው እንደቀረበለት በግዥ ስራ ሂደቱ ላይ አቤቱታው የቀረበበት መሆኑን፣ በቀረበበት አቤቱታ ላይ ያለውን ማስረጃና መግለጫ ማስታወቂያው በደረሰው በአምስት የሥራ ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ እንዲሁም ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ ቀጣይ የግዥ ሂደት እንቅስቃሴ እንዲያቆም የሚገልጽ ማስታወቂያ ለግዥ ስራ ሂደቱ ይልካል (ያሳውቃል)፣

መ/ አቤቱታ የቀረበበት የግዥ ስራ ሂደቱ እንዲልክ የሚጠይቃቸውን ሰነዶች ማስታወቂያው ከተላከለት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሠ/ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ የቀረበበትን ማናቸውንም ግዥ የሚያጣራው እና የውሣኔ ሃሳብ የሚያቀርበው ተቋሙ ለጨረታው ያዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ፣ ይህንን መመሪያ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የጨረታ ግምገማ ሪፖርቱን፣ ተጫራቹ ያቀረበውን የመጫረቻ እና ሌሎች ሰነዶችን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

ረ/ የተቋሙ ግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብ አቤቱታ አጣሪና የውሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ ከላይ በአንቀጽ 42 ፊደል ተራ ‹‹መ›› መሠረት የቀረቡለትን ሰነዶች መርምሮ ውሣኔውን በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ላቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እና ለመ/ቤቱ በጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡

ሰ/ የተቋሙ ግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብ አቤቱታ ኮሚቴው ያቀረበውን የውሣኔ ሃሳብ በዋና ዳይሬክተር የሚሰጠው ውሳኔ ግልባጭ ወዲያውኑ አቤቱታውን ላቀረበው አቅራቢ ወይም ተጫራች እና አቤቱታ ለቀረበበት የግዥ ስራ ሂደት እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

## 49. አቤቱታን በፍርድ ቤት ስለማየት

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 46 እና 48 መሠረት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ዕጩ ተወዳዳሪ፣ ተጫራች ወይም አቅራቢ ጉዳዩን አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

# ክፍል አስራ ሁለት

# ልዩ ልዩ

## 50. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር

50.1. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ደርሷል የሚባለው አቅራቢው ድንገት ደራሽ በሆነ ሁኔታ የውል ግዴታውን እንዳይፈጽም ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ባጋጠመው ጊዜ ነው፣

50.2. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ነው ሊያሰኙ የሚችሉ ምክንያቶች ከሚከተሉት አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ

50.2.1. ውል እንዳይፈጸም በመንግስት የሚደረግ ክልከላ፣

50.2.2. እንደ መሬት መናወጥ፣ መብረቅ፣ ማዕበል፣ እና የመሳሰሉት ፍጥረታዊ መቅሰፍቶች፣

50.2.3. የጠላት፣ የውጪ አገር ወይም የአገር ውስጥ ጦርነት፣

50.2.4. ውል የገባው ወገን መሞት ወይም ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም፣

50.2.5. በፍትሐብሔር ሕግ የተዘረዘሩ ሌሎች ከአቅም በላይ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፣

50.3. ግልጽ የሆነ ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በስተቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ተደርገው ሊቆጠሩ አይችሉም፡-

50.3.1. በተዋዋይ ወይም ስራውን ከሚያከናውነው በአንደኛው ቅርንጫፍ መ/ቤት ውስጥ የተደረገ የሠራተኛ አድማ ወይም የመስሪያ ቤት መዘጋት፣

50.3.2. ለውሉ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች ዋጋ መወደድ ወይም መርከስ፣

50.3.3. ተዋዋይ ያለበትን የውል ግዴታ አፈጻጸም ወጪ የሚያከብድበት አዲስ ህግ መውጣት፣

## 51. የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት

በተቋሙ ግዥ ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንና ከግዥው ልዩ ባህሪ በመነሳት ተቋሙ የሚያወጣቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፣

51.1. በሚገቡት ውል መሰረት ለመፈጸም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ መሳሪያና ሌሎች መገልገያ ስፍራዎች፣ ግዥው በሚፈጸምት ተግባር የስራ አመራር ችሎታ፣ መልካም ዝና እና የሰው ኃይል ያላቸው፣

51.2. ውል ለመፈጸም የሚያስችል የህግ ችሎታ ያለው፣

51.3. በዕዳ ያልተያዘ፣ ያልከሰረ ወይም የስራ እንቅስቃሴውን ያላቋረጠ፣ የንግድ ስራ እንቅስቃሴው ያልታገደ ወይም በነዚህ ምክንያቶች ተከሶ በክርክር ላይ ያልሆነ፣

51.4. በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ፣

51.5. በመንግስት ግዥ እንዳይሳተፍ ታግዶ የነበረ ከሆነ የታገደበትን ጊዜ ያጠናቀቀ፣

51.6. የታደሰ የንግድ ስራ ፍቃድ ያለውና በኢትዮጵያ የግብር ህጎች በተደነገገው መሰረት የግብር እና የታክስ ግዴታውን የተወጣ

**52. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህንን መመሪያ የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ግዥ አዋጅና መመሪያዎች ጋር ለማጣጣም ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ለኤጀንሲው ለሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## ክፍል አስራ ሶስት

## ይህ መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ

**53. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከግንቦት 7 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት 7 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳባ ኦርያ

**የመ/ሠ/ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ**

**ዋና ዳይሬክተር**

አባሪ 1

# የግዥ ዕቅድ ማቅረቢያ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የሚገዛው ዕቃ አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ዓይነት | ግዥው የሚፈጸምበት የገንዘብ ምንጭ | | የግዥው ምድብ* | ለግዥው የተያዘው የበጀት ግምት | | የተመረጠው የግዥ ዘዴ*** | የተመረጠው የግዥው ዓይነት**** | ግዥውን ለመፈጸም የሚወስደው ጊዜ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቦርድ ከጡረታ ፈንድ የሚፈቀድ በጀት | የውጭ አገር ዕርዳታ | | መደበኛ በጀት | ካፒታል በጀት | | | ጨረታው የሚወጣበት/ የሚካሄድበት ጊዜ | ግዥው ተጠናቆ ርክክብ የሚፈጸምበት ጊዜ | |
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |

* ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ አገልግሎት እና የግንባታ ሥራ ተብሎ ይገለጽ፣

** የገንዘቡ ዓይነት በኢትዮጵያ ብር ወይም በሌላ አገር ገንዘብ መሆኑ ይገለጽ፣

*** እንደ ሁኔታው ግልጽ ጨረታ፣ የሁለት ደረጃ ጨረታ፣ የመወዳደሪያ ሃሳብ በመጠየቅ የሚፈጸም ግዥ፣ ውስን ጨረታ፣ በዋጋ ማቅረቢያ የሚካሄድ ግዥ እና ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ ተብሎ ይገለጽ፣

**** ብሔራዊ /አገር ውስጥ/ ወይም ዓለም አቀፍ ግዥ ተብሎ ይገለጽ።

## 1. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢና ፀሐፊ ዋና ዋና ኃላፊነቶች

### 1.1. የግዢ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኃላፊነቶች

የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር የሚሾም ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል

ሀ/ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴን የስብሰባ ቀንና ሰዓት ይወስናል ስብሰባ ይመራል፡፡

ለ/ ከጨረታ ሂደት ጋር የተያያዙ ተግባራት የዚህን መመሪያ ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ያረጋግጣል

### 1.2. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ፀሐፊ ኃላፊነት

የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ፀሐፊ በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር የሚመደብ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል

1.2.1. ማንኛውንም የአጽዳቂ ኮሚቴ የስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ይመዘግባል፣ ኮሚቴው የተሟሉ ሠነዶች እና መዛግብቶች እንዲኖሩት ያደርጋል፣ በጥንቃቄ ይይዛል፡፡

1.2.2. በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ከአቅራቢዎች ጋር የተደረገ ውይይት ካለ ቃለ-ጉባዔ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

1.2.3. ከኮሚቴው ሰብሳቢ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት አጀንዳ ያዘጋጃል፡፡

1.2.4. በአጽዳቂ ኮሚቴ ስብሰባዎች ድምጽ ይሰጣል፡፡

### 1.3. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የስብሰባ ሥነ- ስርዓት

1.3.1. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊሰበሰብ የሚችለው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ሲሆን ውሳ የሚተላለፈው በድምጽ ብለጫ ይሆናል፡፡

1.3.2. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ በውሳኔ አሰጣጥ ወቅት እኩል ድምጽ በሚኖረው ጊዜ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

1.3.3. በድምጽ አሰጣጥ ወቅት በሃሳብ የተለየ አካል ሲኖር የተለየበት ምክንያት በቃለ ጉባኤው እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡

1. ጨረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ

1.1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17.4/2 በተገለጸው መሠረት ዝቅተኛ የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጃና ማቅረቢያ ጊዜ በሚከተለው አኳኃን ይወሰናል፡፡

1.1.1. ተቋሙ የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የግዥውን ዓይነት እና የግዥውን የተሳትፎ ሽፋን በተለይም ውስብስብ የሆኑ እና ያልሆኑ ግዥዎችን በመለየት ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት የመጫረቻ ሰነድ የሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን መወሰን አለበት፡፡

| ተ.ቁ. | የግዥው ዓይነት | ውስብስብነት | የግዥው የተሳትፎ ሽፋን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ | ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ | ውስን ጨረታ | |
| | | | | | የውጭ አገር ተጫራች የሚሳተፉበት | የአገር ውስጥ ተጫራች ብቻ የሚሳተፉበት |
| 1 | የግንባታ ዘርፍ ሥራ | ውስብስብ | 45 ቀናት | 30ቀናት | 45ቀናት | 30ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 35ቀናት | 21ቀናት | 35ቀናት | 21ቀናት |
| 2 | ዕቃ | ውስብስብ | 45ቀናት | 30ቀናት | 45ቀናት | 30ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 35ቀናት | 15ቀናት | 35ቀናት | 15ቀናት |
| 3 | ሌሎች አገልግሎቶች | ውስብስብ | 45ቀናት | 30ቀናት | 45ቀናት | 30ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 35ቀናት | 15ቀናት | 35ቀናት | 15ቀናት |
| 4 | የምክር አገልግሎት<br>• ፍላጎት መግለጫ | ውስብስብ | 14ቀናት | 10ቀናት | - | - |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 10ቀናት | 7ቀናት | - | - |
| | • የመወዳደሪያ ሐሳብ ማቅረቢያ | ውስብስብ | 45ቀናት | 30ቀናት | 35ቀናት | 30ቀናት |
| | | ውስብስብ ያልሆነ | 35ቀናት | 15ቀናት | 21ቀናት | 15ቀናት |

1.1.2. ውስብስብ ያልሆነ የዕቃና የአገልሎት ግዥ የሚባለው በዚህ አባሪ ተራ ቁጥር 1.2 የተመለከተው ዓይነት ግዥ ነው፡፡

1.1.3. ከአንድ አቅራቢ እንዲሁም በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ በሚፈጸም የግዥ የመጫረቻ ሰነድ የማቅረቢያው ጊዜ የግዥውን ዓይነት፣ አስቸኳይነት፣ ውስብስብነት፣ የዘቅራቢዎቹን የተሳትፎ ሽፋን እና የመሳሰሉት ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ በተቋሙ ይወሰናል፡፡

1.1.4. ግዥው የሚፈጸመው የሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴን መሠረት በማድረግ በሚሆንበት ጊዜ

1.1.4.1. በመጀመሪያ ደረጃ እንደ ግዥው ዓይነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) በተመለከተው መሠረት በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ወይም በአገር ውስጥ ግልጽ

ጨረታ ለሚፈጸም ውስብስብ ግዥ የተፈቀደው ዝቅተኛ የጨረታ መቆያ ወይም የመጫረቻ ሰነድ የሚቀርብበት የመጨረሻ ጊዜ ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡

1.1.4.2. በሁለተኛው ደረጃ በተቋሙ በውድድር ተሳታፊ እንዲሆኑ የተመረጡት የተወሰኑ የአገር ውስጥ ወይም የውጪ አገር ተጫራቾች ለሚሳተፉበት የውስን ጨረታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1.1.1 ለውስን ጨረታ የተፈቀደው ዝቅተኛ ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

1.1.5. ተቋሙ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1.1.1ላይ የተገለጸው ዝቅተኛ የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጀትና ማቅረቢያ ጊዜ መሆኑን በመረዳት እንደግዥው ዓይነት እና የገበያው ሁኔታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንደአስፈላጊነቱ ተመጣጣኝ የሆኑ ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

## 1.2. <u>በዚህ አባሪ ተራ ቁጥር 1.1.2. መሠረት ውስብስብ ያልሆኑ ግዥዎች ዝርዝር</u>

| ዕቃዎች | የግንባታ ሥራዎች | የምክር አገልግሎት | ሌሎች አገልግሎቶች |
|---|---|---|---|
| • ለገበያ የተዘጋጁ የጽህፈት መሳሪያዎች<br>• ለገበያ የተዘጋጁ የፅዳት ዕቃዎች<br>• ለገበያ የተዘጋጁ ኮንፒውተሮች እና ተዛማኝ ዕቃዎች<br>• ለገበያ የተዘጋጁ ፕሪንተሮች<br>• ለገበያ የተዘጋጁ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች<br>• ለገበያ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ መለዋወጫዎች (ለምሳሌ ተሽከርካሪ፣ የቢሮ መገልገያ ማሽኖች)<br>• ለገበያ የተዘጋጁየኤሌትሪክ፣ ኤሌክትሮኒክስና ኢሌክትሮ ሜካኒካል ዕቃዎች<br>• ለገበያ የተዘጋጁ የቢሮ መገልገያ ማሽኖች(ለምሳሌ ፋክስ፣ ፎቶ ኮፒ፣ መጠረዣ ማሽን)<br>• የግንባታ ዕቃዎች(ለምሳሌ ሲሚንቶ፣ ብረት፣ አሸዋ፣ ቧንቧ፣ ቀለም፣ እንጨት፣ ምስማር)<br>• የምግብ ጥሬ ዕቃ እና የተዘጋጀ ምግብ<br>• ነዳጅና ልዩ ልዩ ቅባቶች<br>• ለገበያ የተዘጋጁ ልብሶች፣ጨርቆችና ጫማዎች<br>• ለገበያ የተዘጋጁ መድሃኒቶች እና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች<br>• ኬሚካሎች እና ሬኤጀንቶች<br>• ለገበያ የተዘጋጁ መጻሐፍትና ጆርናሎች | • የህንጻ ዕድሳ<br>• የቀለም ቅብ ሥራ<br>• የጊዜያዊ ቤቶች ስራ<br>• የአጥር ሥራ<br>• የቢሮ መከፋፈል (ፓርትሽን) ስራ | • ዝርዝር የጥናት አካሄድ ማቅረብ የማይጠይቁ አገልግሎቶች ግዥዎች | • የህትመት<br>• የተሽከርካሪ ጥገና<br>• የመሳሪያዎችና ዕቃዎች ኪራይ<br>• የቢሮ ዕቃዎችና ማሽኖች ጥገና<br>• የትራንስቶረት ኪራይ<br>• የሆቴልና መስተንግዶ<br>• የቧንቧ እና የኤሌትሪክ ጥገና<br>• የስልጠና<br>• የኦዲት አገልግሎት<br>• የጥበቃና የፅዳት<br>• የግዥ አገልግሎት<br>• የግቢ ማስዋብና ማስተካከል<br>• የቢሮ ማስዋብ<br>• የቢሮ ኪራይ<br>• የትርጉም ስራ |

- « ለገበያ የተዘጋጁ» ማለት ለተጠቃሚው ሕዝብ ፍላጎት ተብለው የሚመረቱ ስታንዳርድ የገበያ ዕቃዎች ሲሆኑ ለተቋሙ በተለየ ሁኔታ የሚመረቱትን አይጨምርም፡፡
- ተቋሙ ዝርዝር የጥናት አካሄድ የማያስፈልጋቸውን ውስብስብ ያልሆኑ የምክር አገልግሎቶች ዓይነት የሚፈልገውን የምክር አገልግት የሚኖረውን የጥናት ባሪያ በማየት ይወስናል፡፡

## በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17/26/7 በቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ለሕንጻ ግንባታ የሚገዙት ማሽነሪች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ለመንገድ ሥራ ተቋራጭ የተፈቀዱ ማሽነሪዎች | ለሕንጻ ስራ ተቋራጭ የተፈቀዱ ማሽነሪዎች |
|---|---|---|
| 1 | ቡል ዶዘር | እስካቫተር |
| 2 | ፍሮንት ኢንድ ሎደር | ሃይሮሊክ ብሬከር |
| 3 | ሞቶር ግሬደር | ክሬን |
| 4 | ትሬንች አክስካቫተር | ታወር ክሬን |
| 5 | ባክሆይ | ዶዘር |
| 6 | ግሪድ ሮለር | ትራክ ሚክሰር |
| 7 | ቫይብራቶሪ ሮለር | ሎደር |
| 8 | ወተር ቦውሰር | ዳምፕ ትራክ |
| 9 | ዳፕ ትራክስ | ስካፎልዲንግ |
| 10 | ትራክ ዊዝ ትሬለር | ፎርምወርክ |
| 11 | ሌቤድ ሀኡሊንግ ትራክ | ፍሮንት ኤንድ ዳምፐር |
| 12 | ቢቱመን ዳስትሪቢውተር | ኮምፓክተር/ሮለር |
| 13 | ስቴሽነሪ ሂተር | ባክሆ |
| 14 | ፔቨር ፎር ቤዝ ኮርስ | ክሬሸር |
| 15 | አስፓልት ፔቨር | ጀኔሬተር |
| 16 | ሰልፍ ፕሮፒልድ ቺፕ ስፒሬደር | ትራክ ዊዝ ትሬለር |
| 17 | ሜካኒካል ብሩም | |
| 18 | ታንደም ሮለር | |
| 19 | ቫይብሬትንግ ሮለር | |
| 20 | ፓድ ፉት ሮለር | |
| 21 | ፕኒውማቲክ ታየር ሮለር | |
| 22 | አስፓልት ፕላንት | |
| 23 | ክራሺንግ እና ስክሪኒንግ ፕላንት | |
| 24 | ዋጎን ድሪል | |
| 25 | ኮምፕሬሰር | |
| 26 | ክሬን | |
| 27 | ኮንክሪት ሚክሰር | |
| 28 | ጀነሬተር | |
| 29 | የኮንሰልታንቶች መቆጣጠሪያ ተሽከርካሪ | |

# በግዥ አፈጻጸም መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 23/2/5 መሰረት

# በተጫራቾች የሚሞላ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና

የግዥ መለያ ቁጥር----------------------(የጨረታ መለያ ቁጥር አስገባ)

ለ መንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

(የተጫራቹን ሙሉ ስም አስገባ ከአሁን በኋላ «ተጫራች» እየተባለ የሚጠራ የግዥ መለያ የዕ ቁጥር-------------) የግዥ መለያ ቁጥር እና የዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎታችን ----------------------(አጭር መግለጫ አስገባ) ካሁን በኋላ ጨረታው እየተባለ የሚጠራው ለማቅረብ በ----------------------/የጨረታ ማስከበሪያ ቀን---------/ቀን ወርና ዓ.ም አስገባ/ የተጻፈውን ጨረታ ያስገባን ስለሆነ እኔ-----------------------/የድርጅቱን ስምና ባለቤት ወይም የመፈረም ሥልጣን ያው ኃላፊ ስም አስገባ/ ከዚህ በታች የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /የጨረታ ዋስትናውን መጠንና የገንዘቡን ዓይነት በቃላትና በቁጥር ግልጽ/ ሙሉ ኃላፊነት ድርጅቱ የሚወስድ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የዋስትና ሰጪው የተለመደ ማህተም ተደርጎበት /ዋስትናው የሚቆይበት የቀን ብዛት በቁጥር፣ በወር ወይም በዓመት መሆኑ ተሌቶ ይገለጽ/ ይታሸጋል፡፡

የሚከተሉትን ግዴዎች በመረዳት ተፈጻሚ ለማድረግ ተስማምቻለሁ፡፡

ሀ/ በጨረታ ሠነዱ ላይ የተገለጸው የመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ጊዜ ካለፈ በኋላ ወይም በመጫረቻ ሠነዱ የተገለጸው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ከጨረታው ራሴን ላለማግለል፣ ወይም

ለ/ በመጫረቻ ሠነዱ የተገለጸው የጨረታ ዋጋ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የግዥ ውል እንድፈርም ከተቋሙ የቀረበልኝን የጸሁፍ ጥያቄ በመቀበል ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ለመሆን፣ ወይም

ሐ/ በጨረታው ውድድር አሸናፊ በመሆኔ ውል እንድፈርም እና የውል ማስከበሪያ እንዳስይዝ ስጠየቅ፣ የውል ማስከበሪያውን ለማስያዝ ፈቃደኛ ለመሆን፣ እና ከዚህ በላይ ተራ ሀ-ሐ እና በጨረታ ሠነዱ የተገለጹትን ሌሎች ተግባ፣ ባልፈጸም ተቋሙ በሚያቀርበው የጽሁፍ ጥያቄ ከላይ የተገለጸውን የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ለተቋሙ በአምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ለመክፈል ተስማምቻለሁ፡፡

ይህ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጨረታው ጸንቶ ከሚቆይበት ጊዜ በተጨማሪ ለ28 ቀናት በሕግ ፊት ፀንቶ ይቆያል፡፡ ይህን ዋስትና በተመለከተ ከተጠቀሰው ጊዜ ዘግይቶየሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

ስም----------------------/ ጨረታውን የሚፈርመው ስም ሙሉ ስምና ሕጋዊ ስልጣኑን አስገባ/

ፊርማ---------------------------/ ስምና ማዕጉን ከላይ የተጠቀሰውን ሰው ፊርማ አስገባ/

ወይም ወኪል ከሆነ ጨረታውን ለመፈረም ሕጋዊ ስልጣን የተሰጠው / ሰው ሙሉ ስምና ፊርማ አስገባ/

ቀን-------------------/ የተፈረመበትን ቀን፣ ወር እና ዓ/ም አስገባ/

# በግንባታ ሥራ ግዥ የብቃት መስፈርት አወሳሰን

1. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም

ሀ) ‹‹አነስተኛ ህንጻ (Low-Rise Building)›› ማለት ምንም ዓይነት አሳንሰር ወይም አሳንሰርን የሚተካ ከምድር ወደ ፎቅ እንዲሁም ከፎቅ ወደ ምድር የሚያመላልስ መሣሪያ የሌለው ሆኖ ከምድር በላይ ከአምስት ያነሱ ፎቆች ያለው ነው፣

ለ) ‹‹መካከለኛ ህንጻ (Mid-Rise Building)›› ማለት ከምድር ቢያንስ አምስት ፎቆች ያለው ሆኖ ከአሥራ አምስት ፎቆች በላይ የሌለው ነው፣

ሐ) ‹‹ከፍተኛ ህንጻ (High-Rise Building)›› ማለት ከምድር በላይ ቢያንስ አሥራ አምስት ፎቆች ያለው ሆኖ ከአርባ አምስት ፎቆች በላይ የሌለው ነው፣

መ) ‹‹በጣም ከፍተኛ ህንጻ (Mega-High Rise Building)›› ማለት ከምድር በላይ ቢያንስ አርባ አምስት እና ከዚያ በላይ ፎቆች ያለው ነው፣

ሠ) አጭር ርዝመት ያው ድልድይ (Short Span)›› ማለት ለተሽከርካሪዎች ወይም ለሌሎች የመጓጓዣ ዘዴዎች የሚያገለግል ሆኖ ርዝመቱ ከ25 (ሃያ አምስት) ሜትር ያነሰ ድልድይ ነው፣

ረ) ‹‹መካከለኛ ርዝመት ያለው ድልድይ (Medium Span)›› ማለት ለተሽከርካሪዎች ወይም ለሌሎች የመጓጓዣ ዘዴዎች የሚያገለግል ሆኖ ርዝመቱ ከ25 (ሃያ አምስት) ሜትር የማያንስ እና ከ50 (ሃምሳ) ሜትር የማይበልጥ ድልድይ ነው፣

ሰ) ‹‹ረጅም ርዝመት ያለው ድልድይ (Long Span)›› ማለት ለተሽከርካሪዎች ወይም ለሌሎች የመጓጓዣ ዘዴዎች የሚያገለግል ሆኖ ርዝመቱ ቢያንስ 50 (ሃምሳ) እና ከዚያ በላይ የሆነ ድልድይ ነው፣

ሸ) ‹‹በአጥጋቢ ሁኔታ የተጠናቀቀ›› ማለት የሥራው 70% (ሰባ በመቶ) እና ከዚያ በላይ የተጠናቀቀ የግንባታ ሥራ ፕሮጀክት ነው፣

ቀ) «በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቀ» ማለት በሥራ ተቋራጩ የተሠራው 70% (ሰባ በመቶ) እና ከዚያ በላይ በተቀመጠለት የጊዜ ሠሌዳ እና በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለመሠራቱ ከአሠሪ መ/ቤቱ የተሰጠ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ የቀረበበት የግንባታ ሥራ ፕሮጀክት ነው፡፡

2. <u>አጠቃላይ ልምድን በተመለከተ</u>

ሀ) የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በሚሰጠው ደረጃ መሠረት ከደረጃ 6 እስከ 10 ካሉት በስተቀር ሌሎች የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች በሥራ ተቋራጭ፣ በሽርክና ማኅበር (Joint Venture) ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ በዘርፉ ቢያንስ የ2 ዓመት የሥራ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ለ) የውጪ ሀገር ሥራ ተቋራጮች በሥራ ተቋራጭ፣ በሽርክና ማኅበር ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭ ደረጃ በዘርፉ ቢያንስ የ5 ዓመት ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

3. <u>ተዛማጅ የሥራ ልምድን በተመለከተ</u>

ሀ) የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ሥራ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ቢያንስ አንድ የግንባታ ሥራ በሥራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማኅበር አባልነት ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት የሠሩና ከሚወዳደሩበት ሥራ በዋጋ ቢያንስ 70% (ሰባ በመቶ) የሆነን ስራ በአስተማማኝ እና አጥጋቢ ሁኔታ ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡

ለ) የግንባታ ሥራው ግንት ከብር አንድ ቢሊዮን በታች ሲሆንና፣ ሥራ ተቋራጮች በፊደል ተራ «ሀ» ላይ የተጠየቀውን የተዛማጅ ሥራ ልምድ ዋጋ በአንድ ፕሮጀክት በሰሩት የሥራ ልምድ ብቻ ማሟላት ካልቻሉ በአጥጋቢ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቁና ሊሰራ ከተፈለገው ሥራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሁለት ፕሮጀክቶች ዋጋ ድምር በልምድነት ሊያዝላቸው ይችላል፡፡ ሆኖም የሁለቱ ፕሮጀክቶች የተናጠል ዋጋ ማሟላ ከሚገባቸው የሥራ ልምድ ዋጋ ከግማሽ (1/2) በታች መሆን አይኖርበትም፡፡

ሐ) የግንባታ ሥራው ግምት ከብር አንድ ቢሊዮን እና ከዚያ በላይ ሲሆንና፣ ሥራ ተቋራጮች በፊደል ተራ «ሀ» ላይ የተጠየቀውን የተዛማጅ ሥራ ልምድ ዋጋ በአንድ ፕሮጀክት በሰሩት የሥራ ልምድ ብቻ ማሟላት ካልቻሉ በአጥጋቢ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቁ ሁለት ወይም ሦስት ፕሮጀክቶች ድምር በልምድነት ሊያዝላቸው ይችላል፡፡ ሆኖም የሁለቱ የሦስቱ ፕሮጀክቶች የተናጠል

ዋጋ ማሟላት ከሚገባቸው የሥራ ልምድ ዋጋ እንደቅደም ተከተላቸው ከግማሽ (1/2) ወይም ከሢሦ (1/3) በታች መሆን የለበትም፡፡

መ) የውጭ ሀገር ሥራ ተቋራጮች ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ሊሰራ ከታሰበው የግንባታ ሥራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ቢያንስ ሁለት የግንባታ ሥራዎችን በሥራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማኅበር አባልነት ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት የሠሩና ቢያንስ የሥራውን 80% (ሰማንያ በመቶ) በአስተማማኝ እና በአጥጋቢ ሁኔታ ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው፡፡

ሠ) ተቋራጩ ያቀረበው የሥራ ልምድ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ወይም በሽርክና ማኅበር አባልነት የተገኘ ሲሆን፣ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት የሠራው መጠን ብቻ ወይም በሽርክና ማኅበሩ ካለው ድርሻ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ልምድ ብቻ በሥራ ልምድነት እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡

ረ) ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሥራ ተቋራጩ በሥራ ልምድነት እንዲያዝለት በሚያቀርበወ የግንባታ ዋጋ ላይ ማስተካከያ የሚደረገው፣ ጨረታ ከሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን 28 ቀናት በፊት የነበረው የምንዛሪ ምጣኔን ውሉ በተፈረመበት ጊዜ በነበረው የምንዛሪ ምጣኔ በማካፈል ከተሰላ በኋላ በሚገኘው ወጤት በማባዛት ነው፡፡ ማስተካከያው የሚሰላው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚሰጠውን የውጭ አገር ገንዘብ መሸጫ ዋጋ መረጃ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

ሰ) የሚጠየቀው የሥራ ልምድ ተመሳሳይነት የሚወሰነው በዚህ አባሪ በተገለፀው ዝርዝር አሠራር መሠረት ሆኖ ለሕንፃ ግንባታ ሥራ የሕንፃውን ቁመት፣ ለመንገድ ግንባታ ሥራ የመንገዱን ዓይነትና ርዝመት፣ ለድልድይ ሥራ የድልድዩን ርዝመት መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ ለሀገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች የሚጠየቀው የሥራ ልምድ በሁሉም የግንባታ ዘርፍ ሊሰራ ከታሰበው ሥራ አንድ ደረጃ ዝቅ ያለ እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

4. <u>የፋይናንስ አቋምን በተመለከተ</u>

ሀ) የሥራ ተቋራጮች ያለፉት አምስት ዓመታት የፋይናንስ አቋማቸውንና ትርፋማነታቸውን የሚያሳይ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ለ) በሥራ ተቋራጮቹ የሚቀርበው የፋይናንስ ሪፖርት ከሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ከሚገኝ ሪከርድ ጋር ተመሳክሮ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 5. ዓመታዊ የተርንኦቨር መጠንን በተመለከተ

ሀ) የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሚወሰደው በግንባታ ላይ ካለና ከተጠናቀቀ የግንባታ ሥራ ላይ የተሰበሰበ ክፍያ ዓመታዊ ተርንኦቨር መካከል ተቋራጩ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ካስመዘገበው የግንባታ ሥራ ዓመታዊ ተርንኦቨር የተሻለውን በመምረጥ ሆኖ፣ ሥራ ተቋራጮች እንዲያሟሉ የሚጠየቁት የተርንኦቨር መጠን የሚሰላው ለስራ የታሰበውን የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ፣ ቀናትን ወደሚቀጥለው ሙሉ ወር በማጠጋጋት ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በሚገመትበት ወርሃዊ ጊዜ በማካፈል እና ውጤቱን በ12 እና 0.8 በማባዛት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ፕሮጀክት በሁለት ዓመት ከአንድ ወር ከ10 ቀን የሚጠናቀቅ ቢሆንና የዋጋ ግምቱ ብር 100 ሚሊዮን ቢሆን ሂሳቡ እንደሚከተለው ይሰላል፡፡

$$\frac{\text{የግምት ዋጋ}}{\text{የሚወስደው ጊዜ(በወር)}} \times 12 \times 0.8 = \text{ሥራ ተቋራጮች እንዲያሟሉ የሚጠየቁት የተርንኦቨር መጠን}$$

$$\frac{100{,}000{,}000}{26} \times 12 \times 0.8 = \text{ብር } 36{,}923{,}077$$

ለ) የውጭ ሀገር ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሚወሰደው በግንባታ ላይ ካለና ከተጠናቀቀ የግንባታ ሥራ ላይ የተሰበሰበ ክፍያ ዓመታዊ ተርንኦቨር፣ የተቋራጩ ያለፉት አምስት ዓመታት ዓመታዊ የግንባታ ተርንኦቨር አማካይ ሆኖ፣ የሚጠየቀው መጠን የሚሰላው ሊሠራ የታሰበውን የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ፣ ቀናትን ወደሚቀጥለው ሙሉ ወር በማጠጋጋት ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በሚገመትበት ወርሃዊ ጊዜ በማካፈል እና ውጤቱን በ2 በማባዛት ይሆናል፡፡

ሐ) በሽርክና ማኅበር ደረጃ ጥምረት ፈጥረው የሚወዳደሩት ሥራ ተቋራጮች የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር በሚሆኑበት ጊዜ ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሚወሰደው በግንባታ ላይ ካለና ከተጠናቀቀ የግንባታ ሥራ ላይ የተሰበሰበ ክፍያ ዓመታዊ ተርንኦቨር የሥራ ተቋራጮቹ ያለፉት አምስት ዓመታት ዓመታዊ የግንባታ ተርንኦቨር ድምር አማካይ ሆኖ የሚጠየቀው መጠን የሚሰላው ሊሰራ የታሰበውን የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ፣ ቀናትን ወደሚቀጥለው ሙሉ ወር በማጠጋጋት ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በሚገመትበት ወርሃዊ ጊዜ በማካፈል እና ውጤቱን በ1.5 በማባዛት ይሆናል፡፡

መ) በጨረታ ግምገማ ጊዜ ለሚደረግ ማስተካከያ ዓላማ ለተርንኦቨር ስሌት የሚወሰደው ሥራ ተቋራጩ ያቀረበው ዓመታዊ የግንባታ ሥራ ተርንኦቨር መጠን፣ ጨረታ ከሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን 28 ቀን በፊት የነበረውን የምንዛሪ ምጣኔን በእያንዳንዱ በጀት ዓመት የመጨረሻ ቀን ላይ ባለው የምንዛሪ ምጣኔ በማካፈል ነው፡፡ ማስተካከያው የሚሰላው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚሰጠውን የውጭ አገር ገንዘብ መሸጫ ዋጋ መረጃ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

ሠ) ሥራ ተቋራጮቹ በሽርክና ማኅበር ደረጃ ጭምረት የፈጠሩ ከሆኑ እያንዳንዳቸው የሽርክና ማኅበሩ አጋር ድርጅቶች ማሟላት የሚገባቸው የተርንኦቨር መጠን ከተጠየቀው ከ25 በመቶ እና የዋናው ሥራ ተቋራጭ ደግሞ ከ40 በመቶ ማነስ የለበትም፡፡

ረ) የምህንድስና ዋጋ ግምት እና የግንባታው ሥራ የሚፈጀውን ጊዜ የመወሰን ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም አካል የምህንድስና ዋጋውን ወይም ሥራው የሚፈጀውን ጊዜ ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ያዘጋጀ ስላለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠትና፣ ግምቱም በግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ መፅደቅ ይኖርበታል፡፡

6. <u>በግንባታ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅትና ብቃትን በተመለከተ</u>

የሥራ ተቋራጮች የጨረታ ሰነዱ ላይ በሚገለፀው መሠረት እንደ ግንባታ ሥራው ባሕርይ ለሥራው የሚያስፈልጉ ብቁ ባለሙያዎችን በሚፈለገው መጠን እና ስብጥር እንደሚያቀርቡ ማሳየትና ባለሙያዎቹም ለሥራው በሚያስፈልጉበት ጊዜ ሁሉ በተመደቡበት ቦታ ላይ ለመሥራት ግዴታ የገቡ መሆኑን የሚያመለክት አስተማማኝ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ባለሙያዎቹም የግንባታ ሥራ ተቋራጩ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ሠራተኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

7. <u>የግንባታ መሣሪያ መሟላትን በተመለከተ</u>

የሥራ ተቋራጮች የጨረታ ሰነዱ ላይ በሚገለፀው መሠረት እንደ ግንባታ ሥራው ባህርይ ለሥራው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን ዓይነት እና መጠን በሚፈለጉበት ጊዜ ሁሉ ማቅረብ እንደሚችሉ የሚያሳይ ማረጋገጫ ማቅረብ የኖርባቸዋል፡፡ የሚቀርቡት መሣሪያዎችም በሥራ ተቋራጩ ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ወይም በኪራይ የተገኙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

8. <u>ከአንድ በላይ ንዑሳን የግንባታ ሥራዎች (Lots) በተካተቱበት ግዥ ላይ የልምድ አያያዝን በተመለከተ</u>

ሀ) በአንድ የጨረታ ማስታወቂያ የሚወጡት ንዑስ የግንባታ ሥራዎች ቁጥር ከአንድ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ማንኛውም ተጫራች መሳተፍ የሚፈልግባቸውን ንዑስ የግንባታ

ሥራዎች ዓመታዊ ተርንኦቨር፣ የገንዘብ አቅምና ተዛማጅ የሥራ ልምድ መስፈርት በድምር ማሟላት አለበት፡፡

ለ) አንድ ተጫራች ለእያንዳንዱ ንዑስ የግንባታ ሥራ የተጠየቀውን መስፈርት አሟልቶ ነገር ግን ለተሳተፈባቸው ንዑስ የግንባታ ሥራዎች በድምር የሚጠየቀውን መስፈርት በማያሟላበት ጊዜ ምንም እንኳን በተናጠል ሲታይ ለየንዑስ የግንባታ ሥራዎቹ የተሻለ ዋጋ ቢያቀርብም፣ ውል ሊፈጽም የሚችለው መስፈርቶቹን ማሟላት በቻለበት ልክ ብቻ ሲሆን፣ ለግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ የተሻለ ጠቀሜታ ከማስገኘት አንፃር ድርጅቱ ውል የሚገባበትን ንዑስ የግንባታ ሥራ ወይም የግንባታ ሥራዎች የመወሰን ሥልጣን የግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ ይሆናል፡፡

9. <u>ለህንጻ ግንባታ ሥራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት</u>

ሀ) ለህንጻ ግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ ሲሆን፣ የሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት ሊሠራ ከታሰበው የህንጻ ሥራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ በአነስተኛ ህንጻ ሥራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ ለመካከለኛ ህንጻ ግንባታ ሥራ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

ለ) ለህንጻ ግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የውጭ አገር ሥራ ተቋራጭ ሲሆን፣ ሊሠራ ከታሰበው የህንጻ ደረጃ ጋር እኩል የሆነ ወይም የበለጠ የህንጻ ሥራ ልምድ ሊኖረው ይገባል፡፡ ለምሳሌ ከምድር በላይ 70 (ሰባ) ፎቆች ያሉት ህንጻ ለመሥራት የሚወዳደር የውጭ አገር ሥራ ተቋራጭ ያለው ልምድ በማናቸውም ሁኔታ ከምድር በላይ 70 (ሰባ) ፎቆች ያሉትን ህንጻ ከመገንባት ያነሰ ልምድ ሊሆን አይገባም፡፡

10. <u>ለድልድይ ግንባታ ሥራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት</u>

ሀ) ለድልድይ ግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ ሲሆን፣

1) በህንጻ ፕሮጀክቶች ሥራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ አጭር ርዝመት ያለው ድልድይ ግንባታ ሥራ ላይ ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል፣

2) አጭር ርዝመት ባለው ድልድይ ግንባታ ሥራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ መካከለኛ ርዝመት ያለው ድልድይ ግንባታ ሥራ ላይ ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

3) መካከለኛ ርዝመት ባለው ድልድይ ግንባታ ሥራ ልምድ ያለው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ ረጅም ርዝመት ያለው ድልድይ ግንባታ ሥራ ላይ ለመወዳደር ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

ለ) ለድልድይ ግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የውጭ አገር ሥራ ተቋራጭ ሲሆን፣

1) የውጭ አገር ሥራ ተቋራጭ የሚጠየቀው የድልድይ ግንባታ ሥራ ልምድ ሊሠራ ከታሰበው የድልድይ ሥራ ያነሰ ሊሆን አይገባም፡፡

2) ግዥ ፈጻሚው መሥሪያ ቤት ለውጭ አገር ሥራ ተቋራጭ ከሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት በተጨማሪ በተወሰነ የድልድይ ዓይነት የድልድይ ግንባታ ሥራ ልምድ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ የቀስት ቅርጽ ያለው ድልድይ (Arch Bridge) ሆኖ ርዝመቱ ቢያንስ 50 ሜትር እና ከዚያ በላይ የሆነ ድልድይ የመስራት ልምድ ያለው በሚል ሊጠየቅ ይችላል፡፡

11) <u>የመንገድ ፕሮጀክቶች አመዳደብ በንጣፍ ዓይነት</u>

የመንገድ ፕሮጀክቶች አመዳደብ የሚከተለው ይሆናል፡፡

1) አስፋልት ኮንክሪት ንጣፍ ወይም ደረቅ ንጣፍ ያለው (Asphalt Concrete Pavement of Rigid Pavement)፣

2) ሁለት ድርብርብ ቢትዩሚነስ (Bituminous) ክፍል ያለው ንጣፍ ወይም ሦስት ድርብርብ ያለው ንጣፍ እና የመሳሰሉት (DBST Pavement, Triple surface treatment etc)

3) ጥምር ልባስ ያለው ወይም የጠጠር መንገድ (Aggregate surfacing /Gravel)

12) <u>ለመንገድ ፕሮጀክቶች የግንባታ ሥራ የሚጠየቅ ዝቅተኛ መስፈርት</u>

ሀ) ለመንገድ ፕሮጀክቶች የግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ ሲሆን፣ ሊሠራ ከታሰበው የመንገድ ሥራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ልምድ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን የመንገድ ግንባታ ስራው የዋጋ ግምት ከብር 400 (አራት መቶ) ሚሊዮን በታች በሚሆንት ጊዜ ሁለት ደረጃ ዝቅ ያለ እና ከዚያ በላይ የሆነ ፕሮጀክት ለተዛማጅ ስራ ልምድነት ሊያዝ ይችላል

ለ) ለመንገድ ፕሮጀክቶች የግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የውጭ አገር ሥራ ተቋራጭ ሲሆን፣ የውጭ አገር ሥራ ተቋራጭ ሊሠራ ከታሰበው የመንገድ ፕሮጀክት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ወይም የበለጠ የመንገድ ሥራ የግንባታ ልምድ ሊኖረው ይገባል፡፡ የሚጠየቀው የገንዘብ መጠን በማናቸውም ሁኔታ ሊሠራ በታሰበው የመንገድ ሥራ ከተገመተው የገንዘብ መጠን ሊያንስ አይገባም፡፡

## በገንዘብ ሚኒስቴር እና የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባለሙያዎች በተቋሙ ረቂቅ የግዥ መመሪያ ላይ ስለቀረበ ሪፖርት

በመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የግዥ መመሪያ ረቂቅ ላይ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባለሙያዎች ታይቶ አስተያየት እንዲሰጥ አቅጣጫ ተሰጥቷል። በዚሁ መሠረት በባለሙያዎች የተሰጠውን አስተያየት ከረቂቁ ጋር በማገናዘብ የተደረገው ማስተካከያ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. **ስለመመሪያው አስፈላጊነት (አጠቃላይ)**

   በባለሙያዎቹ በመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የተዘጋጀው ረቂቅ የግዥ መመሪያ ከፌዴራል መንግሥት ግዥ መመሪያ በቀጥታ የተወሰደ ስለሆነ በአጭሩ የፌዴራል መንግሥት ግዥ መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናል ቢባል በማለት አጠቃላይ የሆነ አስተያየት ተሰጥቷል።

   ሆኖም ኤጀንሲው ከጡረታ ፈንዱ በሚመደብለት በጀት የሚተዳደርና በፌዴራል መንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 2(6) ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተሰጠው ትርጉም ስለማይሸፈን አዋጁና የፌዴራል ግዥ መመሪያው በቀጥታ ተፈጻሚ እንደማይሆን በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመገለጹ የፌዴራል መንግሥት ግዥ መርህ የሚከተልና ከአዋጁ ጋር የሚጣጣም መመሪያ መዘጋጀቱን ማብራሪያ ተሰጥቷል። በዚሁ መሠረት መመሪያው ከፌዴራል መንግሥት ግዥ ጋር በሚጣጣም ሁኔታ መዘጋጀቱ ተገቢ እንደሆነ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

2. **በረቂቅ መመሪያው አንዳንድ አንቀጾች ላይ በግዥ ባለሙያዎች ስለተሰጠ አስተያየት**

   2.1 በረቂቁ አንቀጽ 6.11 ስለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ «መቋቋም» የተገለጸው በሌላ አንቀጽ የተገለጸና የተደገመ ስለሆነ እንዲወጣ የቀረበውን ሀሳብ በመቀበል ተስተካክሏል።

   2.2 በረቂቁ አንቀጽ 6.18 የግዥ ዕቅድ ከፀደቀ በኋላ ለማን እንደሚቀርብ ግልጽ አይደለም ተብሎ የተሰጠውን አስተያየት በሚመለከት የተፈጸሙ ግዥዎችን እንደአስፈላጊነቱ ጊዜውን ጠብቆ ለሥራ አመራር ቦርድ እና ለሚመለከተው አካል መቅረቡን ይከታተላል በማለት ተስተካክሏል፣

2.3 በረቂቁ አንቀጽ 7.4 የተዘረዘሩ መረጃዎች ብቻ በቂ እንዳልሆኑ በመገለጹ «ሰ) ሌሎች ተፈላጊና ተያያዥ የግዥ መረጃዎች /ሰነዶችን/» የሚለው ሀሳብ ተጨምሯል፡፡

2.4 በረቂቁ አንቀጽ 7.9 እና 7.10 ላይ «የኤጀንሲው ድረገጽ...» ለመጠቀም የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር መነጋገር እንደሚያስፈልግ የተገለጸ ሲሆን በረቂቅ መመሪያው የተጠቀሰው የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ «ዌብ ፖርታል» መሆኑን በማስረዳት የጋራ ግንዛቤ ተይዟል፡፡

2.5 በረቂቁ አንቀጽ 14.3 የግዥ ዕቅድ ለሥራ ሂደቶች፣ ሪጅንና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እስከ ሐምሌ ወር ይላካል የተባለው ቀኑ ይጠቀስ በማለት የተሰጠውን አስተያየት በመቀበል ሐምሌ 30 ቀን በማለት ተስተካክሏል፡፡

2.6 በረቂቁ አንቀጽ 17.2 ፊደል ተራ ‹ለ› ከ100 ሺህ በላይ የሆነ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች የቫት ተመዝጋቢ መሆኑን ማስረጃ ማቅረብ እንደሚገባው የተጠቀሰውን በሚመለከት በታክስ /ግብር/ አዋጅ መጠኑ ሊቀንስና ሊጨምር ስለሚችል ቢስተካከል ስለተባለው በግብር አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር የሚል ሀሳብ ተጨምሮ ተስተካክሏል፡፡

2.7 በረቂቁ አንቀጽ 17.8.2 (ለ) ስለቴክኒክና ዋጋ ክብደት (Merit point evaluation system) በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ መመሪያ ላይ ክፍተት ያለ ስለሆነና Merit point evaluation system ለግንባታ ሥራ መጠቀም ስለማይቻል እንዲስተካከል በተሰጠው አስተያየትና ከባለሙያዎቹ ጋር በተደረገ ውይይት መሠረት ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

2.8 በረቂቁ አንቀጽ 17.14.2 ፊደል ተራ ‹ሀ› የግንባታ ሥራ ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ ግንባታውን ለማጠናቀቅ የሚወስደው ጊዜ 12 ወር እና ከዚያ በላይ የተባለው 18 ወር እና ከዚያ በላይ በሚል ቢተካ በሚል የቀረበው ሀሳብ በፌዴራል መንግሥት ግዥ መመሪያ ላይ ቀደም ሲል የተደረገው ማሻሻያ ለተቋሙ ባለመድረሱ ምክንያት የተፈጠረ ክፍተት መሆኑ ስለታወቀ በቀረበው ሀሳብ መሠረት ተስተካክሏል፡፡

2.9 በተራ ቁጥር 2.8 ከተገለጸው ጋር ተያይዞ «በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አጀንሲ የሚሰጥ የገበያ ዋጋ» የሚለው ከማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ በሚሰጥ የገበያ ዋጋ» በሚል ብቻ እንዲተካ የቀረበውን አስተያየት በመቀበል ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

2.10 በረቂቁ አንቀጽ 17.20.3 ‹‹ልዩ አስተያየት ለማግኘት ዕቃውን ለማምረት ከወጣው ጠቅላላ ወጪ 35% የታከለ እሴት ሲኖር›› የሚለው ማሻሻያ እየተሰራ ስለሆነ ዝቅ ቢደረግ በማለት በቀረበው ሀሳብ መሠረት 25% በሚል ተስተካክሏል፡፡

3. ከላይ በዝርዝር በአንቀጾች ላይ ከተመለከተው ሀሳብ በተጨማሪ በገንዘብ ሚኒስቴር ባለሙያ የሕግና አፈጻጸምን አስመልክቶ አስተያየት የተሰጠ ሲሆን፡-

3.1 የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰንን በሚመለከት ከተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤት አልፎ ሪጅን፣ ቅርንጫፎችና መስክ ጽ/ቤቶች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን የተገለጸው ክፍተት እንደሚፈጥር አስተያየት ተሰጠቷል፡፡ ሀሳቡን በመቀበል መመሪያው በዋና መሥሪያ ቤት፣ በሪጅኖችና በተለይ ተገድቦ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚሰጥ ውክልና በሚፈጸሙ ግዥዎች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡

3.2 ተጫራቾች በመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ በአቅራቢነት መመዝገብ እንዳለባቸው በረቂቅ መመሪያው ላይ ያለመገለጹን አስመልክቶ ለቀረበው አስተያየት ሀሳቡ በረቂቁ አንቀጽ 51(4) በግልጽ የተቀመጠ ስለሆነ ማስተካከያ ማድረግ እንደማያስፈልግ ስምምነቱ ላይ ተደርሷል፡፡

3.3 በረቂቁ አንቀጽ 17.20.1 **ልዩ አስተያየት** ስለሚደረግበት ሁኔታ በፌዴራል መንግሥት የግዥ መመሪያ ለገንዘብ ሚኒስቴር የተሰጠውን ሥልጣን ይሽራል ስለተባለው ኤጀንሲው የራሱ መመሪያ በማውጣት በሥራ አመራር ቦርድ ስለሚያፀድቅና እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያ በማድረግ በሚኒስቴሩ ከሚወጣው መመሪያ ጋር የማጣጣም ሥራ ስለሚከናወን ክፍተት እንደማይኖር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

3.4 የማዕቀፍ ግዥን በሚመለከት ለፌዴራል መንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አስቀድሞ ዕቅድ በማሳወቅና በማስፈቀድ መጠቀም እንደሚቻል በረቂቁ እንዲገለጽ የተሰጠውን አስተያየት በመቀበል ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

3.5 የግንባታ ግዥ ብቃት መስፈርት አወሳሰን /አባሪ 6/ አስመልክቶ ስለቀረበው አስተያየት አባሪው ላይ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ማሻሻያዎችን በማካተት ረቂቁ መዘጋጀቱን ለባለሙያዎቹ በማስረዳት ረቂቁ በትክክል መዘጋጀቱን ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡